# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና

# የኮምኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና

# ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በበቶሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ከላይታች እና ከታችላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ ለመረዳት ክሂል ያላቸውን አስተዋጽኦ በማነፃፀር የተሻለውን ሞዴል ለመለየት 7ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ ጥናት

**በ**


አንድነት እርገቱ


ታህሳስ፣ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በበቶሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ከላይታች እና ከታችላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ ለመረዳት ክሂል ያላቸውን አስተዋጽኦ በማነፃፀር የተሻለውን ሞዴል ለመለየት 7ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ ጥናት

ለተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተርስ ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

አንድነት እርገቱ


ታህሳስ፣ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና**

**የኮምኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና**

**ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**


# በበቶሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ከላይታች እና ከታችላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ ለመረዳት ክሂል ያላቸውን አስተዋጽኦ በማነፃፀር የተሻለውን ሞዴል ለመለየት 7ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ ጥናት


**በ**

አንድነት እርገቱ


## የፈተና ቦርድ አባላት

| ስም | ፊርማ |
| --- | --- |
| ______________________ | __________ |
| አማካሪ | |
| ______________________ | __________ |
| ፈታኝ | |
| ______________________ | __________ |
| ፈተኝ | |

# ምስጋና

ከሁሉም አስቀድሞ ነገሮችን ሁሉ አሳክቶ ለዚህ ያበቃኝ ልዑል እግዚአብሔር አመሰግናለሁ፡፡

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የመጨረሻውን ቅርጽ እስኪይዝ ድረስ የእረፍት ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በማማከር ሙያዊ እግዛቸው ያልተለየኝ አማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማውን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ለዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ስኬታማነት በጣም አስፈላጊ የሆነውን የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለጥናታዊ ጽሑፉም የሚሆኑትን መረጃዎች ለሰጡኝ ለበቶሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንና ተማሪዎች፣ ከጐኔ በመሆን ለጥናቱ የሚያስፈልገኝን የተለያዩ ሃሳቦችንና ቁሳቁሶችን በመተባበር ለረዳችኝ ጓደኛዬ ሐድራ መሐመድ እንዲሁም በትምህርቴ ወቅትም ሆነ ጥናቱን በሚካሄድበት ወቅት ባጋጠመኝ ችግር ከጐኔ በመሆን አይዞሽ በማለት ያበረታታችኝን ወንድሜ ፋኖስ አስታጥቄ በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡

የጽሑፍን ስራ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል በመፃፍ ለተባበረችኝ ወ/ሪት አማረች አለልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ ii
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ v
አጠቃሎ ........ vi
ምዕራፍ አንድ
1. መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.3 የጥናቱ ዓላማ ........ 3
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.6 መላምት ........ 4
ምዕራፍ ሁለት
2. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ........ 5
2.1 የማንበብ ክሂል ምንነት ........ 5
2.2 የማንበብ ትምህርት ዓላማ ........ 5
2.3 የማንበብ ትምህርት የአቀራረብ ደረጃዎች ........ 7
2.3.1 ቅድመ ማንበብ ........ 7
2.3.2 በማንበብ ጊዜ ........ 8
2.3.3 የድህረ ማንበብ ደረጃ ........ 10
2.4 የማንበብ ትምህርት የመልመጃ ጥያቄዎች ዓይነት ........ 11
2.5 የአነባብ ስልቶች ........ 12
2.5.1 የዝርዝር ንባብ (Detailed reading) ........ 12
2.5.2 የአሰሳ ንባብ (Scanning) ........ 13
2.5.3 የገረፍታ ንባብ (Skimming) ........ 14
2.5.4 አመሳካሪ ንባብ (Intensive reading) ........ 15

2.5.5 ሰፊ ንባብ (Extensive Reading) ........ 15
2.5.6 ሂሳዊ ንባብ (Critical Reading) ........ 16
2.6 የምንባብ አመራረጥ ........ 16
2.7 የማንበብ ክሂልን የማስተማሪያ ሞዴሎች ምንነት ........ 17
2.7.1 የላይ-ታች ሞዴል (Top Down) ........ 17
2.7.2 የታች-ላይ ሞዴል (Bottom Up) ........ 18
2.8 ቀደምት የጥናትና የምርምር ስራዎች ቅኝት ........ 19
ምዕራፍ ሦስት
3. የአጠናን ዘዴ ........ 21
3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 21
3.2 የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ........ 21
3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ ........ 21
3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........ 21
3.3 የምንባቦች አመራረጥ የመልመጃዎች አዘገጃጀት ........ 22
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 23
3.4.1 የፈተና አዘገጃጀትና አፈታተን ........ 23
3.4.2 ለተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ ........ 24
3.4.3 ምልከታ ........ 25
3.5 የመረጃ አተናተን ........ 25
3.5.1 ከፈተና ውጤቶች የተገኙ መረጃዎች ........ 25
3.5.2 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት ........ 25
3.5.3 ከምልከታ የተገኘ ውጤት ........ 26
ምዕራፍ አራት
4. በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 27
4.1 የፈተና ውጤት ትንተና ........ 28
4.1.1 የቅድመ ልምምድ ፈተና ትንተና ........ 28
4.1.2 የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ትንተና ........ 31
4.2 ለተማሪዎች ከተሠራጨው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና ........ 34
4.2.1 በክፍል አንድ የቀረቡ ጥያቄዎች ውጤት ትንተና ........ 34

4.2.2 በክፍል ሁለት ተማሪዎች ልምምድ ከማድረጋቸው በፊት እየተማሩ ስላሉት የማንበብ ትምህርት አቀራረብ የተጠየቁትን አስተያየት የሚያሳይ ...... 35
4.3 ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ...... 48
4.3.1 ከልምምድ በፊት ከተደረገ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና...... 49
4.3.2 በልምምድ ወቅት ከተካሄደ የክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና ...... 50
ምዕራፍ አምስት
5. ማጠቃለያ እና አስተያየት...... 54
5.1 ማጠቃለያ ...... 54
5.2 አስተያየት...... 55
ዋቢ ጽሑፎች
አባሪ

## የሰንጠረዥ ማውጫ


ገጽ

**ሰንጠረዥ** 1፡ የቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤትን የሚያሳይ ............ 29

**ሰንጠረዥ** 2፡ የቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤትን ጠቅለል ባለ መልኩ የሚያሳይ ............ 30

**ሰንጠረዥ** 3፡ የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤትን የሚያሳይ ............ 31

**ሰንጠረዥ** 4፡ የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤትን ጠቅለል አድርጎ የሚያሳይ ............ 32

**ሰንጠረዥ** 5፡ የቅድመና የድህረ ፈተና ውጤትን የሚያሳይ ............ 33

**ሰንጠረዥ** 6፡ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች ፆታ፣ ዕድሜ፣
የአፍ መፍቻ ቋንቋን የሚያሳይ ............ 34

**ሰንጠረዥ** 7፡ ለተጠያቂዎች ስለ ቅድመ ልምምድ ያላቸውን ግንዛቤ የሚጠይቅ ............ 36

**ሰንጠረዥ** 8፡ ለልምምድ የቀረቡ የመልመጃ ጥያቄዎችና አተገባበራቸውን የሚያሳይ ............ 39

**ሰንጠረዥ** 9፡ ለልምምድ የቀረቡ ምንባቦች አቀራረብና ትግበራን የሚያሳይ ............ 41

**ሰንጠረዥ** 10፡ ዓላማን ወስኖ ማንበብ ላይ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ............ 43

**ሰንጠረዥ** 11፡ በላይታች ሞዴል ልምምድ በማድረጋቸው ምን ግንዛቤ
እንደጨበጡ የሚያሳይ ............ 45

**ሰንጠረዥ** 12፡ በታችላይ ሞዴል ልምምድ በማድረጋቸው ምን
ግንዛቤ እንደጨበጡ የሚያሳይ ............ 47

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በላይታች እና በታችላይ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ ለመረዳት ክሂል ያላቸውን አስተዋጽኦ በማነፃፀር ከሁለቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክተውን ሞዴል መለየት ነው፡፡ ይህንንም ዓላማ ለማሳካት ለጥናቱ መረጃ ሰጪ ሆነው በጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሳሪያዎች በዋናነት ቅድመ ልምምድ ፈተና እና ድህረ ልምምድ ፈተና ሲሆኑ በተጨማሪም የጽሑፍ መጠይቅና ምልከታ ናቸው፡፡ በእነዚህም መሳሪያነት መረጃዎችን ለማግኘት በበቶሙሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሰባተኛ ክፍል ምድቦች ሁለቱ በእጣ ናሙና ከተለየ በኋላ በላይታች የትኛው መለማመድ እንዳለበትና በታችላይ የትኛው መለማመድ እንዳለበት በድጋሚ እጣ በማውጣት ተለየ፡፡ ሙከራዊ የምርምር ዓይነትን መሰረት በማድረግም የተገኙ መረጃዎችን መጠናዊ የምርምር ዘዴን መሠረት በማድረግ ተተንትኗል፡፡ ከልምምዱ በፊት ተመሳሳይ ፈተና ተሰጥቷቸው ውጤቱ በቲ-ቴስት ሲሰላ የቲ-ቴስቱ ዋጋ 0.81 ከቲ-ሰንጠረዡ ዋጋ 1.6645 ያነሰ ስለሆነ በሁለቱ መካከል የአንብቦ የመረዳት ችሎታ መበላለጥ እንደሌላቸው ተረጋግጧል፡፡ ለአንድ ወር ከአምስት ቀን ልምምዱ ከተደረገ በኋላ ለሁለቱም ምድቦች ተመሳሳይ የድህረ ልምምድ ፈተና ቀርቦላቸው ውጤቱ በቲ-ቴስት ተሰልቶ በ0.05 የጉልህነት ደረጃ፣ በ91 የነፃነት ደረጃ የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ 4.16 ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.6645 የበለጠ በመሆኑ በላይታች የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል የተማሩ ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ስለሆነ የተመታው መላምት በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ከፍ በማድረግ በላይታች ሞዴል ማንበብን ከማስተማር በታችላይ ሞዴል ማንበብን ማስተማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል የሚለው ባዶ መላምታ ውድቅ ሆነ፡፡ በአንፃሩም በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ከፍ ለማድረግ በታችላይ ሞዴል ማንበብን ከማስተማር በላይታች ሞዴል ማንበብን ማስተማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል የሚለው ተቀባይነትን አግኝቷል፡፡ ከዚህ ጋርም በማያያዝ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘትም የጽሑፍ መጠይቅ ተሰራጭቶ የተገኘውም መረጃ ይሁን ከምልከታ የተገኘው መረጃ ተማሪዎችን አሳታፊ ያደረገውና ተወዳጅና ወደፊትም ውጤታማ የሚያደርጋቸው ሞዴል የላይታች ሞዴል እንደሆነ ከመረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ከዚህ በኋላ የማንበብ ትምህርቱን በላይታች ሞዴል ማስተማሪያነት ተማሪዎች ቢማሩ ጥሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንደሚያበረክት ነው፡፡ በጥናቱ ወቅትም የማንበብ ትምህርቱ ውጤታማ እንዳይሆን ለሚያደርጉ ችግሮችም የመፍትሔ ሐሳብ ለምሳሌ፡ የማንበብ ትምህርቱን ተማሪዎች በላይታች የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል ቢማሩ፣ ማንበብን ተማሪዎች በግላቸው እያነበቡ እንዲማሩ ቢደረግ፣ ከመጽሐፋቸው ውጪ የተለየዩ ጽሑፎችን እንዲያነቡና በሃሳቡ ላይ እንዲወያዩ ሁኔታዎች ቢመቻችላቸው፣ የሚሉ እና ሌሎች የመፍትሔ ሃሳቦች በማጠቃለያው ላይ ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# 1. መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ተማሪዎች የቋንቋ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ እና በማህበራዊ ኑሮአቸውን ጥሩ የተግባቦት ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡ ከእነዚህም ክሂሎች አንዱ የማንበብ ክሂል ነው፡፡ የማንበብ ተግባር ወደ ሰው ልጅ ተግባርነት የተቀላቀው ከማድመጥና ከመናገር ክሂል በኋላ መሆኑን የተለያዩ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ የሰው ልጅ በወካይ ፊደላት በማንበብ በጽሑፍ መጠቀም ከመጀመሩ በፊት በንግግር እየተገለገለ የቆየ መሆኑ ይታወቃል፡፡ እስከ ቅርብ ዘመን ድረስ አብዛኛው የዓለም ህዝብ ማንበብና መፃፍ እንደማይችሉ በተለያዩ ምሁራን ይገለፃል፡፡ ነገር ግን ከቅርብ ዘመን ወዲህ የሰው ልጆች ከመሃይምነት እንዲላቀቁና በእያንዳንዱ የትምህርት አይነቶች የሚቀርቡ እውቀቶችን አንብበው እንዲረዱ ለማድረግ የማንበብ ክሂል ትምህርት ትኩረት ተሰጥቶት ተማሪዎች እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ ይህንንም የማንበብ ክሂልን በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን እንደየ ትኩረት አቅጣጫቸው የተለያዩ ብያኔዎች መስጠቱን በምሳሌነት የሚከተሉትን ለማየት እንሞክራለን፡፡

Davis (1995:1) ማንበብ ግላዊ የአእምሮአዊ ግንዛቤ ሂደት ነው፡፡ አንባቢው ፀሐፊው በጽሑፉ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት አንብቦ ለመረዳት የሚተጋበት ነው፡፡ ይህም ማለት ማንበብ አንባቢው በግሉ ተነሳስቶ የሚተገብረው እንጅ በሌሎች ሲነበቡ የሚያደምጠው ወይም ሌሎች እንዲረዱት ጮክ ብሎ የሚያነበው ተግባር መሆን እንደሌለበት ነው፡፡

Nuttal (1982:3) ማንበብ ተማሪዎችን በሚያነቡበት ወቅት ክሂሉን ማዳበር ብቻ ሳይሆን የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበርም የሚረዳ ክሂል ነው፡፡ ከዚህ አገላለጽ የምንረዳው አንድን ጽሑፍ በምናነብበት ወቅት የማንበብ ክሂላችንን ከማዳበር በተጨማሪ ቋንቋ ችሎታችንም ከፍ እንደሚል ነው፡፡

ግሩም ጥበቡ (2003፣ 1) Grabe and Stoller (2002: 9)ን በመጥቀስ ማንበብ በጽሑፍ ከቀረበ ምንባብ ፍቺን ማውጣትና ፍቺን በተገቢው መልኩ መተርጎም የሚያስችል ክሂል ነው፡፡ ማለታቸውን ገልፀዋል፡፡ ይህ አገላለጽ የሚያስረዳን ማንበብ ከሚነበበው ጽሑፍ ፍቺን ማውጣት ብቻ ሳይሆን ፍቺውን በአንድምታ መተርጎምን የሚጠይቅ ውስብስብ ተግባር መሆኑን ነው፡፡

እንግዳ ዘውዴ (1992፣ 20) Higgins (1984) እና Goodman (1970) ዋቢ አድርጎ "ማንበብ ዓላማ መወሰንን፣ የምንባቡን መልዕክት አስቀድሞ መገመትን፣ የተገመተውን ግምት ማጥራትንና የምንባቡን መልዕክት ከግል ገጠመኝ ጋር አዛምዶ ተቀባይነቱንና ተጨባጭነቱን መገምገምን የሚያጠቃልል ተግባር ነው" ማለታቸውን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ የምንረደው ምንባቡን ከማንባባችን በፊት ዓላማ መንድፍና የምንባቡን መልዕክት ምን ሊሆን እንደሚችል መገመትን የሚጠይቅ፣ በምናነብበት ጊዜ ደግሞ የግምታችንን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካነበብን በኋላ የምንባቡን ሃሳብ ከራሳችን ገጠመኝ ጋረ አያይዘን መገምግምንና ማረምን የሚጠይቅ ክሂል መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ ማንበብ በጽሑፍ የቀረበን መልዕክት ትክክለኛ መንፈሱንና ሃሳቡን እያስተዋሉና እየገመገሙ ተጨባጭ የሆኑ ረቂቅ ፅንሰ ሃሳቦችን መቅሰም፣ ከራስ ገጠመኝ ጋር ማዋሀድ፣ መተርጎም፣ አዳዲስ ሃሳቦችን ማፍለቅ፣ በሚነበበው ጽሑፍ የጎደለውን መሙላትን፣ የተዛባውን ማቅናትን፣ የጠበበውን ማስፋትን፣ ወዘተ እና የግል አስተያየትን ጨምሮ የደራሲውን ሃሳብ በትክክል ማንፀባረቅን የሚጠይቅ ውስብስብ ተግባራት ያሉበት ክሂል ነው፡፡ ከአገልግሎቱ አንፃር ሲታይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ቢሆንም የክሂሉ የትምህርት አሰጣጥ በየትምህርት ቤቱ ወጥ ያልሆነና በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ላይ ትኩረት እንደማይሰጠው ከዚህም የተነሳ በተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ክሂሉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ ለምሳሌ መዓዛ ደጀኔ (1999)፣ እንግደ ዘውዴ (1992)፣ ግሩም ጥበቡ (2003)፣ ይታያል ወርቁ (2203) በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት እንዳጠና ያነሳሳኝ ከዚህ በፊት በመማር ማስተማር ላይ በቆየሁበት ወቅት የማንበብ ትምህርት አሰጣጥ ችግሮች መኖሩን አይቻለሁ፡፡ የማንበብ ትምህርትን እኔ በሠራሁበት ትምህርት ቤቶች መምህራን የሚያስተምሩት በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ብቻ ተመርኩዘው ሲሆን እነዚያንም ምንባቦች አንዴ በመምህሩ ከተነበቡ በኋላ የተሻለ የማንበብ ችሎታ ባላቸው ውስን ተማሪዎች ከፍ ባል ድምጽ ይነበባሉ፡፡ ሌሎቹ ተማሪዎች በማንበብ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አንባቢ ሳይሆኑ አድማጮች ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ ሂደቱ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት የማያነሳሳ የማንበብ ክሂል እንዳይዳብሩ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ይህም ሁኔታ በአጥኚዋ አእምሮ ጥያቄ እየጫረ ያለ በመሆኑ ጥያቄውን ለመመለስ የማንበብ ትምህርት

በየትኛው የማንበብ ትምህርት ሞዴል ቢሰጥ የተሻለ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል። ሞዴሎችን በማነፃፀር እንዳጠና ያነሳሳኝ ከዚህ በፊት እንግዳ (1992) የማንበብ ትምህርት ላይ ታች ሞዴል ቢሰጥ የተሻለ ውጤት እንደማያስገኝ በፍትነታዊ ምርምር አጥንቶ ያረጋገ ሲሆን፣ በተቃራኒው ደግሞ ግሩም (2003) የማንበብ ትምህርት በ"ታች ላይ" ሞዴል ቢሰጥ ይሻላል ብለው ምክንያቶቻቸውን አስቀምጠዋል።

ሁለቱም የተለያዩ ሞዴሎችን ፈትሸው ውጤታማነታቸውን ቢገልጹም አሁን ባለንበት ወቅትም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን ቀደም ሲል እንደገለጽኩ ከዚህ በኋላ ባለው ተማሪዎች ከሁለቱ በየትኛው የማንበብ ትምህርት ቢቀርብላቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ከፍ እንደሚያደርግ በጥናት ለመፈተሽ ነው።

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ "የላይ ታች" እና የ"የታች ላይ" የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ ለመረዳት ክሂል ያላቸውን አሰተዋጽኦ በማነፃፀር ከሁለቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክተውን ሞዴል መለየት ነው።

ይህንንም መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይቻላል።

1. ከሁለቱ ሞዴሎች በአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክተውን በመተፈሽ ማረጋገጥ።
2. ተማሪዎች ከሁለቱ ሞዴሎች ልምምድ በኋላ በየትኛው ሞዴል የተለማመዱ ተማሪዎች የበለጠ የልምምዱን ሞዴል አቀራረብ እንደወደዱ መለየት።
3. ከልምምዱ በፊት መምህራን የማንበብ ትምህርቱን በምን መልኩ እንደሚያስተምሩ ማረጋገጥ።

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሞች ይሰጣል ተብሎ ይገመታል፦

1. በጥናቱ ዓላማ የተነሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ ያስችላል።
2. ለተማሪዎች የማንበብ ክሂላቸውን በተሻለ መልኩ ለማዳበር የሚያስችላቸውን ሞዴል አነፃፅሮ ለማቅረብ።

3. በመማር ማስተማሩ ሂደት ተሳታፊ ለሆኑ መምህራን ስለማንበብ ትምህርት አቀራረብ የተሻለ ግንዛቤ አግኝተው የተማሪዎቻቸውን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዲጨምሩ ያስችላል፡፡
4. ለመርሃ ትምህርት እና ለመጽሐፍ አዘጋጆች እንደመነሻነት የሚያገለግል የጥቆማ ሃሳብ ይሰጣል ተብሎ ይገመታል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በጋሞ ጎፋ ዞን በደብረፀሐይ ወረዳ በበቶ ከተማ በሚገኘው በቶ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በእጣ ናሙና በተመረጡ በ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ የተከናወነ ነው፡፡ ጥናቱ ከ"ላይታች" እና ከ "ታችላይ" የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል የትኛው እንደሚሻል በሙከራ ለማረጋገጥ የሞዴሎችን የትምህርት አቀራረብ መመሪያ በክፍል ውስጥ ተግባሪዊ እንዲያደርጉ መጠቆምና መፈተሽ ነው፡፡ ስለዚህ በነዚህ የአቀራረብ መመሪያዎች ትምህርቱ ሲቀርብ የተሻለውን ሞዴል መፈተሽ ላይ የተወነ እንጅ ሌሎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች ለምሳሌ፡- የመረጃ መሳሪያ አመጠቃቀም፣ የመምህራን የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ ወዘተ.. ላይ አያተኩርም፡፡

## 1.6 መላምት

በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ከ"ላይታች" የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል የ "ታችላይ" የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

## 2.1 የማንበብ ክሂል ምንነት

ማንበብ የምንባቡን መልዕክት ከመረዳትም አልፎ ምንባቡ በማን? የት? ለምን ዓላማ? እንደተፃፈ መመርመርንና በመገንዘብ መልዕክቱን ቃል በቃል ከመቀበል አመዛዝኖ መረዳትን ያመለክታል፡፡ ይህንንም በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡ Williams (1984:3) "ማንበብ ተፈላጊውን መረጃ የማግኘትና የመረዳት ሂደት ነው፡፡" የመረዳቱ ሁኔታ ከሚነበቡት ዓላማ የማንበቢያ ስልት የተለያዩ ሊሆን ይችላል፡፡ Grellet (1981:3) በተመሳሳይ መልኩ የአነባብ ስልትን መለያየት ሲያስቀምጡ "ከማስታወቂያ ፍሬ ሃሳቡን በገረፍታ የሚነበብ ሲሆን ሳይንሳዊ ምርምር ግን በጥልቀት ማንበብን ይጠይቃል" ከዚህም የምንረዳው የአነባብ ስልታችን እንደየዓላማችን የተለያየ ሊሆን እንደሚችል ነው፡፡

Wallace (1992:4) ማንበብ አንባቢው ከጸሐፊው ጋር ግንኙነት ለመፍጠርና የጸሐፊውን ሃሳብ ለመረዳትና ለመተርጎም በግሉ የሚያደርገው ጥረት ነው፡፡ ከዚህም ሃሳብ የምንረዳው ማንበብ አንባቢውን ከፀሐፊው ጋር ለማገናኘት እንደ ድልድይ የሚያገለግል መሳሪያ መሆኑን በመሳሪያነቱም አንባቢው ተጠቅሞ ጸሐፊው ማለት የፈለገውን ሃሳብ በራሱ አገላለጽ መተርጎም እስከመቻል የሚያደርስ መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ምሁራንም ሆኑ ሌሎች በምዕራፍ አንድ በጥናቱ ዳራ የተጠቀሱ ስለማንበብ ከሚያስቀምጡት ብያኔ የምንረዳው ማንበብ የሚነበበውን ነገር መምረጥን፣ ማስተዋልን፣ መመርመን በጽሑፍ የሰፈረን መልዕክት ትክክለኛ መንፈሱን እያስተዋሉና እየገመገሙ ተጨባጭ የሆኑ ጽንሰ ሃሳቦችን መቅስም ከራስ ገጠመኝ ጋር ማዋሃድን የሚጠይቅ ክሂል መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

## 2.2 የማንበብ ትምህርት ዓላማ

የማንበብ ትምህርት የሚሰጥበት ዋና ዓላማ የማንበብ ክሂልን ለማዳበር ነው፡፡ ከተጨማሪም ብዙ ዝርዝር ጥቅሞች አሉት፡፡ ማንበብ ከማንኛውም የሰው ልጅ ህይወት ጋር ግንኙነት ያለው ተግባር ስለሆነ፣ ተማሪዎች በማንኛውም ስፍራ አዳዲስ ሃሳብን በማፍለቅ እንደልብ ሃሳባቸውን ከተለያየ አቅጣጫ በማየት አሳማኝና አስተማሪ በሆነ መንገድ እንዲገልጹ ያደርጋቸዋል፤ በማህበራዊ ኑሮአቸው ለሚያጋጥሙአቸው ችግሮች በቀላሉ መፍትሄ እንዲሰጡ እገዛ

ያደርጋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ ለምን ዓላማ፣ በየትኛው የአነባብ ስልት መነበብ እንዳለበት ከምንባቡ ምን ሊያገኙ እንደሚችሉ ከማንባባቸው አስቀድመው ተንብየው እንዲያነቡ ማድረጉ የአንብቦ መረዳቱን ተግባር የተቀላጠፈ ያደርገዋል፡፡ አስቀድመው እንዲተነበዩ ማድረጉ የተማሪዎችን ተሳትፎም ይጨምራል፡፡

አንድ አንባቢ ከማንበቡ በፊት ሊያስቀምጠው የሚገባው ምንባቡን ለምን እንደሚያነበው ማወቁ ሊዘነጋ አይገባም፡፡ የሚያነብበትን ዓላማ ካወቀ ዓላማውን ከግብ ለማድረስና አንብቦ ለመረዳት በየትኛው የአነባብ ስልት ማንበብ እንዳለበት ለማወቅ ዓላማ መንደፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ስለማንበብ ዓላማ አስመልክቶ Nuttal (1982:21) ተማሪዎችን ዓላማ ነድፈው እንዲያነቡ በማድረግ ማስተማር ተማሪዎች የሚፈልጉትን መረጃ በፍጥነት አንብበው እንዲረዱና አዳዲስና ግራ የሚያጋቡ ሃሳቦች ቢያጋጥሙ እንኳ በትኩረት አንብበው ሃሳቡን እንዲረዱ ያስችላቸዋል፡፡ ከዚህ አገላለጽ እንደምንረዳው በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩ ተማሪዎች ዓላማ ነድፈው እንዲያነቡ ማድረግ እንዳለባቸውና ተማሪው ዓላማውን ከነደፈ እንዴት ማንበብ እንዳለበት የአነባብ ስልቱን ለማወቅ አይቸገርም፡፡ የአነባብ ስልቱን ካወቀ ደግሞ የጽሑፉን ሃሳብ በፍጥነት አንብቦ ለመረዳት እንደሚያስችል ነው፡፡

የማንበብ ትምህርት በዋነኛነት የማንበብን ክሂል የሚያዳብር ሲሆን ዘርዘር ያሉ ዓላማዎችም እንዳሉ Wallace (1992, 6) እንደሚከተለው ጠቅሷል፡፡

### ሀ. ማንበብ ለመጠንቀቅ

ማንበብ ያልንበትን አካባቢ ሁኔታ ለመረዳት ያስችላል፡፡ የተለያዩ በጽሑፍ የሚቀርቡ የማስጠንቀቂያ መመሪያዎችን አንብበን ተግባራዊ እንድናደርግ ያግዛል፡፡ ወይም ለአደጋ እንድንጋለጥ አያደርገንም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ከማንኛውም አደጋ ለመጠንቀቅና የአካባቢያቸውን ሁኔታ ለይተው እንዲያውቁ ለማድረግ የማንበብ ክሂል የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

### ለ. ማንበብ ለመደስትና ለመዝናናት

ማንበብ የማንበብ ክሂሉን ከማዳበር በተጨማሪ አእምሮን የማዝናናትና የማስደሰት አቅም አለው፡፡ ተማሪዎችን ለዚህ ዓላማ ብሉ እንዲያነቡ ማድረግ የማንበብ ፍላጎታቸውን ይጨምራል፡፡ ለዚህ ዓላማ ብለው የተለያዩ ጽሑፎችን በአፍ መፍቻቸውም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋቸው በሚያነቡበት ወቅት የቋንቋ ችሎታቸውንም ያዳብራሉ፡፡

### ሐ. ማንበብ አዳዲስ ነገርን ለማወቅ

በማንበብ ስለአካባቢያችንና ስለዓላማችን የቀረቡ አዳዲስና ወቅታዊ እውቀትን እንድናውቅና እንድንጨብጥ ትልቅ እገዛ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም አዳዲስ የሆኑ የትምህርት ይዘቶችን ለመረዳት ያስችላል፡፡

ከላይ በ Wallace ከቀረበው ሃሳብ የምንረዳው የማንበብ ትምህርት ራስን ከአደጋ ለመከላከልና አስፈላጊ የሆኑ አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ መረጃዎችን ለማግኘት ዓላማ ተብሎ የማንበብ ትምህርት መስጠት እንዳለበትና ተማሪዎችም ለነዚህ ዓላማዎች ብለው ማንበብ እንደሚችሉ ነው፡፡ በተጨማሪም USAID/ Ethiopia (2003: iv) ማንበብ በትምህርት ቤት ለሚገኝ ስኬት ብቻ ሳይሆን በህይወት ዘመን እውቀትና ደስታም ጭምር መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ይህም ማለት በማንበብ የምናገኘው እውቀት በትምህርት ቤት ከፍተኛ ውጤት ለማምጣት ብቻ ሳይሆን በህይወታችን ዘለቄታ ያለው ጠቀሜታ እንደሚሰጠን ነው፡፡

## 2.3 የማንበብ ትምህርት የአቀራረብ ደረጃዎች

የማንበበብ ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ ትምህርቱ አሰልቺ እንዳይሆን በተለያዩ ደረጃዎች እየተከፋፈሉ ሊቀርቡ እንደሚገባ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ትምህርቱ የማያስለች ከሆነ ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት እንዲያነቡ ያነሳሳቸዋል፡፡ ስለአቀራረቡም ደረጃዎች በተለያዩ የመስኩ ባለሙያዎች የተሰጡ ብያኔዎችና አስተያየቶችን እንደሚከተለው እናያለን፡፡

ግሩም (2003፡17) Karkas (2002) ጠቅሶ እነዚህ የማንበብ ደረጃዎች በማንበብ ትምህርት ወቅት የሚፈጠርን መሰናክል እንዲቀንሱና በሶስት ደረጃዎችም እንደሚከፋፍሉ ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ USAID /Ethiopia (2003 ፡14) ደረጃዎች ከማንበብ በፊት፣ በማንበብ ጊዜና ከማንበብ በኂላ ሲሆኑ በነዚህ ጊዜት መምህሩና ተማሪው በማሰብ በመገመት፣ በማረጋገጥና በመፍጠር የነቃ ተሳትፎ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ትምህርቱ በነዚህ ተከፋፍሎ መቀረቡ በሙሉ ወይም ወደ ሙሉ የተቃረበ ስኬታማ የመማር ውጤቶች ያመራል፡፡ ይህም ማለት ትምህርቱ በደረጃዎች ተከፋፍሎ ቢቀርብ ተማሪው የቱ ደረጃ ላይ ግር እንዳለው መምህሩ ለይቶ ተማሪውን በመርዳት ውጤታማ እንዲሆን እንደሚያደርገው ነው፡፡

### 2.3.1 ቅድመ ማንበብ

ይህ የማንበብ ትምህርት ደረጃ አንባቢዎች ፅሁፉን በማንበብ ከመጀመራቸው በፊት የጽሁፉን ርዕስ ለማስተዋወቅ፣ የማንበብ ፍላጎታቸውን ለመቀስቀስ ፅሁፉን ለምን እንደሚያነቡ

ለመግለጽና የፅሁፉን ሀሳብ ለመረዳት እነቅፋት ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ ሀሳችን በማንሳት አስቀድሞ የቋንቋ ዝግጅት ለማድረግ ይጠቅማል፡፡ Williams (1984) የቅድመ ማንበብ ጊዜ ለተማሪዎች ርዕሱን ለማስተዋወቅና የማንበብ ፍላጎትን ለማነሳሳት፤ የሚያነቡበትን ምክንያት በማሳወቅ አንባቢዎችን ለማነቃቃት፣ ለማንበብ ዝግጁ ለማድረግ ያገለግላል፡፡ በዚህም ጊዜ አንባቢዎች ምን? ለምን? ለማን? እንዴት? ለየትኛው የማንበብ ስልት ማንበብ እንዳለባቸው ይወስናሉ፡፡

ግሩም (2003:17) Karkes (2002) ዋቢ አድርጎ በዚህ ጊዜ ስለ ትምህርት ርዕስ አጠቃላይ ነጥብ ማንሳትና ስለምንባቡ መላምቶችን አቅርቦ መገመት ያስፈልጋል፡፡ ይህም መደረጉ ለተማሪዎች እንዲያነቡ ከማዘዛቸው በፊት በፍላጎታቸው እንዲያነቡ የማያደርጉ ጥያቄዎችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

መዓዛ (2003) ድህረ ገጽን ዋቢ አድርገው በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል መገመት፣ ለቁልፍ ቃላት ፍቺ መስጠት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡ ይህን ሀሳብ ማጠናከር በድሉ (1996) በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በርዕሱ ዙሪያ በቂ ዳራዊ ዕውቀት ከሌላቸው መምህሩ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ፍንጭ የሚሰጥበት፣ አዳዲስ ቃላትን አቅርቦ ፍቺውን እንዲገምቱ የሚያደርጉበት፣ መሪ ጥያቄዎችን የሚጠይቅበት፣ የማንበብ እንቅፋቶችን ለማስወገድ የሚጥሩበት ደረጃ ነው፡፡ ተማሪዎችም የምንባቡን ርዕስ በመመልከት ያላቸውን የቀደመ እውቀት ከምንባቡ ርዕስ ጋር አዛምደው ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን ሀሳብ የሚተነብዩበት፣ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ የሚገምቱበት፣ ከርዕሱ ጋር የሚተዋወቁበት ጊዜ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

USAID/ Ethiopia (2003:14) በዚህ ጊዜ መምራን የተማሪዎችን የቅደመ ንባብ ዕውቀትን ማነሳሳት፣ የማንበብ ፍላጎትን መቀስቀስ፣ የተማሪዎችን ቅድመ ዕውቀትን መገምገም፣ የአነባብ ስልቶችን በመጠቀም ማሳየት፣ ምንባቡን ከተማሪዎች ህይወት ጋር የተያያዙ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 2.3.2 በማንበብ ጊዜ

በዚህ ደረጃ ቀደም ሲል በቅድመ ማንበብ ደረጃ ለተነበዩት ትንበያ እና የቃላት ግምታዊ ፍቺ የሰጡበትን ለማረጋገጥ የሚያነቡበት ጊዜ ሲሆን እነዚህን ጉዳዮች በፍጥነት አንብቦ ለመረዳት መዓዛ (2003) ድህረ ገጽ ዋቢ አድርገው እንደጠቀሱት ምንባቡ በአሰሳ እና በገረፍታ የአነባብ

ስልት እንደሚነበብና የበለጠ መረጃን ለማግኘት በዝምታ የሚነበብበት ጊዜ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በዚህም ጊዜ ተማሪዎቹ የጽሁፉን አደረጃጀት የሚለዩበት የቃላትን ፍቺ ከአውዱ የሚረዱበት፣ ዝርዝር መረጃዎችን የሚያወጡበት ጊዜ ነው፡፡ በማለት ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Meiryun (1995:127) በዚህ ጊዜ ተማሪዎችን ርዕሱን ማስታወስ፣ ስዕሎችን፣ ሰንጠረዦችን ግራፎችን፣ ወዘተ ማሳየትና ተፈላጊውን መረጃ በዳሰሳና በገረፍታ እንዲያነቡ የሚያደርግበት ደረጃ ነው፡፡ ቀደም ሲል የተነበዩትን ትንበያ ተፈላጊውን መረጃ ለማረጋገጥ ወይም ለመተው ግርፍ ንባብ የሚካሄድበት፣ እንደገና የሚነበቡበትና ተማሪው ትንበያ ወይም የመረጃመሪያውን የሚከልስበት ነው፡፡

Williams (1994) የንባብ ጊዜ ዓለማው አንባቢዎች የፀሐፊውን አላማ መገንዘብና የፅሁፉን ይዘትና አወቃቀር መረዳት ነው፡፡ የሚናነበው ለጥናትና ምርምር ከሆነ ተፈላጊውን መረጃ ከጽሁፉ ለማሰባሰብ ዝርዝር ወይም ተፈላጊ መረጃዎችን በመረዳት ላይ ስለሚመሰረት በጥንቃቄ ጥልቅ የንባብ ስልትን መጠቀምን የሚጠይቅ የማንበብ ደረጃ ነው፡፡ የምናነበው ለማስታወስ ከሆነ ግን አስፈላጊ መረጃዎችን በአሰሳ በፍጥነት የሚነበብበት ነው፡፡ ከዚህም አገላለጽ የምንረዳው ይህ ደረጃ ትኩረት የሚያደርገው ከላይ በቅድመ ንባብ በትንበያና በግምት የቀረቡ ሀሳቦችን ለማረጋገጥ በቀረበው ጽሁፍ ላይ ትኩረት በማድረግ እንደየ አላማችን የተለያዩ የአነባብ ስልቶችን ተጠቅመን መረጃዎችን የምንሰበስብበት ደረጃ መሆኑን ነው፡፡

USAID/ Ethiopia (2003:16) በዚህ ደረጃ መምህራን ተማሪዎቻቸውን አዳዲስ ዕወቀትን እንዲያገኙ የሚያደርጓቸው፣ አዲሱን ዕወቀት እንዴት እንደተረዱት የሚገመግሟቸው፤ በላይኛው የማንበብ ደረጃ የተነበዩት ትንበያ ሀሳብ አሁን ሲያነቡ ከሚያገኙት ሀሳብ ጋር አለመግባባት ካለ አለመግባባቱን የሚያብራሩበትና ችግሩን ለይተው እንዲያውቁ የሚያደርጋቸው ሂደት ነው፡፡ ለተማሪዎች ዝርዝር ጉዳዮችን ለመፈለግ ወይም የአስቸጋሪ ቃላትን ትርጉም አፈላለግንና ከዋናው ቁምነገር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ሲፈልጉ በየትኛው ስልት መጠቀም እንዳለባቸው የሚገልጹበት ነው፤ ተማሪዎቹም በምን አይነት ዘዴ እንደተጠቀሙ የሚጠይቁበት ደረጃ ነው፡፡

ግሩም (2003፡19) Karakas (2003:16) በዚህ ደረጃ አንብቢው እንዲረዱ መምህራን አስቀድመው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከጓደኞቻቸው ጋር የእርስ በርስ መማማርና መገማገም እንዲኖራቸው ስለ ጽሁፉ አስተያየት የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ሊጠይቁ ይገባል፡፡ በዚህም ጊዜ በጸሐፊውና በአንባቢዎቹ መካከል ያለው መስተጋብር እንዲፋጠን የቋንቋ መምህራን የዳሰሳ፣

የገረፍታና የገለጻ ስልትን ተግባሮችን ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ ይህን ማድረግም የጽሁፉ መልዕክት በአንባቢዎቹ አዕምሮ ምስልን እንዲፈጥር ያደርጋል፡፡

### 2.3.3 የድህረ ማንበብ ደረጃ

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ከላይ በቀረቡት ደረጃዎች ያገኙትን ትምህርት የሚያጠናክሩበትና የሚያረጋግጡበት ነው፡፡ ያገኙትን አዳዲስ ዕወቀት ከግል ገጠመኞቻቸው ጋር ለማጣጣም በመልመጃዎች አማካኝነት የሚመቻችበት ደረጃ ነው፡፡

Williams (1984:1) የድህረ ንባብ ዓላማው የተነበበውን ጽሁፍ ሀሳብ ማንፀባረቅ፤ የጽሁፉን ሀሳብ ከራስ ገጠመኝ ፍላጎት ጋር በማያያዝ የራስን ዕወቀት መጨበጥ ነው፡፡ እነዚህንም ዓላማዎች ለማሳካት በዚህ ወቅት አንባቢዎች የተረዱትን ሀሳብ ከራስ የህወት ልምድ ጋር አያይዘው በራሳቸው አገላለጽ የሚተነትኑበትና የሚያንፀባርቁበትን የሚጋብዙ ክንውኖች ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

ግሩም (2003፡20) Karakas (2002) ዋቢ አድርጎ አንባቢዎች ምንባቡን አንብበው የተረዱትን ነገር ለማረጋገጥ መከለስ፣ መጠየቅና መመለስ፣ ማጠቃለያ መስጠት ተግባራትን ሲፈጽሙ በቀረበላቸው ጥያቄና መልሶቻቸው መካከል ያለውን ዝምድና ይፈትሻሉ፡፡ ቀደም ሲል በማንበብ ጊዜ ስሜት ያልሰጣቸውን ሀሳብ ተግባራትን ከጓደኞቻቸው ጋር በመወያየት፣ ምንባቡን እንደገና በመከለስ በሚያነቡበት ወቅት ሀሳቡ በአዕምሮአቸው ውስጥ ምስልን እንዲፈጥር ያደርጋል፡፡

USAID/ Ethiopia ይህ ደረጃ ተማሪዎች ያነበቡበትንና የተረዱትን ዕውቀት ተግባራዊ የሚያደርጉበት ደረጃ ነው፡፡ ይህን ተግባራዊ እንዲያደርጉም መምህራን በራሳቸው እንደተማመኑና ፍላጎታቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያደርጉ መልመጃዎችን ማቅረብ አለባቸው፡፡ ጥያቄያዎችም አዲስ ዕውቀት ላይ የሚያንፀባርቁ፣ የምንባቡን ሀሳብ እንደገመገሙ የሚያደርጉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ተማሪዎችም አንብበው ተረድተዋል ማለት የሚቻለው እነዚህን የቀረቡ ጥያቄዎችን ሠርተው ውጤታማ ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ እንደተመለከትነው በመስኩ ባለሙያዎች የተጠቀሱት ማብራሪያዎች የሚገልፁ በነዚህ ሶስት ደረጃዎች ተጠቅሞ የማንበብ ትምህርትን ማስተማር ተማሪዎችን ለማንበብና የማንበብ ክሂላቸውን ለማዳበር የሚያበረታቱና ለመማር ዕድል የሚሰጡ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ በነዚህ ሁኔታ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው እንዲዳብሩ የሚያስፈልጋቸውን የአነባብ ስልቶችን እንዲለማመዱ ያደርጋል፡፡ ለልምምዱ

እንዲያመችም ተማሪዎች በቅድመ ንባብ ጊዜ ርዕሱን በማየት ቀጥሎ በጽሁፉ ውስጥ ሊያገኙ የሚችሉትን ነገር ይተነብያሉ፣ ዓላማ ይነድፋሉ ዓላማቸውም የአነባብ ስልታቸውን እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፡፡ በማንበብ ጊዜ ደግሞ የተነበዩትንና የገመቱትን ግምት ለማረጋገጥ በዓላማቸው መሠረት በተወሰነው የአነባብ ስልት አንብበው እስከሚረዱ ያነባሉ፡፡ በድህረ ማንበብ ጊዜ ደግሞ ከምንባቡ ያገኙት ዕወቀት ካላቸው ዕውቀት ጋር አዛምደው እያንዳንዱ ደረጃ አንብቦ መረዳትን በተግባር የሚገልጹበት ነው፡፡

እነዚህ ደረጃዎች ለመምህሩ የራሱ የሆነ መረጃ ይሰጣሉ፡፡ በቅድመ ማንበብ ጊዜ መምህሩ የተለያዩ የቅድመ ዕውቀት መቀስቀሻ ጥያቄዎችን በማቅረብ የተማሪዎችን ችግር ለይቶ ያውቃሉ፡፡ ለችግሩም መፍትሔ እንዲፈለግ ፍንጭ ይሰጣል፡፡ በማንበብ ጊዜ ደግሞ መምህሩ በሰጡት ምሳሌ መሠረት ተማሪዎች ማንበብ መቻላቸውን ለማገምገም ያስችላቸዋል፡፡ በድህረ ማንበብ ጊዜ ከማንበብ በኋላ በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ላይ ውጤታማ የሚሆኑ ከሆነ የመምህሩ የማንበብ ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ አስተማማኝ መሆኑን ራሱንም መምህሩ እንዲገመግም ያደርገዋል፡፡

## 2.4 የማንበብ ትምህርት የመልመጃ ጥያቄዎች ዓይነት

የማንበብ ልምድን ለማዳበር፣ ተማሪዎች ካነበቡት ጽሁፍ አጠቃላይ መልዕክት፣ የምንባቡ አወቃቀር ምን እንደሚመስል፣ በምንባቡ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተገለጹ እውነታዎችን መገንዘብ አለመገንዘባቸውን ለማረጋገጥና የተማሪዎችን ችግር ለይቶ ለመደገፍ የመልመጃ ጥያቄዎች የሚሰጡት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

ስለመልመጃዎች በተመለከተ Grellet (1981:5) የምንባቡን አወቃቀር ተማሪዎች አንብበው እንዲረዱ ለማድረግ ጥያቄዎቹ የምንባቡን አወቃቀር አስመልክተው ሊቀርቡ ይገባል ይዘቱን እንዲረዱ ለማድረግ ደግሞ በምንባቡ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተገለጹ ዘቶችን የሚጠይቅ ጥያቄ ሊቀርብ ይገባል፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ መልኩ Nuttal(1982:132) ላይ ተማሪዎች አንብበው መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉት ዓይነት ጥያቄዎች ሊቀርቡላችው ይገባል ይላሉ፡፡

1. ቀጥተኛ ጥያቄዎች፡- የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ከቀረበው ምንባብ ውጭ ያልሆነ መልስ የሚሰጥበት ወይም ለጥያቄዎቹ መልሱን በቀጥታ ከምንባቡ አግኝተው የሚመልሱት ዓይነት ጥያቄ ነው፡፡

2. ማገናዘብና ማቀናበርን የሚፈልጉ ጥያቄዎች፡- ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ተማሪዎች ከቀረበላቸው ምንባብ ያገኙትን ዕውቀት (ፍሬ ሀሳብ) ሳያዛንፉ ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እያገናዘቡ በራሳቸው አገላለጽ አቀናብረው እንዲገልጹ የሚያበዙ የጥያቄ ዓይነት ነው፡፡
3. አንድምታዊ ግንዛቤ የሚፈልጉ ጥያቄዎች፡- የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ተማሪዎች በምንባቡ የቀረበውን ሀሳብ በቀጥታ ሳሆን ከተለያዩ አአቅጣጫ በመመልከትና በመመራመር የሚመልሱት ዓይነት ጥያቄ ስለሆነ በትኩረትና በጥልቀት ማንበብን ይጠይቃል፡፡
4. የግምገማ ጥያቄዎች፡- ይህ የጥያቄ ዓይነት የምንባቡን ሀሳብና አጠቃላይ አወቃቀር፣ ይዘት፣ ወዘተ በተለያየ አቅጣጫ በማየት ገምግመው የራሳቸውን ሀሳብ እንዲሰጡ የሚጋብዙ ዓይነት ጥያቄ ነው፡፡
5. የግል አስተያየት የሚጠይቁ ጥያቄዎች፡- ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ስላነበቡት ምንባብ ይዘት ያላቸውን አመለካከት እንዲገልጹ የሚጋብዙ ናቸው፡፡

ከላይ በምሁራኑ የተሰነዘሩ ገለፃዎች ተማሪዎች አንብበው መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎች መሆናቸውን ነው፡፡ ተማሪዎችን ጥያቄዎችን መጠየቁም ሆነ ለጥያቄዎቹ መልስ በተረዱትና በቀጥታ ከማንበብ ያገኙትን እንዲገልጹ ማድረጉ ለማንበብ ይገፋፏቸዋል፡፡ በተለይ ተማሪው በራሱ አገላለጽ የተረዳውን ሀሳብ ከገጠመኙ ጋር እያገናዘበ እንዲመልስ የሚጋብዙ ጥያቄዎች የተማሪውን ተሳትፎ ለማሳደግ፣ ትምህርቱን በራሱ ፍላጎት እንዲማርና አንብቦ የመረዳት ችሎታውን ለማዳበር የሚሰጠው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.5 የአነባብ ስልቶች

የአነባብ ስልትን በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶች በተለያዩ ምሁራን እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ Grellet (1981:3) ከአንድ ጽሁፍ ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት የተለያዩ የአነባብ ስልቶችን ልንጠቀም እንደምንችል ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ ማስታወቂያ ለማንበብና ሳይንሳዊ ጥናቶችን ለማንበብ የምንጠቀመው የአነባብ ስልት የተለያየ ነው፡፡ ይህም የሚያስረዳው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዲዳብር ከተለያዩ የአነባብ ስልቶች ጋር ተማሪዎችን ማስተዋወቅ ተገቢ መሆኑን ነው፡፡ የአነባብ ስልቶች የሚባሉትን እንድሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 2.5.1 የዝርዝር ንባብ (Detailed reading)

ይህንን የአነባብ ስልት በተመለከተ Nuttal (1982:23) ከሚነበበው ምንባብ አጠቃላዩንና ዝርዝሩን ሀሳብ አንብቦ መረዳትንና መለየት የሚፈለግ ስለሆነ በጥንቃቄና በዝግታ ትኩረት

ሰጥቶ ማንበብን የሚጠይቅ የአነባብ ስልት ነው፡፡ የትኩረት ንባብ ዓላማው ዋናውን ሀሳብ በጥልቀት መገንዘብ ማስቻል ነው፡፡ ግንዛቤውን ማስጨበጡ ፍሬ ሀሳቡን መረዳት ላይ ብቻ ሳይሆን ፍሬ ሀሳብ እንዴት እንደተቀናበረ መረዳትም ጭምር የሚረዳ ስልት ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱም የማንበብ ስልት ተማሪዎች ጽሁፉን አንብበው ጠቅላላ ፍሬ ሃሳቡን በመገንዘብ የራሳቸውን አስተያየት ከግል ገጠመኛቸው ጋር አገናዝበው እንደረዱ ያግዛል፡፡

በአጠቃላይ ይህ የአነባብ ስልት ጥቃቅን ዝርዝር መረጃዎችንና አጠቃላ መረጃዎችን በትኩረት በመርመር መረጃዎችን ለመገንዘብ የሚደረግ የአነባብ ስልት ነው፡፡ ስልቱም ጥቅሙም እውነትን ከግል አስተያየት ለመለየት፣ ገጠመኝን ከሚነበበው ጽሁፍ ሀሳብ ጋር ለማነፃፀርና ገምግሞ የተጠራ መረጃን ለማግኘት፤ በዋናና በዝርዝር ሀሳብ መካከል ያለውን ዝምድና ለማየት፤ መመሪያን ተከትሎ ለመስራት፣ ወዘተ እንደሚያገለግል ነው፡፡ በትኩረት የንባብ ስልት በጽሁፉ ውስጥ የቀረቡ ሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና፣ ለዲስኮርስ ቃላት አጠቃቀም፣ ወዘተ ለእያንዳንዷ ነጥብ ትኩረት ሰጥተን ማንበብ አስፈላጊ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ከአገላለጹም እንደምንረዳው በዚህ የአነባብ ስልት ማንበብ በጽሁፍ ውስጥ ከሚገኙ ጥቃቅን ዲስኩር ቃላት አጠቃቀም አንስቶ እስከ ጸሐፊው አመለካከት ያለውን ለመረዳት የሚረዳ የአነባብ ስልት መሆኑን ነው፡፡

### 2.5.2 የአሰሳ ንባብ (Scanning)

የአሰሳ ንባብ ከጽሁፍ ውስጥ ተፈላጊው መረጃ ለማግኘት ተብሎ በፍጥነት የሚነበብ የአነባብ ስልት ነው፡፡ በዚህ ስልት በፍጥነት የሚነበቡ መረጃዎች ለምሳሌ (የአገር፣ የሰው፣ የነገሮች) ስም፣ አሀዛዊ መግለጫዎች፣ ዓመት ምህረት፣ ወዘተ ናቸው በዚህ ስልት ተማሪዎች እንዲያነቡ ለማድረግም በምሳሌው የተጠቀሱትን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ሊቀርቡ ይገባል፡፡ Nuttal (1982:34) ይህ የንባብ ስልት ትኩረታችንን ዝርዝር ጉዳዮና በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ ሳይሆን በሚንፈልገው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ብቻ አድርገን እንድናነብ የሚደርገን የአነባብ ስልት ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ እንግዳ (1992፡29) Hyland (1995:104) ዋቢ አድርጎ በዚህ የአነባብ ስልት ትኩረት መደረግ ያለበት በሚፈለግ ነጥብ ላይ ብቻ መሆን እንዳለበት ገልጸዋል፡፡ ስልቱ ተግባራዊ እንዲሆን ተማሪዎችን ከምንባቡ የሰዎችን ስም፣ ቀናት በምንባቡ የሚገኙበትን ስፍራ የሚጠይቁ ጥያቄዎችን ማቅረብ፣ በምንባቡ ውስጥ የሚኙ አያያዥ ቃላትን ሀረጋትንና አባባሎችን ለይተው እንዲያመለክቱ መጠየቅ፣ ተማሪዎች በዚህ ስልት እንዲያነቡ እንደሚያደርጋቸው ከምሁራኑ ሃሳብ መረዳት ተችሏል፡፡

### 2.5.3 የገረፍታ ንባብ (Skimming)

የገረፍታ ንባብ የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ማንበቡን እስከመጨረሻ በፍጥነት የሚነበብበት ስልት ነው፡፡ አጠቃላይ መልዕክቱን ለማግኘት ተማሪዎች ሲለማመዱ ከአሰሳ ንባብ ስልት ባነሰ ፍጥነት እንዲያነቡ በማድረግ ማለማመድ ተገቢ ይሆናል፡፡ በልምምዱ ወቅትም ፍሬ ሀሳቡን ሊያገኙ የሚችሉበትን የጊዜ ገደብ ወስኖ ማለማመድ አስፈላጊ እንደሆነ Nuttal (1982:34) ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ እንግዳ (1992፡28) Hyland ጠቅሶ የዚህ አነባብ ስልት ዋና ዓላማው ምንባቡን በፍጥነት በመቃኘት አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መገመት ነው፡፡ በተጨማሪም እንግዳ (1992፡28) Hyland (1995)፤ Aebersold and Kield 1997) ዋቢ በማድረግ እያንዳንዱ አንቀጹ የራሱ የሆነ ፍሬ ሀሳብ እንዳለው፣ የመግቢውና የመደምደሚው አንቀጽ የምንባቡን መልዕክት አሳጥረው በመያዝ ለአንባቢያን ዳራዊ ዕውቀት እንደሚሰጡ ተማሪዎች በልምምዳቸው ወቅት እነዚህን ከላይ የቀረቡ ጉዳዮችን ካወቁ በኋላ በጽሁፉ አጠቃላይ ሀሳብና በዝርዝር ሀሳቡ መካከል ያለውን ዝምድና እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች ለመግለጽ ጸሐፊው የተጠቀማቸውን የቃላት አጠቃቀም ተረድተው የተረዱትን ነገር ግልጽ በሆነ መልኩ ለማቅረብ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች የአነባብ ስልቱን ተጠቅመው ምንባቡን እንዲያነቡ ለማድረግ የመልመጃዎች አቀራረብ ወሳኝነት እንዳለው ከምሁራኑ አገላለፅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ተማሪዎች በዚህ የአነባብ ስልት እንዲያነቡ ለማድረግ እንግዳ (1992፡29) Nuttal (1996) እና Hyland (1995) ዋቢ አድርገው የሚከተሉትን ተግባራት እንዲሰሩ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

- በአንቀጾቹ ውስጥ የተዛቡ ዐ.ነገሮችን እንዲያቃኑ መጠየቅ
- በአንቀጾቹ የሃይለቃል መገኛ ስፍራንና የአንቀጹን ውስጣዊ ግጥምጥምያነት ለመረዳት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ተዘበራርቀው የተቀመጡ አንቀጾችን እንዲያቃኑ መጠየቅና ስለምንባቡ አወቃቀር ያላቸውን ግንዛቤ የሚገልጹትን ጥያቄ መጠየቅ
- በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በተለያዩ ጸሀፊዎች የተጻፉ ጽሁፎችን በማቅረብ የትኛው የተሸለ የመልዕክት አገላለጽ እንዳለው የሚጠይቁ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡

እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎችን መጠየቅ በገረፍታ ንባብ ስልት ተጠቅመው ተማሪዎች እንደልመዱ ማድረግ እንደሚቻል ያመለክታል፡፡

### 2.5.4 አመሳካሪ ንባብ (Intensive reading)

ስለ አውዳዊ ንባብ Grellet (1981) አውዳዊ ንባብ በጽሁፍ ውስጥ የቀረቡ የአዳዲስ ቃላትን ሀሳብ ተማሪዎች ለመረዳት ቃላቱን ከተለያየ አቅጣጫዎች አይተው ለመተርጎም የሚያስችላቸው የአነባብ ስልት ነው አቅጣጫዎችም ቃሉ ከአካባቢ ሁኔታ ጋር በማየት፣ ከባህል ጋር በመያያዝ፣ ከተለያዩ አስተሳሰቦች ጋር አያይዘው የሚመረምሩበት ሲሆን እነዚህም ርዕሰ ጉዳዮችን ማንሳት ለተማሪዎች ፍንጭ መስጠት ቃሉን የመረዳት ፍጥነታቸውን ይጨምራል።

እንግዳ (1992:30) Carrel, Liberto and Pharis (1989:660) Williams (1994:59) እና Chicalans (1993:931) ዋቢ አድርገው ይህን የአነባብ ስልት ለማለማመድ ሶስት ዓይነት ጥያቄዎች ሊቀርቡ እንደሚገባ እንደሚከተለው ተቀምጧል።

ሀ. ውስን መረጃ የሚጠይቁ አውዳዊ ጥያቄዎች:- የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ መልሱ ከምንባቡ በተለያዩ አንቀጾች በቀጥታ የሚገኝ ሆኖ ተማሪዎቹ እንደ አገነዛዘባቸው እንዲመልሱ የሚጋብዙ ጥያቄዎችን በማቅረብ ማለማመድ

ለ. ቀጥተኛ አውዳዊ ጥያቄዎች:- ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኋላ የምንባቡን መልዕክት መሠረት አድርገው መልዕክቱን አመዛዝነውና ገምግመው መልሶቻቸውን እንዲያቀርቡ የሚያደርጉ ጥያቄዎች

ሐ. ቀጥተኛ ያልሆነ አውዳዊ ጥያቄ:- ይህ የጥያቄ ዓይነት ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኋላ የማንበብን ሀሳብ ከቀዳሚ ዕውቀታቸው ጋርና ከተለያዩ ሁኔታዎችና አቅጣጫዎች ጋር በማያያዝ በምንባቡ በአሉታዊና በአዎንታዊ መልክ የቀረቡ ሀሳቦችን መርምረው በምክንያት አስደግፈው እንዲመልሱ የሚጠይቁ ጥያቄዎችን በማቅረብ ማለማመድ።

### 2.5.5 ሰፊ ንባብ (Extensive Reading)

ይህ የአነባብ ስልት እንደስሙ ሰፊ ጊዜን የሚጠይቅ ረጅም ልብወለድ፣ አጭር ልቦለድ እና ረጃጅም ጽሑፎችን ከክፍል ውጪ ማንበብን የሚጠይቅ ነው። ከዚህም አገላለፅ የምንረዳው ይህን የአነባብ ስልት ለማለማመድ መምህራን የተለያዩ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት እና መጠየቅ፣ ምንባቦችን መርጦ እንዲያነቡ ማድረግ እና ማንበባቸውን ለማረጋገጥ የምንባቡብ ሀሳብ በዘገባ መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ ለምሳሌ ስለ ፅሁፍ ጭብጥ፣ ስለ ደራሲው ማንነት ወዘተ መጠየቅ እና መከታተል ተገቢ ነው።

### 2.5.6 ሂሳዊ ንባብ (Critical Reading)

ይህን አነባብ ስልት በተመለከተ Meiryun (1995: 186) እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ የዚህ ንባብ ስልት አላማ ደራሲው ለማን? ምን? ለምን? እንደጻፈ ገምግሞ አስተያየት ለመስጠት የሚነበብ የአነባብ ስልት ነው፡፡ ልምምዱን ተግባራዊ ለማድረግ መምህራን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳይ የተጻፉ ጽሁፎችን በማቅረብ በጥልቀት አንብበው እንዲገመግሙ በማድረግ ማለማመድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በአጠቃላ ከላይ የተዘረዘሩ የአነባብ ስልቶች በአላማም ሆነ በአተገባበር የተለያዩ ቢሆኑም አንዱ ሲተገበር ሌላውም አብሮ በውስጥ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ሰፊ የአነባብ ስልትን ተከትለን ስናነብ ሂስ እየሰጠን በአትኩሮት እናነባለን፤ ለአዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እየሰጠን እናነባለን፡፡ በተጨማሪም በአሰሳ በምናነብበት ጊዜ ተፈላጊውን መረጃ እስከምናገኝ በአሰሳ ካነበብን በኋላ መረጃውን እንዳገኘን መረጃወን በደንብ ለመረዳት ያነባብ ስልታችን ወደ ትኩረት ንባብ ይቀየራል፡፡ ስለዚህ መምህሩ ይህንን ጉዳይ ተገንዝቦ እንደየአስፈላጊነታቸው በቅንጅት ሊያስተምራቸው እና አቀናጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ መርዳት አለበት፡፡

## 2.6 የምንባብ አመራረጥ

ለትምህርት የሚቀርቡ ምንባቦችን በጥሞና በተገቢው ሁኔታ አደራጅቶ ማቅረብ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ ሲመረጥም ለክፍሉ ደረጃ የሚመጥን መሆን አለመሆኑ እና ወቅታዊ መሆኑ ሊፈተሽ ይገባል፡፡ አመራረጡንም በተመለከተ Nuttall (1982), Williams (1984) እንደሚከተለው ይላሉ፡፡ የሚመረጠው ምንባብ አብዛኛውን ተማሪ ሊስብ የሚችልና በፍላጎቱ እንዲያነብ ሊገፋፋው የሚችል ወይም አሳታፊ የሆነ ምንባብ፣ ከተማሪዎች አካባቢ ማህበረሰብ ባህል፣ ጋር የተዛመደ ምንባብ ሊመረጥ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪ Nuttal (1982:30) የሚመረጠው ምንባብ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት እንዲቀሰቅስ ምንባቡ አዳዲስ እውቀትን ሊይዝ ይችላል ተብሎ የሚገመት ርዕሰ ጉዳይ፣ የሌሎችን ሰዎች አመለካከት ከራሳቸው ጋር ለማነፃፀር የሚያስችል ምንባብ፣ ስለርዕሰ ጉዳዩ ለመረዳት ጥልቅ ምርምርን የሚጠይቅ፣ ፍፃሜውን ለማወቅ የሚያጓጓ፣ ለደረጃው የሚመጥን፣ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት አመቺ የሆነ ምንባብ ሊሆን ይገባል፡፡ የሚመረጠው ምንባብ ይዘት ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የሚጣጣም ከሆነ የቋንቋ ችሎታ ባይኖራቸውም አንብቦ ሊረዱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ለትምህርት የሚቀርበው ምንባብ የተማሪዎችን ደራዊ እውቀትና ፍላጎት ያገናዘበ መሆን አለበት እንግዳ (1992፣ 39) Coady (1979) እና Hudgun (1982)ን ጠቅሰው ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ የሚመረጡ ምንባቦች ወቅታዊ የሆኑ፣ የተማሪውን ደረጃና ፍላጎት የሚመጥኑ ሃይማኖታዊ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ሆነው የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጐት የሚቀሰቅሱ ሆነው ሊቀርቡ እንደሚገባ ከምሁራኑ ሃሳብ መረዳት ተችሏል፡፡

## 2.7 የማንበብ ክሂልን የማስተማሪያ ሞዴሎች ምንነት

### 2.7.1 የላይ-ታች ሞዴል (Top Down)

USAID /Ethiopia (2003: 43) የላይ ታች ሞዴል፣ ከጥቅል ዋና ሃሳብ ጀምሮ ዝርዝሩን የሚያካትት ነው፡፡ የጽሁፉን መልዕክት አንብቦ ለመረዳት በአንባቢዎች የቅድመ እውቀትና ልምድ ላይ መሠረት የሚያደርግ ሞዴል ነው፡፡ በዚህ ዘዴ የማንበብ ሂደቱ በመላምትና ትንበያ በመጀመር የጽሑፍን መልዕክት ከቀድመ እውቀት ጋር በማቀናጀት ማረጋገጥን የሚጠይቅ ነው፡፡ ሞዴሉ ቃላትን ለይቶ ለማወቅ ዘግምተኛ የሆነና ስለሚነበበው ጽሑፍ የቀድመ እውቀት ላለው ደካማ አንባቢ ቀላል የሆነ ሞዴል መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

Nuttal (1982) አንባቢያን በዚህ ሞዴል ተጠቅመው ለማንበብ የቀደመ እውቀት ሊኖራቸውና ያንን እውቀትና ልምድ መነሻ ቢያደርጉ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ያፋጥናል ብለዋል፡፡ የምንባቡንም መልዕክት ምንባቡን ከማንበቡ በፊት በተመንበይና መላምቶች በማስቀመጥ በሚያነብበት ወቅት ደግሞ እነዚህን እያረጋገጠ ከቀዳሚ እውቀቱ ጋር እያዛመድ መልእክቱን ለመተርጎምና ለመረዳት ጥረት የሚያደረግበት ሞዴል ነው፡፡

ግሩም (2003፣11) Carelli (1988), Gove (1983), Graban & Stoller (2002), Anderson (2000)ን ጠቅሰው የላይታች ሞዴል ትኩረት የሚያደርገው፣ የጽሑፉን ሃሳብ በማብላላት፣ በአንባቢው ግብና ግምት ላይ ነው፡፡ ከማንበቡ በፊት የገመትውንና የተነበየውን ትንበያ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ስህተት ከሆኑ በቂ የሆነ መረጃን ከጽሑፉ ለማግኘት ጥረት የሚደረግበት ሞዴል ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ ወቅትም ሞዴሉ ችሎታን ያቀላጥፋል፡፡ በላይታች ሞዴል ጠቅሞ ለማንበበ አንባቢው የቀድመ እውቀት ሊኖረው እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

Nunan (1993፣ 67) በዚህ ሞዴለ የአንብቦ መረዳት ትምህርትን ለመማር ሰዋስዋዊ እውቀት ብቻ በቂ እንዳልሆነና ይህን እውቀት ለማዳበር የሚያስችሉ ዳራዊ እውቀት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን ሁለቱ ሰዋስዋዊ እውቀትና ዳራዊ እውቀትን ይዞ አንባቢው የሚያነበው ከሆነ ዳራዊ እውቀቱን በዓለም ካሉ ነገሮች ጋር በማያያዝ ለማሰታወስና ሊመጣ የሚችለውን ለመገመት

ትልቅ እገዛ ያደርጋል፡፡ በዚህም ሁኔታ ያለ አንባቢ ቀድሞ ስለሚያነበው ነገር አጠቃላይ እውቀት ካለው ዝርዝር ጉዳዩን በቀላሉ ይረዳዋል፡፡

እንግዳ (1992) Goodman (1970)ን ጠቅሰው ተማሪዎች የማንበብ ክሂል ለማዳበር ትምህርታዊ ክንውኖችንን ረቂቅ ነገሮችን ለመተርጎምና ለመረዳት ከማከናወን በፊት አጠቃላይ መልዕክቱን ለመረዳት የሚጥሩበት ነው፡፡ ይህንን አጠቃላይ መልዕክት ለመረዳት ከማንበባቸው በፊት ርዕሱን አይተው ምን ምን ርዕሰ ጉዳዮችን በምንባቡ ውስጥ ሊያገኙ እንደሚችሉ መገመት አለባቸው፡፡ በሚያነቡበት ጊዜ ደግሞ የገመቱትን ግምት አንብበው ከሚያገኙት እውቀት ጋር በማዛመድ ትክክል መሆን አለመሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡ ይዘታቸው ስህተት ከሆነ ለስህታቸው ምክንያቱን ይሰጣሉ፡፡

እንግዳ (1992፣ 20) Higgins (1984) እና Goodman (1970)ን ጠቅሰው በዚህ ሞዴልን ማንበብ ዓላማ መወሰንን፣ የምንባቡን መልዕክት አስቀድሞ መገመትን፣ የተገመተውን ግምት ለማረጋገጥ ደጋግሞ አንብቦ የተገኘውን መልዕክት ከቀዳሚ እውቀት ጋር በማዛመድ መገምገምን የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ እንግዳ በተጨማሪም Silberstein (1977)ን ጠቅሰው ሞዴሉን ተጠቅመው መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት ተማሪዎች ከምንባቡ ተፈላጊውን መረጃ አንብበው እንዲያገኙ ለማድረግ እያንዳንዱ ቃል ከመተርጎም ይልቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው አጠቃላይ መልዕክቱ ላይ እንዲያነጣጥሩ መምህራን አመቺ፣ ማራኪ አውዶች እና መልመጃዎችን አዘጋጅተው ማለማድ አለባቸው፡፡ ልምምዱም መካሄድ ያለበት በሚከተሉ የአነባብ ስልቶች ነው፡፡ በአሰሳ፣ በገረፍታ፣ በአድምታ የአገባብ ስልት ተጠቅመው ትንበያቸውን እንዲያረጋግጡ፣ አንባቢው ፍቺና ድርሰታዊ ፍንጮችን እንዲያገኙ በማድረግ ማለማመድ እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል፡፡

### 2.7.2 የታች-ላይ ሞዴል (Bottom Up)

USAID /Ethiopia (2003) የታች ላይ ሞዴል ከዝርዝር ሃሳብ በመነሳት ወደ አጠቃላይ ሃሳብ የሚሄድ ዘዴ ነው፡፡ አቀራረቡም ማንኛውንም የምንባቡ ዋና ሃሳብ በተማሪዎቹ ጥረት እንዲገኙ አድርጎ ማቅረብና፣ የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ መረዳታቸውን ለማረጋገጥም ቃላትን ወደድምጽ መቀየር መቻላቸው መፈተሽ ነው፡፡ ሌላው በዚህ ዘዴ የማንበብ ትምህርት ሲቀርብ ተማሪዎች በፍጥነት ቃላትን ለመለየትና ለማወቅ የሚያስችሉ መልመጃዎች ሊቀርቡ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ቃልንና ሀረግን ለይቶ ማወቅ፡፡

ግሩም (2003፣ 910) Grabe and Stoller (2002) እና Anderson (1999)ን ዋቢ አድርገው በታች ላይ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል ተማሪዎቹ አንብበው እንዲረዱ በአንባቢው የቀደመ እውቀትና በጽሑፉ መካከል ጣልቃ ገብነት ሳይኖር አንባቢው የጽሑፉን መልዕክት በጥቃቅን ቅንጣቶች በመጠቀም ትርጉም ለመስጠት ይጥራል፡፡ እያንዳንዷን የቋንቋ ቅንጣት ፊደላትን፣ ቃላትን ለይቶ ካወቀ በኂላ ፀሐፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት የሚረዳበት ሂደት ነው፡፡ ስለዚህም የታችላይ ሞዴል መስመራዊ ነው ማለት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ግሩም (2003) Anderson (1999), Grabe (1991, 39)ን ግሩም ጠቅሰው የታች ላይ ሞዴል አንባቢው የጽሑፉን መልዕክት ለመረዳት ከአነስተኛ ውህድ አሀድ እና ስነልሳናዊ አሃዶች ከድምፆች ጀምሮ ምዕላድን፣ ቃላትን፣ ሐረግን፣ ዓረፍተ ነገሮችን እየተገነዘበ ከሄደ በኂላ በመጨረሻ ላይ አጠቃላይ ግንዛቤን የሚያገኙበት ነው፡፡

ግሩም (2003፣ 12) Harmer (2001) እና Garbe (1988) ጠቅሰው በላይታች እና በታች ላይ የማንበብ ሞዴሎች መካከል ያለውን ልዩነት ሲገልፅ “የታችላይ” ሞዴል በጫካ ውስጥ ሆኖ እያንዳንዱን ዛፍ ከመመርመር ጋር ሲያያይዝ የላይታች የማንበብ ሞደል ደግሞ አንድ ነገርን አዝቅዝቆ እንደ መመልከት ይቆጠራል እንዳሉ ገልጸዋል፡፡

ከዚህም አገላለጽ እንደምንረደው የአንብቦ መረዳት ችሎታ፣ በፍጥነት ለማዳበር ተመራጭነት ያለውና ውስብስብ ያልሆነው ሞዴል የላይታች ሞዴል እንደሆነ ነው፡፡ ግሩም (2003) Garbe (1988)ን ጠቅሰው የተለያዩ የመስኩ ተመራማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ሁለቱም የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴሎችን በማነፃፀር እነሱ አጥንተው ያገኙት የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል ተቀባይነት እንዲያገኝ የግል አስተያየታቸውንና ሃሳባቸውን ይሰነዝራሉ ማለታቸውን ገልጸዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው ከዚህ በፊት አጥኚዎቹ ፈትሸው ያገኙትን ሞዴል ለአንብቦ መረዳት ችሎታ የበለጠ ውጤታማ መሆኑን ዝም ብሎ ከመቀበል የትኛው ሞዴል ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መዳበር የተሻለ እንደሆነ በሙከራዊ ምርምር ዘዴ በማነፃፀር ለመፈተሽ ነው፡፡

## 2.8 ቀደምት የጥናትና የምርምር ስራዎች ቅኝት

ቀደምት የጥናትና ምርምር ስራዎች በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥናት ለማካሄድ ለሚነሱ አጥኚዎች በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ ጥናቶች ፍንጭ ሰጪነታቸው የጐላ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ በማንበብ ትምህርት ዙሪያ ከዚህ በፊት የተሰሩ ጥናታዊ ስራዎችን ለመቃኘት

ተሞክሯል። ከእነዚህም ውስጥ የተወሰኑትን ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ግንኙነትና ልዩነት እንደሚከተለው ለመጥቀስ ተሞክሯል።

እንግዳ (1992) "ቶፐዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል የአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት በሚል ርዕስ የተጠና ነው። ጥናቱም የላይታች ሞዴልን በመጠቀም የንባብ ክሂልን ማስተማር ውጤታማ እንደሆነ አመልክቷል።

መአዛ (2003) "በዘጠነኛ ክፍል የንባብ ትምህርት ሲሰጥ ለንዑሳን ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሦስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ ጥናት አካሄዳለች። የጥናቷ ትኩረትም መምህራን ንባብ በክፍል ሲያስተምሩ በንዑሳን ተግባራት ትኩረት ይሰጣሉ? የሚለውን ጥያቄ በትኩረት መፈተሽ ነው። ከጥናቷም ያገኘችው ውጤት መምህራን የንባብ ትምህርትን ሲያስተምሩ ለአብዛኛዎቹም ንዑሳን የንባብ ክሂሎች ዝቀተኛ ትኩረት እንደሚሰጡ አረጋግጣለች።

ግሩም (2003) "የላይታች" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር ያለው ውጤታማነትና ተተግባሪነት በስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ነው። ጥናቱም የታችላይ ሞዴል ተጠቅሞ ንባብ ማስተማር ውጤታማ እንደሚያደርግ በፍትነታዊ ሙከራ አረጋግጧል።

ይህንን ጥናት ከላይ ከተጠቀሱት ጥናታዊ ጽሑፎች አንድ የሚያደርገው በማንበብ ትምህርት ዙሪያ የሚሰራ መሆኑ ነው። ይሁን እንጅ ሁሉም ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ለማጥናት የተጠቀሙበት ቦታ፣ ጊዜ የትኩረት አቅጣጫ የተለያየ ነው። ከዚህም አንፃር ሲታይ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ልዩነቱ የእንግዳ ጥናት ከዚህ ጥናት የሚለየው እሱ ትኩረት ያደረገው በላይታች ሞዴል ላይ ብቻ መሆኑ፣ የመአዛን ጥናት ከዚህ ጥናት የሚለየው እሷ ትኩረት ያደረገችው የንዑሳን ንባብ ክሂሎች አተገባበር ላይ መሆኑን፣ የግሩም ጥናት ከዚህ ጥናት የሚለየው ግሩም የታችላይ የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል ላይ ብቻ ማጥናቱ ነው። ይህን ጥናት ከሌሎቹ የሚለየው የላይታች እና የታችላይ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴሎችን በማነፃፀር የትኛው የማንበብ ትምህርትን ለማስተማር የተሻለ ሞዴል መሆኑን ለመለየት በንፅፅር ያጠና መሆኑ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

# 3. የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከላይ ታች እና ከታች ላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ ለመረዳት ክሂል ያላቸውን አስተዋጽኦ በማነጻጸር ከሁለቱ ሞዴሎች ተማሪዎችን የበለጠ ውጤታማ የሚያደርገውን መለየት ነው። ይህንንም ለማድረግ መላምት በመምታት ትክክልኝነታቸውን ለማረጋገጥ ሙከራዊ የምርምር አይነትም በመጠቀም የተገኙ መረጃዎችን ያለው (2004፣247) ላይ ካስቀመጣቸው ገላጭ እና ድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ውስጥ በመጠናዊ ምርምር ወቅት ገላጭ ስታቲስቲክስን መጠቀሙ የግድና አስፈላግ መሆኑን ጠቅሰዋል። ይህም ጥናት መጠናዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ስለሆነ የተገኙ መረጃዎችን በገላጭ ስታቲስቲክስ ተተንትኖ ቀርቧል።

## 3.2 የናሙና አወሳሰድ ዘዴ

### 3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በጋሞ ጎፋ ዞን በዑባ ደብረፀሐይ ወረዳ ነው። በወረዳው ውስጥ 25 የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ ካለው የጊዜ፣ የጎልበትና የገንዘብ ውስንነት የተነሳ አመቺ ናሙናን በመጠቀም በቶሙሉ አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤት ተመርጧል።

### 3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ ካሉ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የሰባተኛ ክፍል በአመቺ ናሙና ተመርጧል ።ይህም የሆነበት ምክንያት የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በክልላቸው ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ስለሚወዳደሩ እነሱ ላይ ጫና ላለመፍጠር ሲባል አልተመረጡም።የተቀሩት አምስተኛ እና ስድስተኛ ክፍሎች ያልተመረጡት ደግሞ በእነዚህ ክፍል ደረጃ ከሚገኙ ተማሪዎች ይልቅ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ከሌሎች የክፍል ደረጃ ተማሪዎች የተሻለ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ተብሎ ስለታሰበ ነው።በዚህ ክፍል ደረጃ ካሉ አራት የሰባተኛ ክፍል ምድቦች ውስጥ ‹‹7ኛA››እና‹‹7ኛB››በዕጣ ናሙና ተመርጠዋል። በእነዚህ ክፍሎች የሚገኙ ተማሪዎችም ተጠኚ ሆነዋል።

## 3.3 የምንባቦች አመራረጥ የመልመጃዎች አዘገጃጀት

Nuttal (1982), Williams (1984) ለትምህርት የሚመረጠው ምንባብ አብዛኛውን ተማሪ በፍላጎቱ እንዲያነብ የሚያደርግ፤ ከተማሪው አካባቢ ማህበረሰብ ባህል ጋር የሚስማማ፤ አዳዲስ እውቀትን የያዘ፤ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚያስችል ሊሆን እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ለማዳበር የሚቀርብ ምንባብ መመረጥ ያለበት ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ መሆን አለበት፡፡ ይህም ማለት ምንባቡ የተማሪዎችን ፍላጎት ያገናዘበ፣ ወቅታዊ የሆነ፣ ከክፍል ደረጃቸው ጋር የተመጣጠነ፣ የተማሪዎችን ፍላጎት መቀስቀስ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ የደቡብ ክልል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጸሀፍ አዘጋጆች ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ይመጥናል ብለው ካዘጋጁ ምንባቦች የተወሰኑት መጸሀፉ ላይ በተቀመጡት ቅደም ተከተል መሰረት ለጥናቱ ተወስደዋል፡፡

የተመረጡ ምንባቦችም ከሰባተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ መሆኑ ከላይ ተገልጿል፡፡ ምንባቦችም ለጥናቱ ከመዋላቸው በፊት ተማሪዎች ያልተማሩዋቸው መሆናቸው ተረጋግጦ የተመረጡ ናቸው፡፡ ምንባቦቹም የመጀመሪያው "የአፈር እንክብካቤ"፣ሁለተኛው "የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት"እና ሦስተኛ "ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች" በሚል ርዕስ የቀረቡ ምንባቦች ናቸው፡፡ ምንባቦቹ ለትምህርት በሚቀርቡበት ጊዜ የግብአት እጥረት ኖሮ አንብቦ ለመረዳት ሂደቱ እንቅፋት እንዳይፈጥር ምንባቦቹ ከትምህርቱ ክፍለጊዜ ቀድመው በተማሪዎቹ ቁጥር ተባዝቷል፡፡ከዚያ በኋላ በክፍለ ጊዜው ለማስተማር የታቀደው ምንባብ ለተማሪዎቹ ከተዳረሰ በኋላ የማንበብ ትምህርቱን እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

የመልመጃዎችም በምዕራፍ ሁለት ላይ በምሁራን የተጠቀሱ የመልመጃ ዓይነቶችን መሠረት በማድረግ ለሁለቱም ሞዴሎች ተዘጋጅቶ ቀርቧል (ከአባሪ ሁለት እስከ ሰባት ያሉትን ይመለከቱ)፡፡

የተዘጋጁ የመልመጃ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ማስተማሪያነት ከመቅረባቸው በፊት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሁለተኛ ዲግሪ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪ ለሆኑ ሁለት ተማሪዎች ቀርበው በሰጡት አስተያየት መሰረት ማስተካከያ ተደረገ፡፡ በኋላም ለአማካሪ ቀርቦ የመጨረሻ ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ በተግባር ላይ ውለዋል፡፡

### 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለው ፈተና ነው። በተጨማሪነትም ምልከታና የጽሑፍ መጠይቅ መረጃ መሰብሰብያ ሆነው በጥቅም ላይ ውለዋል።

#### 3.4.1 የፈተና አዘገጃጀትና አፈታተን

አንብቦ የመረዳት ፈተና ዓላማው በተማሪዎች መካከል ያለውን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ነው። ይህም አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤትን የሚወስነው የቀረበው ምንባብ፣ ከምንባቦቹ የወጡ ጥያቄዎችና ለተማሪዎቹ ምንባቡን በተመለከተ በሚኖራቸው ዳራዊ እውቀት ነው እንግዳ(1992፣50) እና ( Weir (1993)፣ Maderson (1983) እና Hughes (1989)ን ዋቢ አድርገው ገልጸዋል።

ከዚህ አገለለጽ እንደሚንረዳው ለፈተና የሚቀርቡ ምንባቦች ጥያቄዎች ከተማሪዎች የክፍል ደረጃ ጋር የማይመጣጠኑ፣ ዳራዊ እውቀታቸውን ያላገናዘቡ ሆነው ከቀረቡ በተማሪዎች ውጤት ላይ ተጽኖ ስለሚፈጥሩ አዘገጃጀቱ ጥንቃቄ እንደሚጠይቅ ነው።

ቅድመ ልምምድ ፈተና ማለት ልምምድ ከመደረጉ በፊት የሚሰጥ ፈተና ማለት ነው። ለተጠኚ ተማሪዎች የቅድመ ልምምድ ፈተና ተሰጥቷቸዋል። ዓላማውም ከልምምድ በፊትበሁለቱ ተጠኚ ምድቦች መካከል የአንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ያህል እንደሆነ ለመፈተሽ ነው። ድህረ ልምምድ ፈተና ማለት ልምምድ ከተደረገ በኂላ የሚሰጥ ፈተና ማለት ነው። የተጠኚ ተማሪዎች ከልምምዱ በኂላ የተፈተኑትን ፈተና ውጤት ከቅድመ ልምምዱ ውጤት ጋር በማነፃፀር በየትኛው ሞዴል ማስተማሪያነት የተማሩ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት እንዳስመዘገቡ ለመለየትና ለወደፊቱ ተማሪዎች በየትኛው ሞዴል ቢማሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ከፍተኛ እንደሚሆን ለሚመለከተው አካል የመፍትሄ  አቅጣጫ ለማስቀመጥ ነው።

በመማሪያ መጽሐፋቸው ከቀረበላቸው ምንባቦች "ጉዞ ወደ ጊቤ ሸለቆ ብሔራዊ ፓርክ" በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ለፈተና ተመርጧል። ምንባቡንም መሰረት በማድረግ  50 ጥያቄዎችን (23 ምርጫ ሰጪ፣ 7 እውነት ወይም ሐሰት፣ 15 የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ የሚጠይቁ ጥያቄዎች 5 ክፍት ጥያቄ) ተዘጋጀ። ለተማሪዎቹ ከመቅረባቸው  በፊት ለሁለት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቀርቦ ከተገመገመ

በኋላማስተካከያ ተደርጓ፡፡ ከዚያም ለአማካሪ ቀርቦ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ከተስተካከለ በኋላ ለተማሪዎሪቹ ቀርቧል፡፡

በቅድመ ፈተና ውጤት ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ከተገመገመ በኋላ ምድብ 7Aን በ"ላይ ታች" ሞዴል እንዲሁም ምድብ 7Bን በ"ታች ላይ" ሞዴል እንዲያስተምሩ ስለሞዴሎቹ ዝርዝር መገለጫዎችንና የአተገባበሩ ሂደት ምን መምሰል እንዳለበት የተመረጡ ምድቦችን ለሚያስተምሩ መምህራን ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በማብራሪያው ላይም ውይይት ተደርጓል፡፡ በተሰጣቸው ማብራሪያና በተካሄደው ውይይት መሠረት ተግባራዊ እንደሚያደርጉና እንደማያደርጉ ምልከታ ከተደረገ በኋላ ተማሪዎቹ ትምህርቱንም በየሳምንቱ 3 ክፍለጊዜ ከጥቅምት 6 እስከ ህዳር 1 ድረስ እንዲከታተሉ ተደርጓል፡፡

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ የታቀደው ልምምድ ከተጠናቀቀ በኋላ የተማሪዎችን ከልምምድ በፊትና ከልምምድ በኋላ  አንብቦ  በመረዳት ችሎታ ያሳዩትን ለውጥ ለማነጻጸር እንዲያመች በቅድመ ልምምድ የተሰጠው ፈተና በድጋሚ በድህረ ልምምዱ ተሰጥቷል፡፡ የፈተናው ዓላማ በቅድመ ልምምድ ተፈትነው ካመጡት ውጤት ከሁለቱ ሞዴሎች በየትኛው ሞዴል የተማሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ውጤት ከፍተኛ እንደሆነ ለማወቅና ከሁለቱ የተሻለው ሞዴል የትኛው እንደሆነ ለመለየት  ነው፡፡ የአፈታተኑ ሁኔታም ፈተናው ለሁለቱም ምድቦች በተመሳሳይ ሰዓት ቀርቦላቸው ከተፈተኑ በኋላ የተሰበሰበው የፈተና ወረቀት በትምህርት ቤቱ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ተጠሪዎች አማካኝት ታርሟል፡፡

### 3.4.2 ለተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሑፍ መጠይቁ ስለ አንብቦ መረዳት ችሎታ እና ስለማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብ በ2 ክፍሎች ተከፍሎ የቀረበ ነው፡፡ በአደኛው ክፍል 3 የተማሪዎችን ዳራ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በክፍል ሁለት አጠቃላይ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ከልምምድ በፊት የማንበብ ትምህርትን አቀራረብ ምን እንደምመስል መረጃ ለማገኘት 12 ዝግ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በዚሁ ክፍል ልምምድ ያደረጉበትን የማንበብ ትምህርት የመልመጃዎች አቀራረብና ማስተማሪያ ሞዴልን በተመለከተ መረጃ የሚጠይቁ 10 ዝግ ጥያቄዎችና 1 ክፍት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

የጽሑፍ መጠይቁ በምዕራፍ ሁለት የቀረበውን የምሁራንን ሃሳብ መሠረት በማድረግ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የማንበብ ትምህርቱ ለተማሪዎችል እንዴት እየተሰጠ እንዳለ

ለወደፊቱ እንዴትና በየትኛው ሞዴል ቢማሩ የተሻለ እንደሆነ መረጃን ለማግኘት በሚያመቹ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡ የተዘጋጀውም መጠይቅ ለተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሁለተኛ ዲግሪ በአማርኛ ቋንቋ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ለሆኑ ሁለት ተማሪዎች በመስጠት ተገምግሞ ማስተካከያ ተደረገ፡፡ ከዚያ በኋላ ለአማካሪ ቀርቦ ማስተካከል የሚገቡ ነጥቦችን በማስተካከል መጠይቁ ተዘጋጅቷል(አባሪ-ስምንትና ዘጠኝ ይመልከቱ)፡፡

ከላይ በተዘረዘረው መልኩ ተዘጋጅቶ የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ ለተጠኚ ተማሪዎች በተቃራኒ ፈረቃቸው ፈቃደኛ የሆኑ መምህራን ጋር በመተባበር እንዲሞሉ አድረግን፡፡

### 3.4.3 ምልከታ

ለዚህ ጥናት ከፈተና ውጪ በተጨማሪነት መረጃ መስብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ከሚያገለግለው ምልከታ አንዱ ነው፡፡ ምልከታውንም ከልምምዱ በፊት መምህራን የማንበብ ትምህርትን እንዴት እያስተማሩ እንደሆነ ለማየት በሁለቱም ክፍሎች ሦስት ሦስት ክፍለ ጊዜ እና ልምምዱ በሚካሄድበት ወቅት የማንበብ ትምህርቱን በተሰጣቸው የሞዴሎች ማስተማሪያ መሰረት ማሰተማር አለማሰተማራቸውን ለመከታተል የክፍል ውስጥ ክንውን በመመልከት ማስታወሻ ተይዟል፡፡ የተመዘገበው የማስታወሻ ሃሳቦችም አጠር ባለ መልኩ ቀርበዋል (አባሪ አስር ይምልከቱ)፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን

### 3.5.1 ከፈተና ውጤቶች የተገኙ መረጃዎች

የቅድመ ልምምድ ፈተና በ "ላይታች" ሞዴል ለሚማሩም ሆነ በ "ታችላይ" ሞዴል ለሚማሩ ተማሪዎች ተሰጥቷል፡ ታርሞ የተገኘውም ውጤት የሁለቱን ምድቦች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለማነፃፀር በሚያመች መልኩ ገላጭ ስታቲስቲክስን በመጠቀም በአማካይ፣ በልይይትና በመደበኛ ልይይት ተሰልቶና ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ (ሰንጠረዥ አንድና ሁለትን ይመልከቱ)፡፡

### 3.5.2 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት

በጽሑፍ መጠይቁ አማካይነት የቀረቡ ጥያቄዎች ትኩረት ከሚሰጥባቸው ጉዳዮች አንጻር ተለይተው ከተደራጁ በኋላ በክፍል ሁለትና ሦስት ለቀረቡ ጥያቄዎች በእያንዳቸው የተጠሰው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ተቆጥሮ በብዛትና በመቶኛ ተለይቶ ተመዝግቧል፡፡ ለክፍት ጥያቄ አብዛኛው ተማሪ የሰጡት መልስ በመረጃነት ተመዝግቧል፡፡

### 3.5.3 ከምልከታ የተገኘ ውጤት

በቅድመ ልምምድ በተደረገው ምልከታ መምህራን አንብቦ የመረዳት ክሂልን እንዴትባለመልኩ እንደሚያስተምሩ፤ በልምምዱ ወቅትም የተሰጣቸውን ማብራሪያና ማስተማሪያ ግብአቶችን ተጠቅመው ማስተማራቸውን በመከታተል የተያዘውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ እየዳበረ የሄደው በየትኛው ሞዴል በመማራቸው እንደሆነ በአጭሩ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የዚህ ጥናት አላማው ከላይ ታች እና ከታች ላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ ለመረዳት ክሂል ያላቸውን አስተዋጽኦ በማነፃፀር ከሁለቱ ሞዴሎች ተማሪዎችን የበለጠ ውጤታማ የሚያደርጋቸውን ለመለየት ነው፡፡

ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት ሲባል ጥናቱ በበቶ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአንድ ወር ከአምስት ቀናት ሲካሄድ የሚከተሉ ሂደቶችና ክንውኖች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

በ25/01/2010 ዓ.ም ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህራን ጋር በመገናኘት ስለመጣሁበት ጉዳይ ተነጋግረን፡፡ በጉዳዩ አላማ ገለፃ አድርጊ ከተማመንን በኋላ በወቅቱ ሰባተኛ ክፍሎችን አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የተመደበችውን መምህርትና የክፍለ ትምህርቱ ተጠሪዎች ጋር አገናኙኝ፡፡ ከነዚህ አካላት ጋር ስለጥናቱ ዓላማ፣ አስፈላጊነት፣ ስለሚጠኑ ሞዴሎች ምንነት በስፋት ከተወያየን በኋላ የማጠቃለያ ገለፃ ተደረገላቸው፡፡ ከዚያም የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህርቷ ጋር በመሆን በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከነበሩ ሦስት የሰባተኛ ክፍል ምድቦች ሁለቱን ምድቦች በእጣ ከለየን በኋላ ከነዚህም የትኛው ምድብ በላይታች ሞዴል የትኛው በታች ላይ ሞዴል እንደሚማር በድጋሚ በእጣ ለየናቸው፡፡ ከዚያ ምድቦቹ በቀጣዩ ቀን በተቃራኒ ፈረቃ እንድትጠራቸው ወስነን ተለያየን፡፡

በ26/01/2010 ዓ.ም እነዚህን የለየናቸውን ምድቦች በተጠሩት ሰዓት ከተገኘው በኋላ ለጥናት የተመረጡ መሆናቸውን ገለፅን፡፡ ለጥናቱ ፈቃደኛ መሆናቸውን እጅ በማውጣት እንዲገለጽ አድርገን ፈቃደኝነታቸውን አረጋገጥን፡፡ ከዚያም ስለ ጥናቱ ዓላማ፣ ስለ አንብቦ መረዳት ምንነት፣ ስለአነባብ ስልቶች በስፋት ከተወየየን በኋላ በመቀጠልም በቀጣዩ ቀን ልምምድ ከመጀመራቸው በፊት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን የሁለቱ ክፍሎች ምን እንደሚመስል ለመለየተ ቅድመ ልምምድ ፈተና እንደሚሰጣቸው ተነጋግረን ቀኑንና ሰዓቱን ወስነው ተለያየን

በ29/01/2010 ዓ.ም ሁለቱም ምድቦች በተመሳሳይ ሰዓት የቅድመ ልምምድ ፈተናውን ተፈተኑ፡፡ ወረቀታቸውም ተሰብስቦ በአማርኛ ቋንቋ መምህርቷና ከሌሎች ሁለት ነባር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በመሆን በማረም ውጤቱ ተመዝግቧል፡፡ ይህንንም በተሳታፊ በተመልካችነት መከታተል ችያለሁ፡፡

በ6/02/2010 ዓ.ም እስከ 1/03/2010 ዓ.ም ድረስ በላይታች እንዲለማመዱ የተመረጡ ተማሪዎችን ለክፍሉ አማርኛ ቋንቋን እንድታስተምር የተመደበችው መምህርት ስታስተምር በታችላይ እንዲማሩ ዕጣ የደረሳቸውን ተማሪዎችን ደግሞ አንዲት የትምህርት ቤቱ ነባር የአማርኛ የቋንቋ መምህርት በፈቃደኝነት አለማመደች፡፡ እነዚህ ሁለቱም በሚያለማምዱ ሰዓት ተገኝቼ በተመልካችነት የሂደቱን ተገቢነት ተከታትያለሁ፡፡

ልምምዱ ለምህራንና ለተማሪዎች በተገለጸውና በተወያየነው መሠረት ለአራት ሳምንታት ከተካሄደ በኋላ ተማሪዎች ከልምምድ በኋላ በየትኛው ሞዴል የተለማመዱ በአንብቦ መረዳት ከፍተኛ ውጤት እንዳስመዘገቡ ለመለየት የሚረዳ ድህረ ልምምድ ፈተና በቀን 4/03/2010 ዓ.ም ተሰጥቷቸዋል፡፡

በዚህም መሠረት ዓላማውን ለማሳካትና ለመፈተሽ የሚያስችሉ ዝርዝር ዓላማዎች በምዕራፍ አንድ በ1.2 ስር የቀረቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ በሚያስችል መልኩ መረጃዎች ከተሰጡ ቅድመና ድህረ ፈተናዎች፣ ከጽሑፍ መጠይቅና ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች በሚከተለው መልኩ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 4.1 የፈተና ውጤት ትንተና

የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ ለመመዘን ከሚያስችሉ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንዱና ዋነኛው የተማሪዎቹ የፈተና ውጤት መሆኑ በምዕራፍ ሦስት ላይ ተገልጿል፡፡ በዚህም መሠረት ለሁለቱም ምድቦች የቅድመና የድህረ ልምምድ ፈተና ከ50% ተሰጥቷቸው ያገኙት ውጤት ድምር፣ አማካይ፣ ልይይትና መደበኛ ልይይት፣ በጉልህ ደረጃና፣ በነፃነት ደረጃ ቲ-ቴስት ተሰልቶ ከቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ ጋር በማነፃፀር የተገኘው በድምዳሜ ሃሳብ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 4.1.1 የቅድመ ልምምድ ፈተና ትንተና

ተማሪዎች ከመለማመዳቸው በፊት ተፈትነው ያመጡት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

ሰንጠረዥ 1፡ የቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤትን የሚያሳይ

| በላይታች እንዲለማመዱ የተመረጠው ምድብ የፈተና ውጤት 7ኛ “A” | | በታች ላይ ሞዴል እንዲለማመዱ የተመረጠው ምድብ የፈተና ውጤት 7ኛ “B” | |
|---|---|---|---|
| 1.38 | 24. 24 | 1. 37 | 24.21 |
| 2.37 | 25.23 | 2.36 | 25.20 |
| 3.37 | 26.23 | 3.36 | 26.20 |
| 4.34 | 27.24 | 4.35 | 27.19 |
| 5.33 | 28.24 | 5.35 | 28.19 |
| 6.32 | 29.24 | 6.34 | 29.18 |
| 7.31 | 30.24 | 7.32 | 30.18 |
| 8.31 | 31.22 | 8.35 | 31.17 |
| 9.30 | 32.21 | 9.32 | 32.16 |
| 10.30 | 33.21 | 10.31 | 33.15 |
| 11.30 | 34.20 | 11.30 | 34.14 |
| 12.29 | 35.18 | 12.30 | 35.14 |
| 1329 | 36.15 | 1329 | 36.19 |
| 14.28 | 37.12 | 14.28 | 37.12 |
| 15.28 | 38.12 | 15.27 | 38.13 |
| 16.27 | 39.11 | 16.27 | 39.13 |
| 17.27 | 40.11 | 17.25 | 40.13 |
| 18.27 | 41.8 | 18.25 | 41.12 |
| 19.28 | 42.9 | 19.24 | 42.11 |
| 2025 | 43.7 | 20.24 | 43.10 |
| 21.25 | 44.6 | 21.23 | 44.9 |
| 22.25 | 45.4 | 22.22 | 45.8 |
| 23. 25 | | 23. 22 | 46.7 |
| | | | 47.6 |
| $x_1$=1047<br>$\overline{X}_1$=23.26<br>$n_1$= 45<br>$s^2{}_1$=75.05<br>$s_1$=8.66 | | $x_2$= 1024<br>$\overline{X}_2$=21.78 | $n_2$=47<br>$s_2{}^2$= 79.13<br>$s_2$= 8.89 |

ከላይ ከቀረበው የሠንጠረዥ መረጃ ላይ ለመረዳት እንደተሞከረው በላይ ታች ሞዴል እና በታች ላይ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል ልምምድ ለማድረግ የተመረጡ ተማሪዎች ከመለማመዳቸው

በፊት የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው በሁለቱ ምድቦች መካከል ምን እንደሚመስል ውጤታቸው በዝርዝር ሰፍሯል፡፡ ከውጤታቸው በመሳት በላይታች እንዲለማዱ እጣ የደረሰው ምድብ የተማሪዎች አጠቃላይ ውጤት 1047፣ አማካዩ 23.26፣ መደበኛ ልይይት 8.66 እና ልይይት 75.05 ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩም በታች ላይ ሞዴል እንዲለማመዱ ዕጣ የደረሰው ምድብ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች አጠቃላይ ውጤት 1024፣ አማካይ 21.78፣ መደበኛ ልይይት 8.89 ልይይቱ ደግመ 75.05 መሆኑን ከተመዘገበው ውጤት ተረጋግጧል፡፡

በተጠኚ ምድቦች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር የሁለት ተማሪ መበላለጥ ስለሚታይ የቴ-ቴስት ዋጋን ለማስላት በያለው እንዳወቅ (2004፣ 282) ላይ ሁለተኛ ላይ ያለውን ፎርሙላ በመጠቀም የቲ-ቴስት ዋጋው ሲሰላ 0.81 ሲሆን በ90 የነፃነት ደረጃ፣ በ0.05 የጉልህነት ደረጃ የሠንጠረዡ ዋጋ 1.664.5 ነው፡፡ የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ 0.81 ከቲ-ሠንጠረዡ ዋጋ 1.6645 ጋር ሲነፃፀር የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ ያንሳል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው በሁለቱ ተጠኚ ምድቦች መካከል በቅድመ ልምምድ ፈተና የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡ ከዚህም ሃሳብ በመነሳት በሁለቱም ምድቦች መካከል ከልምምድ በፊት በአንብቦ የመረዳት ችሎታ የጎላ ልዩነት የላቸውም የሚል የድምዳሜ ሃሳብ ላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡

የሁለቱ ተጠኚ ምድቦች የቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት ጠቅለል ባለመለኩ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡** የቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤትን ጠቅለል ባለ መልኩ የሚያሳይ

| ፈተና | በላይታች የሚለማመደው ምድብ ውጤት | | | | | በታች ላይ የሚለማመድ ምድብ ውጤት | | | | | የቲ-ቴስት ዋጋ | የቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | n | x | $\bar{x}$ | $s_2$ | s | n | x | $\bar{x}$ | $s_2$ | s | | | |
| ቅድመ ልምምድ ፈተና | 45 | 1047 | 23.26 | 75.05 | 8.66 | 47 | 1024 | 21.78 | 79.13 | 8.89 | 0.81 | 1.6645 | የለም |

ከላይ ከቀረበው መረጃ በመነሳት ሁለቱም ምድቦች የተመረጡት በዕጣ ናሙና አመራረጥ በመሆኑ ከልምምድ በፊት የማንበብ ትምህርት በተመሳሳይ አቀራረብ የተማሩ ስለሆኑ በቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት በምድቦች መካከል የጎላ ልዩነት የለም፡፡

ይህም መሆኑ ወይም ልዩነት አለመኖሩ ለቀጣዩ ከልምምድ በኋላ የሚመጣውን ውጤት ለመወሰን እንቅፋት እንዳይፈጥር ያግዛል።

### 4.1.2 የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ትንተና

ተማሪዎች ከተለማመዱ በኋላ ተፈትነው ያመጡት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ 3፡** የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤትን የሚያሳይ

| በላይታች ሞዴል የተለማመዱ ተማሪዎች ውጤት | | በታችላይ ሞዴል የተለማመዱ ተማሪዎች ውጤት | |
|---|---|---|---|
| 1. 45 | 24.42 | 1.44 | 24. 26 |
| 2.42 | 25.33 | 2.40 | 25.17 |
| 3.40 | 26.45 | 3.35 | 26.25 |
| 4.44 | 27.27 | 4.32 | 27.32 |
| 5.37 | 28.36 | 5.30 | 28.12 |
| 6.40 | 29.27 | 6.34 | 29.20 |
| 7.41 | 30.29 | 7.35 | 30.29 |
| 8.33 | 31.40 | 8.32 | 31.27 |
| 9.38 | 32.25 | 9.36 | 32.13 |
| 10.30 | 33.39 | 10.40 | 33.21 |
| 11.42 | 34.31 | 11.37 | 34.16 |
| 12.39 | 35.20 | 12.26 | 35.17 |
| 13.44 | 36.22 | 13.41 | 36.12 |
| 14.43 | 37.19 | 14.33 | 37.20 |
| 15.28 | 38.26 | 15.25 | 38.12 |
| 16.44 | 39.27 | 16.30 | 39.15 |
| 17.35 | 40. 23 | 17.29 | 40.19 |
| 18.32 | 41.25 | 18.27 | 41.16 |
| 19.44 | 42.29 | 19.25 | 42.13 |
| 20.29 | 43.13 | 20.30 | 43.28 |
| 21.42 | 44.24 | 21.19 | 44.26 |
| 22.30 | 45.31 | 22.31 | 45.20 |
| 23. 34 | | 23. 18 | 46.30 |
| | | | 47.17 |
| x= 1509<br>$\overline{x}$=33.53<br>$s_2$= 99.25<br>s=9.96 | | x=1200<br>$\overline{x}$=25.53<br>s=73.33<br>s=8.56 | |

ከላይ ከቀረበው መረጃ ለመረዳት እንደተሞከረው በላይታች የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል የተለማመዱ ተማሪዎች አማካይ ውጤት እና ልይይት በታች ላይ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል ከተለማመዱ ምድብ ውጤት ይበልጣል፡፡ ሁለቱ ምድቦች ያስመዘገቡት ውጤት እንደሚከተለው ሲነፃፀር በላይታች የተለማመደው ምድብ አጠቃላይ ውጤት 1509፣ አማካይ 33.53፣ መደበኛ ልይይት 9.96፣ የናሙና ልይይት 99.25 ሲሆን፤ በታችላይ ሞዴል የተለማመደው ምድብ ደግሞ አጠቃላይ ውጤት 1200፣ አማካይ 25.53፣ መደበኛ ልይይት 8.56፣ የናሙና ልይይት 73.33 ነው፡፡ ይህንንም በቲ-ቴስት በማረጋገጥ የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ 4.16 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ፣ በ90 የነፃነት ደረጃ በባለ አንድ አቅጣጫ መላምት ከቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር የቲ-ቴስት ዋጋ 4.16 ከቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ 1.6645 ይበልጣል፡፡

የሁለቱ ምድቦች የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡** የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤትን ጠቅለል አድርጎ የሚያሳይ

| ፈተና | በላይታች የተለማመዱ ተማሪዎች ውጤት | | | | | በታች ላይ የተለማመዱ ተማሪዎች ውጤት | | | | | የቲ-ቴስት ዋጋ | የቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | $n_1$ | $x_1$ | $\overline{x}_1$ | $s_1^2$ | $s_1$ | $n_2$ | $x_2$ | $\overline{x}_2$ | $s^2_2$ | $s_2$ | | | |
| የድህረ ልምምድ ፈተና | 45 | 1509 | 33.53 | 99.25 | 9.96 | 47 | 1200 | 25.53 | 73.33 | 8.56 | 4.16 | 1.6645 | ታይቷል |

ከላይ ከቀረበው መረጃ በመነሳት በሁለቱ ምድቦች መካከል በድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ላይ የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ ከቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ የበለጠ ነው፡፡ ስለዚህ ለምርምሩ መላምት ሆኖ የቀረበው አልቦ መላምቱ ማለትም ከልምምድ በኋላ በሁለቱም ሞዴሎች ማንበብን በተማሩ ተማሪዎች መካከል አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት አይኖርም የሚለው ውድቅ ሆኖ በተለዋጩ ማንበብን በታች ላይ ሞዴል ከተማሩ ተማሪዎች በላይታች ሞዴል የተማሩት የተሻለና የጎላ ውጤት አስመዝግበዋል የሚለው ተለዋዋጩ መላምት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ማንበብን በላይታች ሞዴል ማስተማር በታችላይ ሞዴል ከማስተማር ይልቅ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ከተገኘው መረጃ ተረጋግጧል፡፡

የእያንዳንዱ ምድብ የቅድመና የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤታቸው በቲ-ቴስት ተሰልቶ እንደሚከተለው በሰንጠረዡ ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 5፡** የቅድመና የድህረ ፈተና ውጤትን የሚያሳይ

| ፈተና | በላይታች የተለማመዱ ተማሪዎች ውጤት | | | | በታች ላይ ሞዴል የተለማመዱ ተማሪዎች ውጤት | | | | የቲ-ቴስት ዋጋ | የቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | $n_1$ | $\overline{x}_1$ | $s_1^2$ | $s_1$ | $n_2$ | $\overline{x}_2$ | $s_2^2$ | $s_2$ | | | |
| ቅድመ ልምምድ | 45 | 23.26 | 75.05 | 8.66 | 47 | 21.78 | 79.13 | 8.89 | 0.81 | 1.6645 | የለም |
| የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት | 45 | 33.53 | 99.25 | 9.96 | 47 | 25.53 | 73.33 | 8.50 | 4.16 | 1.6645 | ታይቷል |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መገንዘብ እንደሚቻለው ምድቦቹ በየትኛው ፈተና የተሻለ ውጤት እንዳስመዘገቡ በንጽጽር መለየት ተችሏል፡፡ ይህንን መረጃ መሠረት በማድረግ በላይታች ሞዴል የተለማመዱ ተማሪዎች ለማነፃፀር አማካይ ውጤት 23.26 እና 33.53 በመቀናነስ፣ ልይይታቸው 75.05 እና 99.25ን በመያዝ የቲ-ቴስት ዋጋ ሲሰላ በ0.05 የጉልህነት ደረጃ፣ በ44 የነፃነት ደረጃ የቲ-ቴስት ዋጋ 7.78 ሲሆን የቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ 1.6775 ነው፡፡

በዚህም መሠረት የቲ-ቴስት ዋጋው ከቲ-ሠንጠረዡ ዋጋ የበለጠ ነው፡፡ ስለሆነም በላይታች ሞዴል የተማሩ ተማሪዎች በድህረ ልምምድ ፈተና ያመጡት ውጤት ልዩነት ጉልህ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ቀድሞ ከሚማሩት የማንበብ ማስተማሪያ ዘዴ ከሚማሩት ይልቅ አሁን በተለማመዱት ሞዴል መማራቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱ ተረጋግጧል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በታች ላይ ሞዴል የተማሩ ተማሪዎችን የቅድመ ልምምድና ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ልዩነት ለማነፃፀር አማካይ ውጤት 21.78 እና 25.53ን በመቀናነስ፣ ልይይታቸው 79.13 እና 73.33ን በመያዝ የቲ-ቴስት ዋጋ ሲሰላ 0.05 የጉልህነት ደረጃ፣ በ46 የነፃነት ደረጃ የቲ-ቴስት ዋጋ 3.03 ከቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ 1.6775 ጋር ሲነፃፀር የቲ-ቴስት ዋጋ ከቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ የበለጠ ነው፡፡ ልምምዱ ተማሪዎች ማንበብን ቀድመው ሲማሩት ከነበረው የበለጠ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በአጠቃላይ ከፈተና ውጤታቸው ለመረዳት እንደተሞከረው በሁለቱም ምድቦች በቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አልታየም፡፡ ነገር ግን ከልምምዱ በኋላ ባስመዘገቡት ውጤት ቲ-ቴስት ሲሰላና ከቲ-ሠንጠረዥ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በሁለቱ ምድቦች መካከል ጉልህ ልዩነት ታይቷል፡፡ ማለትም በላይታች ሞዴል የተማሩ ተማሪዎች በታች ላይ ሞዴል ከተማሩ ተማሪዎች የበለጠ ውጤት በድህረ ልምምድ ፈተናቸው አስመዝግበዋል፡፡ ከዚህም በመነሳት ተማሪዎች ማንበብን በታች ላይ ከሚማሩ ይልቅ በላይታች ቢማሩ ጥሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ይኖራቸዋል ከሚል ድምዳሜ ለመድረስ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የእያንዳንዱ ምድብ ቀድመ ልምምድ ፈተና ውጤታቸው ከድህረ ልምምድ ፈተና ውጤታቸው በቲ-ቴስት ዋጋቸው ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ የሁለቱም የድህረ ልምምድ ውጤት አሁን የተለማመዱት ልምምድ ከቀድሞው የማንበብ መማሪያ ስልት የተሻለ በመሆኑ የቲ-ቴስት ዋጋቸው ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ በልጦ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በሁለቱም ምድቦች የቀድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ሲነፃፀር ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡

## 4.2 ለተማሪዎች ከተሠራጨው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና

### 4.2.1 በክፍል አንድ የቀረቡ ጥያቄዎች ውጤት ትንተና

የጽሑፍ መጠይቁ የቀረበላቸው ተጠኚዎች ዳራዊ መረጃ ማለትም የተማሪዎች ፆታ፣ ዕድሜ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎች እንደሚከለተው በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 6፡** መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች ፆታ፣ ዕድሜ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋን የሚያሳይ

| ተ.ቁ | ምድብ | | | | ዕድሜ ክልል | | | ቋንቋ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ብዛት | 13-15 | 16 እና በላይ | ብዛት | አማርኛ | ጎፍኛ | ገዞኛ | ኦሪኛ | ሚሊኛ | ብዛት |
| 1 | ከላይታች መጠይቁን የሞሉ | 24 | 20 | 44 | 40 | 4 | 44 | 24 | 13 | 5 | 1 | 1 | 44 |
| 2 | ከታች ላይ መጠይቁን የሞሉ | 22 | 25 | 47 | 42 | 5 | 47 | 20 | 18 | 6 | 3 | - | 47 |
| | ድምር | 46 | 45 | 91 | 82 | 9 | 91 | 44 | 31 | 11 | 4 | 1 | 91 |

ከላይ የተቀመጠው መረጃ እንደሚያስረዳው በላይታች ሞዴል ከተለማመዱ ተማሪዎች መካከል 24 (54.54%) በታች ላይ ሞዴል ከተለማመዱት ደግሞ 22(46.80%) ወንዶች ናቸው፡፡

የቀሩት ከሁለቱ ምድቦች 45(49-45%)ቱ ሴቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እድሜያቸውን በተመለከተ በላይታች ከተለማመዱት 40(90.90%) ከ13-15 የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ 4(9.09%) እድሜያቸው 16 እና ከ16 በላይ እድሜ ክልል ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በተመለከተም በላይታች ከተለማመዱት 24(54.54%) በአማርኛ፣ 13(29.54%) በጎፍኛ፣ 5(11.36%) በገዞኛ፣ 1(2.27%) በማሊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ሲሆኑ በታችላይ ሞዴል ከተለማመዱ ተማሪዎች ውስጥ 20(42.55%) በአማርኛ፣ 18(38.29%) በጎፍኛ፣ 6(12.76%) በገዞኛ፣ 3(6.38%) በኦሪኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ መሆናቸውን ከሰጡት መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በላይ ታች ሞዴል እንዲለማመዱ እጣ የደረሳቸውም ሆኑ በታች ላይ እንዲለማመዱ ዕጣ በደረሳቸው ተማሪዎች መካከል አብዛኛዎቹ በተመሳሳይ እድሜ ክልል ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ደረጃም መረጃው እንደሚያሳየው አብዛኛዎቹ አፋቸውን የፈቱት በአማርኛ ቋንቋ ሲሆን የቀሩት ጥቂቶቹ አፋቸውን በተለያዩ ቋንቋዎች የፈቱ መሆናቸውን ከሰጡት መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህም በመነሳት በሁለቱም ምድቦች የሚገኙ ተማሪዎች በተቀራራቢ እድሜ ክልል ውስጥ መገኘታቸውና አብዛኛዎቹ አፋቸውን የፈቱት በአማርኛ ቋንቋ መሆናቸው በእድሜና በአፍ መፍቻ ቋንቋ መበላለጥ ተጽእኖ ምክንያት የሚመጣ የውጤት መበላለጥ የጎላ ልዩነት እንደማይኖር ከመረጃው ተረጋግጧል፡፡

ሌላው በላይ ታች ሞዴል የተለማመዱት አርባ አምስት ተማሪዎች ሲሆኑ የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉት ግን አርባአራት ተማሪዎች ናቸው፡፡ አንዱ ተማሪ ባጋጠመው ችግር ምክንያት የጽሑፍ መጠይቁን ሊሞላ አልቻለም፡፡

### 4.2.2 በክፍል ሁለት ተማሪዎች ልምምድ ከማድረጋቸው በፊት እየተማሩ ስላሉት የማንበብ ትምህርት አቀራረብ የተጠየቁትን አስተያየት የሚያሳይ

ተማሪዎች ልምምድ ከማድረጋቸው በፊት ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ መስማማት አለመስማማታቸውን ለማረጋገጥ ተሞክሯል፡፡ ለጥያቄዎቹም እንዲመርጡ የቀረቡላቸው ምርጫዎችም

ሀ. እስማማለሁ
ለ. በጣም እስማማለሁ
ሐ. አልስማማም
መ. በፍጹም አልስማማም የሚሉ ናቸው፡፡

**ሰንጠረዥ 7፡ ለተጠያቂዎች ስለ ቅድመ ልምምድ ያላቸውን ግንዛቤ የሚጠይቅ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | በ.እስማማለሁ | | አልስማማም | | በፍፁም አልስማማም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 2 | ከልምምድ በፊት መምህራችን በምንባቡ ርዕስ ዙሪያ በቂ የቅድመ እውቀት ከሌለን ከማንበብ ጊዜ እንቅፋት እንዳይሆንብን ከምንባቡ መልዕክት ውስጥ አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም ፍንጭ ይሰጡን ነበር፡፡ | 8 | 8.79 | 3 | 3.29 | 44 | 48.35 | 36 | 39.56 |
| 3 | ከልምምዱ በፊት ለምን እንደምናነብ፣ እንዴት እንደምናነበው ወስነን እንድናነብ መምህራችን ያበረታቱናል፡፡ | 6.9 | 6.59 | 2 | 2.19 | 56 | 61.53 | 27 | 29.67 |
| 4 | ከልምምዱ በፊት የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ዝግ ባለ ድምፅ ምንባቦችን በግላችን እንድናነብ ሁኔታዎችን ያመቻቹልን ነበር፡፡ | 10 | 11.98 | 6 | 6.59 | 39 | 42.85 | 36 | 39.56 |
| 7 | ከዚህ ቀደም መምህራችን ከመጽሐፋችን ውጭ ከጋዜጣዎች፣ ከመጽሔቶች፣ ወዘተ አንብበን ያገኘናቸውን ቁም ነገሮች በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችን እንድናነብና እንድንወያይ ይጋብዙናል፡፡ | 7 | 7.69 | 7 | 7.69 | 34 | 37.36 | 43 | 47.25 |
| 8 | ወላጆቻችሁ ከተለያዩ ጽሑፎች ስለተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች አንብበው እንዲወያዩ ያደርጉናል፡፡ | 1 | 1.09 | 6 | 6.59 | 59 | 64.83 | 25 | 27.47 |
| 12 | ከዚህ ቀደም ስለምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት አስቀድሞ ባይገመትም ስለ ርዕሱ የቀደመ እውቀት ባይቀሰቅሱም የማንበብ ፍላጎቴን አልቀነስም ነበር፡፡ | 9 | 9.89 | 5 | 5.49 | 38 | 41.75 | 39 | 42.85 |

ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎች በተመለከተ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ሃሳቦች ተጠቅሰዋል፡፡ ለምሳሌ ማንበብ ከቀድመ እውቀት ጋር መያያዝ እንዳለበት USAID (2003), Nuttal (1996), Goodman (1979) ማንበብ መጀመር ያለበት ከማንበብ በፊት በመተነበይና መላምት በመስጠት ያንን ለማጋገጥ መነበብ አለበት፡፡ ይህም መሆኑ ማንበብ የቀደመ እውቀት ላይ መመሥረቱ አንብቦ የመረዳት ችሎታን እንዲፋጠንና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ለምን አላማ እንደሚያነቡ እንዲወስኑ እንደሚያደርጓቸውም ምሁራኑ ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት የምንባቡን ርዕስ በማየት ምንምን ሃሳቦችን በምንባቡ ሊመጡ

እንደሚችሉ በመተንበይና በቀረቡላቸው የመነሻ ጥያቄዎች ግምታዊ መልስ በመስጠት የሰጡትን ግምት ለማጋገጥ ማንበባቸው እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው እንዲወስኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህንንም ሃሳብ መነሻ በማድረግ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሰንጠረዡ እንደምናየው አዎንታዊና አሉታዊ ምላሾችን ተማሪዎች ሰጥተዋል፡፡

ከልምምዱ በፊት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የቀደመ እውቀታችሁን ይቀሰቅሳሉ ተብለው ለተጠየቁት 2ኛ ጥያቄ 11 ተማሪዎች (12.08%) አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ 80(87.9%) አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ለ3ኛ ጥያቄ ከልምምዱ በፊት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከማንበባችሁ ለምን ዓላማና እንዴት ማንበብ እንዳለባችሁ እንድትወስኑ ያደርጋሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ 8(8.79%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት 83(91.20%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ከዚህ ቀደም የቋንቋ መምህራን የቀደመ እውቀት ባይቀሰቅስም የማንበብ ፍላጎቴ አልቀነስም ለሚለው የ12ኛ ጥያቄ 14(15.38%) አዎንታዊ ሲሰጡ የተቀሩት አብዛኛዎቹ 77(84.61%) አሉታዊ መልስ መስጠታቸው ከምልሳቸው ተረጋግጧል፡፡

አራተኛው ጥያቄን በተመለከተ የማንበብ ተግባር በግል የሚደረግ ጥረት መሆኑን Wallace (1992), Davis (1995) ገልጸዋል፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ መልክ ለቀረበላቸው ጥያቄ ጥቂቶቹ 16(17.58%) አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ አብዛኛዎቹ 75(82.41%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከመረጃው እንደሚንረደው ከልምምዱ በፊት ተማሪዎች ማንበብን በግላቸው እየተገበረ አልመሆናቸውን ነው፡፡ ስለዚህም ተማሪው ከልምምዱ በፊት በግሉ የጸሐፊውን ሃሳብ እንዲረዳና እንዲተረጉም መምህራን ስለሚያደርጓቸው የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤታቸው አናሳ መሆኑን ከመረጃው መረዳት ተችሏል፡፡

ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ በማህበራዊ ኑሮኣቸው የሚያጋጥሙ ችግሮችን በቀላሉ እንዲፈቱ ለማስቻልና አዳዲስ ሃሳቦችን ከተለያዩ ጽሑፎች አንብበው አግኝተው አግባባዊ በሆነ ቦታና ጊዜ እንደልባቸው እንዲጠቀሙ ለማስቻል መምህራንም ሆኑ ወላጆች በከፍተኛ ድርሻ አለባቸው፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከመጽሐፍ ውጭ የተለያዩ መጽሐፎችን፣ መጽሔቶችን፣ ጋዜጣዎችን አንብባችሁ ባገኛችሁት ቁም ነገር ላይ ከጓደኞቻችሁ ጋር እንድትወያዩ ያደረጋሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ጥቂቶቹ 14(15.38%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ አብዛኛዎቹ 77(84.61%) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ከልምምዱ በፊት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም ሆኑ ወላጆች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት

ችሎታ ከፍ ለማድረግ የማንበበ ፍላጎታቸውን ለመጨመር የሚያደርጉት ጥረት አነስተኛ መሆኑን ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከልምምድ በፊት ስለምንባብ ትምህርት አቀራረብ ሁኔታ በተጠየቁት ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ለጥያቄዎቹ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም ከልምምዱ በፊት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከማንበባቸው በፊት የተማሪዎችን ፍላጐት ለመቀስቀስ፣ አላማ ወስነው እንዲያነቡ ለማድረግ፣ በግላቸው እንዲያነቡ ለማበረታታት ጥረት እንደማያደርጉ እና በመጽሐፋቸው ውስጥ ካሉት ውጪ ከሌሎች ጽሑፎች እንዲያነቡ ወላጆችም ሆኑ መምህራን እንደማያበረታቱዋቸው ከምላሻቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህም በመሆኑ አሁን በቀረበላቸው መለማመጃ መልክ የማንበብ ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ ሁለቱም ምድቦች ከቅድመ ልምምድ ፈተና ውጤታቸው የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤታቸው የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ክፍል ሦስት በልምምድ ጊዜና ከልምምድ በኋላ ባሉ ተግባራት ላይ የቀረቡላቸው ጥያቄዎች ትንተና

በዚህ ክፍል ተማሪዎች እንዲለማመዱ የቀረበላቸውን ልምምድ ካጠናቀቁ በኋላ በምዕራፍ አንደ በዓላማ ስር በጥያቄ መልክ ለቀረቡ ዓላማዎች ምላሽ ለማግኘት የሚያስችሉ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ለልምምድ የቀረቡ መልመጃዎች ተማሪዎች እርስ በእርስ እንዲወያዩ፣ ከራሳቸው አካባቢ ጋር እያገናኙ አስተያየት በመስጠት እንዲረዳድ የሚያደርጓቸው፣ አዳዲስ ቃላትንና ሐረጋትን አውዳዊና ቀጥተኛ ፍተ እንዲሰጡ የሚጋብዛቸው ሰዋሰዋዊ ይዘቶችን እንዲሰረና አንብበው መረዳታቸውን እንዲያረጋግጡ አመቺ ሆነው መቅረባቸውን አስመልክተው ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች እንደሚከተለው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 8፡ ለልምምድ የቀረቡ የመልመጃ ጥያቄዎችና አተገባበራቸውን የሚያሳይ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ.እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | አልስማማም | | በፍፁም አልስማማም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 13 | ለልምምድ የቀረቡ የመልመጃ ጥያቄዎች ለውይይትና ለመረዳዳት አመቺ ሆነው የቀረቡ ስለሆኑ የመልመጃ ጥያቄዎችን እየተወያዩና እየተረዳዱ ለመሥራት ተችሏል | 62 | 68.13 | 23 | 25.27 | 6 | 6.59 | - | - |
| 14 | ለልምምድ የቀረቡ መልመጃዎች ለአዳዲስ ቃላትና ሐረጋት አውዳዊና ቀጥተኛ ፍቺ እንድንሰጥ የሚጋብዙ ስለሆኑ ምንባቡን በተለያዩ የአነባብ ስልት በመጠቀም ደጋግሜ ማንበቤ ለቃላትና ለሐረጋት አውዳዊ ፍችና ቀጥተኛ ፍች እንዲሰጥ አስችሎኛል፡፡ | 50 | 54.94 | 33 | 36.26 | 7 | 7.69 | 1 | 1.09 |
| 15 | ለልምምድ የቀረቡ መልመጃዎች በምንባቡ ዋና ሃሳብ ላይ እንድንወያይና የራሳችንን ሃሳብ እንድንሰጥ የሚጋብዙ ሆነው የቀረቡ ስለሆኑ የምንባቡን ዋና ሃሳብ ከግል ገጠመኝ ጋር በማዛመድ የግል አስተያየት ለመስጠት ጥረት አድርጊያለሁ፡፡ | 44 | 48.35 | 37 | 40.65 | 8 | 8.79 | 2 | 2.19 |
| 16 | ለልምምድ የቀረቡ መልመጃዎች የምንባቡን ዋና ሃሳብ ከራሳችን አካባቢ ጋር እያገናዘብን በራሳችን አገላለጽ ሃሳቡን አሳጥረን እንድንገልጽ ምቹ ሆነው ቀርበዋል፡፡ | 44 | 48.35 | 33 | 36.26 | 12 | 13.18 | 2 | 2.19 |
| 17 | ለልምምድ የቀረቡ መልመጃዎች ማንበባችንን ለማረጋገጥ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ስለዚህም ምንባቡን ካነበብኩ በኋላ ጥያቄዎችን በመሥራት ምን ያህል እንደተረዳሁ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ | 50 | 54.94 | 32 | 35.16 | 9 | 9.89 | - | - |
| 18 | ለልምምድ የቀረቡ መልመጃዎች ሰዋስዋዊ ይዘቶችን እንድሰራ አመቺ ሆነው ቀርበዋል፡፡ | 46 | 50.54 | 28 | 38.76 | 14 | 15.38 | 3 | 3.29 |

አንብቦ ለመረዳት ከምንባቡ ውስጥ የሚወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሊሆኑ የሚገባቸው ተማሪዎችን እርስ በእርስ እንዲረዳዱ የሚያደርጉ፣ የምንባቡን ሃሳቦች ግልጽ ለማድረግ ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እያገናኙ ለመመለስ የሚያስችሉ እና ጥሩ አንባቢ እንዲሆኑ

የሚያግዛቸው ሆነው መቅረብ እንዳለባቸው ይታመናል። ከዚህም በመነሳት ለልምምድ የቀረቡ የመልመጃ ጥያቄዎች ተማሪዎች ምን ያህል የምንባቡን ሃሳብ ከራሳቸውና ከአካባቢያቸው ሁኔታ ጋር እያገናዘቡ እንዲመልሱ እንዳደርጋቸው፣ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ምን ያህል እንዲወያዩ ተደርገው የቀረቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ለቀረቡላቸው ለ13ኛ ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 23(25.27%)ቱ እስማማለሁ ብለው የመለሱ ሲሆን 62(68.13%)ቱ በጣም እስማማለሁ ሲሉ የተቀሩት ጥቂቶቹ 6(6.59)ቱ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። በተመሳሳይ መልኩም መልመጃዎቹ በምንባቡ ዋና ሃሳብ ላይ ተማሪዎች ተወያይተው የግል አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ያደረጋቸው መሆን አለመሆኑን በጥያቄ ቁጥር 15 ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኛዎቹ 37(40.65%)ቱ እስማማለሁ ብለው ሲመልሱ 44(48.35%)ቱ በጣም እስማማለሁ ብለው መልሰዋል። የቀሩት ጥቂቶቹ 10 ተማሪዎች (10.98%)ቱ በሃሳቡ አለመስማማታቸውን ገልጸዋል። ከነዚህ ጋር በተያያዘ መልኩም በጥያቄ ቁጥር 16 ላይ የምንባቡን ዋና ሃሳብ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ሁኔታ ጋር እያገናዘቡ በራሳቸው አገላለጸ እንዲገልጹ ሁኔታዎች ተመቻችተው መልመጃዎች የቀረቡ መሆናቸውን 33 ተማሪዎች (36.26%) እስማማለሁ ሲሉ 44(48.35%) ተማሪ በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል። ከዚህም በመነሳት ለነዚህ ለጥያቄ ቁጥር 13፣ 15ና 16 ላይ ለቀረቡ ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከመለሱት አዎንታዊ ምላሽ የጥያቄዎቹ አቀራረብ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ፍላጎታቸውን የሚቀሰቅሱ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል።

ሌላው 14ኛው ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ 33 ተማሪዎች (36.26%) እስማማለሁ ብለው ሲመልሱ 50(54.94%)ቱ በጣም እስማማለሁ ብለው መልሰዋል። ቀሪዎቹ ጥቂት ተማሪዎች 8(9.89%)ቱ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም የሚያስረዳው ለልምምድ የቀረቡ የመልመጃ ጥያቄዎች ተማሪዎችን ከምንባቡ ውስጥ ለአዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍች እንዲያገኙ የተለያዩ የአነባብ ስልቶችን በመጠቀም ምንባቡን መልሰው መላልሰው እንዲያነቡ ያደረጋቸው መሆኑንና ለቃላቱና ለሀረጋቱ ቀጥተኛ ፍች ለመስጠት ሲሉ የተለያዩ የአነባብ ስልትን በመጠቀም ከመጸሐፋቸው ውጭ ከመዝገበ ቃል ፍች እንዲፈለጉ እንዳደረጋቸው ከሰጡት አዎንታዊ መልስ መመለሳቸው የቀረበላቸው የመልመጃ ጥያቄ የሰግስው ይዘቶችን ለመሥራት መመልሳቸው አመቺ ሆነው መቅረባቸውን መረዳት ተችሏል። በተጨማሪም 17ኛው ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች 32 (35.16%) እስማማለሁ ሲሉ 50 ተማሪዎች (54.94%) በጣም እስማማለሁ ብለው አዎንታዊ መልስ መልሰዋል። የቀሩትም ጥቂቶቹ ተማሪዎች 9(9.98%)

አልስማማም ብለው አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ለልምምድ የቀረቡላቸው የመልመጃ ጥያቄዎች ምንባቡን ማንበብ አለማንበባቸውንና ምን ያህል አንብበው እንደተረዱ እንዲያረጋግጡ የሚያስችሉ ሆነው የቀረቡ መሆናቸውን ከሰጡት ምላሽ ተረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ ለልምምድ የቀረበላቸው የመልመጃ አቀራረብ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ፍላጎት የሚጭምሩና ለአንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ከፍተኛ መሆን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ መሆናቸውን ከተማሪዎች ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በማንበብ ትምህርት ጊዜ እንግዳ (1992) Higgins (1985) እና Goodman (1970)ን ጠቅሰው ምንባቡ ከቀረበ በኋላ የማንበብ ዓላማን መወሰነ፣ የምንባቡን መልዕክት አሰቀድሞ መገመት፣ የተገመተውን ግምት ለማረጋገጥ ደጋግሞ አንብቦ የተገኘውን መልዕክት ቀደም ሲል ካለ እውቀትና ከተገመተ ግምት ጋር በማዛመድ መገምገምን የማያጠቃልል ተግባር መሆኑን እንዳለበት ገልጸዋል፡፡ ከዚህም መንደርደሪያ ሃሳብ በመነሳት ለተማሪዎች የቀረቡላቸው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ላይ ምን ያህሉ እንደተስማማና ምን ያህሉ ተማሪ በሃሳቡ እንዳልተስማሙ በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 9፡** ለልምምድ የቀረቡ ምንባቦች አቀራረብና ትግበራን የሚያሳይ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | በጣም እስማማለሁ | | አልስማማም | | በፍፁም አልስማማም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 1 | በማንበብ ትምህርት ጊዜ የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት ከራሳችን ገጠመኞች ጋር እያገናኘን እንድንገመገም የመወያያ ጥያቄዎች ቀርበውልን ነበር፡፡ | 33 | 36.26 | 33 | 36.26 | 23 | 25.27 | 2 | 2.19 |
| 6 | በማንበብ ጊዜ ከማንበባችን በፊት የገመትነውን ግምት እንድናረጋግጥና ቀጣይ ሊመጣ የሚችለውን እንድንተነብይ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረውልን ነበር፡፡ | 39 | 42.85 | 16 | 17.58 | 30 | 32.96 | 6 | 6.59 |
| 11 | የአንድ ምንባብ ፍሬ ሃሳብ በቀላሉ ለመረዳት አጠቃላይ መልዕክትን አስቀድመን ባንገምትም ፍሬ ሃሳቡን ከምንባቡ ረቂቅ አሀዶች አወቃቀር ተነስተን እንድንረዳው ሆኖ ቀርቦልናል፡፡ | 15 | 16.48 | 16 | 17.58 | 30 | 32.96 | 40 | 43.95 |

ከሠንጠረዡ መረጃ ለመረዳት እንደተሞከረው የማንበብ ትምህርቱ ምንባቡ ከቀረበላቸው በኋላ የምንባቡን ርዕስ በማየት የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እያገናኙ እንዲገምቱና እንዲገመግሙ የሚጋብዛቸው ጥያቄዎች በልምምዱ ወቅት መቅረቡን ለተጠየቁት ለ1ኛ ጥያቄ 33 ተማሪዎች (36.26%)ቱ እስማማለሁ በማለት አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ 23 ተማሪዎች ደግሞ (25.27%)ቱ አልስማማም ሲሉ 2(2.19%)ቱ በፍጹም አልስማማም ብለው መለሰዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በጥያቄ ቁጥር 6 ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ 16 ተማሪዎች (17.58%)ቱ እስማማለሁ ሲሉ 39 ተማሪዎች (42.85%)ቱ በጣም መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ የቀሩት 30 ተማሪዎች (32.96%)ቱ አልስማማም ብለው ሲመልሱ 6(6.59%)ቱ በፍጹም አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ከነዚህም ምላሾች ለመረዳት እንደተሞከረው በአዎንታዊና በአሉታዊ የተጠጋጉ (የተቀራረቡ) ምላሾች ሊመዘገቡ የቻሉበት ምክንያት በታችላይ ለሚማሩ ተማሪዎች በቀረበላቸው መልመጃ የቀደመ እውቀትን የሚጠይቁና የሚመጣውን እንዲተነብዩ የሚጋብዛቸው ጥያቄ በመቅረቡ በተራ ቁጥር 1 እና 6 ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች በሀሳቡ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አለመስማማታቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል የአንድን ምንባብ ፍሬ ሃሳብ በቀላሉ ለመረዳት አጠቃላይ መልዕክቱን ከመገመትና ከመተንበይ ምንባቡን አንብቦ ከምንባቡ ረቂቅ አሀዶች አወቃቀር በመነሳት ዋናውን ሃሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ ለሚለው ሃሳብ ለጥያቄ ቁጥር አሥራ አንድ 16 ተማሪዎች (17.58) እስማማለሁ ብለው ሲመልሱ 15(16.48%)ቱ በጣም መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ የቀሩትም 30 ተማሪዎች (32.96%) አለመስማማታቸውን ሲያመለክቱ 40(43.95%)ቱ በፍጹም አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ከዚህም ምላሽ ለመረዳት እንደተሞከረው የአንድን ምንባብ አጠቃላይ መልዕክት ከማንበብ በፊት ሳይገምቱ የምንባቡን ረቂቅ አሀዶችን አወቃቀር አንብቦ ለመረዳት መሞከር የአንድን ምንባብ መልዕክት በፍጥነት አንብቦ ለመረዳት እንደማያስችል አብዛኛው ተማሪ ከሰጡት አሉታዊ ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡

በማንበብ ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች ወደ ማንበቡ ተግባር ከመግባታቸው በፊት ምን? ለምን? እና እንዴት? ማንበብ እንደሚገባቸው መወሰን እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡ ይህንንም በተመለከተ ለተማሪዎች የሚከተሉት ጥያቄዎች ቀርበው የመለሱት መልስ በዝርዝር በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 10፡ ዓላማን ወስኖ ማንበብ ላይ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | በጣም እስማማለሁ | | አልሰማማም | | በፍጹም አልስማማም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 5 | ከማንበቤ በፊት ለምንና እንዴት ማንበብ እንዳለብኝ መወሰኔ የማንበብ ፍላጎቴን ቀስቅሶልኛል፡፡ | 33 | 36.26 | 40 | 43.95 | 17 | 18.68 | 1 | 1.09 |
| 9 | ከማስታወቂያና ከሌሎች ጽሑፎች የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ ለማግኘትና ለመረዳት የምናደርገው የአነባብ ስልት ተመሳሳይ አለመሆኑን ከልምምዱ ተረድቻለሁ፡፡ | 28 | 30.76 | 42 | 46.15 | 10 | 10.98 | 11 | 12.08 |
| 10 | የምናነበው አንብቦ የመረዳት ክሂላችንን ለማዳበር ብቻ ሳይሆን በትምህርታችን ጥሩ ውጤት ለማምጣትና ለማህበራዊ ኑሮአችን ለመጠቀም ጭምር መሆኑን በልምምዱ ወቅት ተረድቻለሁ፡፡ | 26 | 28.57 | 46 | 50.64 | 11 | 12.08 | 8 | 8.79 |

ማንኛውንም ጽሑፍ ከማንባባችን በፊት ለምን እንደምናነብ አውቀን ማንበብ እንዳለብንና ዓላማችንን ማወቃችን እንዴት ማንበብ እንዳለብን እንደሚመራን Wallace (1992)፣ USAID (2003) ምንባቡን የሚናነበው ለጥንቃቄ፣ ለመደሰት፣ አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅ፣ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የሚገጥሙንን ማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት ነው? የሚሉትን ዓላማዎች አስቀድሞ ማወቁ አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ እነዚህንም መሠረት ሃሳቦች መሠረት ተደርገው ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ለ5ኛው ጥያቄ 33 ተማሪዎች (36.26%) እስማማለሁ ሲሉ 40(43.95%) በጣም መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ሌሎች 17 ተማሪዎች (18.68%)ቱ አለመስማማታቸውን ያመለከቱ ሲሆኑ 1 ተማሪ(1.09%) በፍፁም አለመስማማቱትን ገልጿል፡፡ ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት ለምንና እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ወስነው ማንበባቸው የማንበቡን ተግባር በጉጉት እንዲተገብሩ እንደሚያደርጋቸው ከሰጡት አዎንታዊ ምላሽ ማረጋገጥ

ተችሏል። በተመሳሳይ መልኩ በ10ኛው ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ 26 ተማሪዎች (28.57%)ቱ መስማማታቸውን ሲገልጹ 46(50.54%) በጣም መስማማታቸውን ገልጸዋል። የቀሩት 11 ተማሪዎች (12.08%) አለመስማማታረቸውን ሲያመለክቱ 8ቱ ደግሞ (18.79%) በፍፁም አለመስማማታቸውን ገልጸዋል። ከዚህም መረዳት የሚቻለው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ምንባብ የሚነበበው አንብቦ የመረዳት ክሂልን ለማዳበር ብቻ ሳይሆን በትምህርታቸውም ጥሩ ውጤት ለማምጣትና የሚገጥሟቸውን ማህበራዊ ችግሮችን በቀላሉ ለመፍታት እንዲያግዛቸው ጭምር መሆኑን ከሰጡት አዎንታዊ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል።

ሌላው ደግሞ ከማስታወቂያ የማስታወቂያውን ሃሳብ አንብቦ መረዳትና ከሌሎች ጽሑፎች ፍሬ ሃሳብን አንብቦ ለመረዳት የሚደረገው የአነባብ ስልት ተመሳሳይ አለመሆኑን ለ9ኛ ጥያቄ 28(30.76%)ቱ መስማማታቸውን ሲገልጹ 42(46.15%)ቱ በጣም መስማማታቸውን ገልጸዋል። 10(10.98%) አለመስማማተቸውን ሲያመለክቱ 11(12.08%)ቱ በፍጹም አለመስማማታቸውን አመልክተዋል። ከዚህም በመሳት ከማስታወቂያና ከሌሎች ጽሑፎች ፍሬ ነገሩን ለመረዳት የሚተገበረው የአነባብ ስልት ተመሳሳይ እንዳልሆነ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከሰጡት አዎንታዊ መልስ ማረጋገጥ ተችሏል።

ልምምድ ካደረጉ በኋላ ከልምምዱ ምን እውቀት እንዳገኙና ያገኙት እውቀት ለወደፊቱ ምን ያህል እንደሚጠቅማቸው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መልስ በሚከተለው ሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ 11፡ በላይታች ሞዴል ልምምድ በማድረጋቸው ምን ግንዛቤ እንደጨበጡ የሚያሳይ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | በጣም እስማማለሁ | | አልስማማም | | በፍጹም አልስማማም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 19 | ልምምድ ማድረጌ በግል የተለያዩ ጽሑፎችን ከማንበቤ በፊት ስለምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት እንዲገምት፣ የማንበብ ስልቶችን እንድወስን፣ በማንበብ ጊዜ ግምቴ ትክክል መሆን አለመሆኑን እንዳረጋግጥ፣ ካነበብኩት በኋላ የተረዳሁትን ነገር ከራሴ ገጠመኝ ጋር በማገናኘት እንድረዳ አስችሎኛል፡፡ | 28 | 63.63 | 13 | 29.54 | 3 | 6.8 | | |
| 20 | በልምምዱ ያገኘሁት ግንዛቤና እውቀት ለወደፊቱ ተግባራዊ አደርጋለሁ፡፡ | 20 | 45.45 | 17 | 38.63 | 5 | 11.36 | 2 | 4.54 |
| 21 | በላይታች ሞዴል ልምምድ ማድረጌ ለወደፊቱ ጥሩ ልምድ አስጨብጦኛል፡፡ | 8 | 18.18 | 32 | 72.72 | 4 | 9.09 | | |

በተዘጋጀላቸው የልምምድ መልመጃዎች ልምምድ ማድረጋቸውና በላይታች ሞዴል ማንበብን መማራቸው ወደፊት በግላቸው ምንባብ ከማንበባቸው በፊት ስለምንባቡ መልዕክት እንዲገምቱ፣ ለምንና እንዴት ምንባቡን ማንበብ እንዳለባቸው አስቀድመው እንዲወስኑ ግንዛቤ ማስጨበጡንና ከልምምዱ ያገኙትንም ግንዛቤ ለወደፊቱ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ በቁጥር 19 ላይ ለቀረቡላቸው ሃሳብ 28 ተማሪዎች (63.63%) በሃሳቡ መስማማታቸውን ሲገልጹ 13(29.54%)ቱ በጣም መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ የቀሩት 3 ተማሪዎች (6.8%)ቱ ብቻ በሃሳቡ አለመስማማታቸውን ከሰጡት አሉታዊ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በላይታች ሞዴል ልምምድ ማድረጋቸው ተማሪዎችን ከማንበባቸው በፊት ስለሚያነቡት ነገር እንዲገምቱና እንዲተነብዩ ማድረጉንና ለምንና እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ወስነው ማንበብ የገመቱትንም ግምትና የተነበዩት ትንቢያ ትክክል መሆን አለመሆኑን እያረጋገጡ እንዲያነቡ ማስቻሉን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከሰጡት አዎንታዊ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለ20ኛው ጥያቄ 20 ተማሪዎች (45.45%)ቱ በሃሳቡ መስማማታቸውን ሲገልጹ 17(38.63%) በሃሳቡ በጣም መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ከቀሩት 5 ተማሪዎች (11.36%) አለመስማማታቸውን ሲያመለክቱ 2(4.54%) ተማሪዎች በሃሳቡ በፍጹም አለመስማማታቸውን

ገልጸዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ከልምምዱ ያገኙትን እውቀትና ግንዛቤ ለወደፊቱ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከሰጡት አዎንታዊ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሌላው በላይታች ሞዴል ማንበብን መለማመዳቸው ጥሩ ልምድ እንደስጨበጣቸውና እንዳላስጨበጧቸው ለተጠየቁት ለ21ኛ ጥያቄ 8 ተማሪዎች (18.18%) መስማማታቸውን ሲገልጹ፤ 32 ተማሪዎች (72.72%)ቱ በጣም መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ በዚህም ሃሳብ አብዛኛው ተማሪ በዚህ ሞዴል ልምምድ ማድረጋቸው ጥሩ ልምድ እንዳስጨበጣቸው ከሰጡት አዎንታዊ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ጠቅለል ባለመልኩም በላይታች ሞዴል አቀራረብ ላይ ተጨማሪ አስተያየት እንዲሰጡ ለቀረበላቸው 22ኛው ጥያቄ አብዛኛው ተማሪ የትምህርቱን አቀራረብ በጣም እንዲወደዱትና በዚህ መልኩ ቢማሩ ጥሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ሊያዳብሩ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ ለመውደዳቸውም ምክንያት ያደረጉት ነጥቦች ከዚህ ቀደም የማንበብ ትምህርትን የሚንማረው ፈቃደኛ የሆኑ የተወሰኑ ተማሪዎች እንዲያነቡ ተደርጎና መምህሩ ሲያነቡ ሌሎቻችን በማድመጥ የምንማር ሲሆን በልምምዱ ወቅት ግን ለየግላቸው እንዲያነቡ መደረጉ የምንባቡን ሃሳብ በሚገባን መልኩ አገናዝበን እንዳንረዳ አስችሎናል፡፡ ሌላው ከማንባባችን በፊትና በምንባብ ጊዜ በመሐል የቀረቡ ጥያቄዎች በምንባብ ውስጥ ሊወጡ የሚችሉ ነጥቦችን መገመታችን ግምታችን ትክክል መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ስንል ምንባቡን በጉጉት እንድናነብ አድርጎናል፡፡ ስለዚህም ማንበብን በዚህ መልኩ ለወደፊቱ ቢማሩም ጥሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንደሚኖራቸው እርግጠኛ መሆናቸውን ከሰጡት ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ እነዚህን የ19ኛ እና የ20ኛ ጥያቄዎች በታችላይ ሞዴል ለተለማመዱ ተማሪዎች ቀርበው የሰጡት መልስ እንደሚከተለው በጠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 12፡ በታችላይ ሞዴል ልምምድ በማድረጋቸው ምን ግንዛቤ እንደጨበጡ የሚያሳይ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የስምምነት ምርጫዎች | | | | ያለመስማማት ምርጫዎች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | በጣም እስማማለሁ | | አልስማማም | | በፍጹም አልስማማም | |
| | | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| 19 | ልምምድ ማደረጌ የተለያዩ ጽሑፎችን ከማንበቤ በፊት ስለምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት እንዲገምቱ፣ የማንበብ ስልቶችን እንዲወስን፣ በማንበብ ጊዜ ግምቴ ትክክል መሆን አለመሆኑን እንዳረጋግጥ፣ ካነበብኩ በኋላ የተረዳሁትን ነገር ከራሴ ገጠመኝ ጋር በማገናኘት እንድረዳ አስችሎኛል፡፡ | 10 | 21.27 | 9 | 19.14 | 16 | 34.04 | 12 | 25.53 |
| 20 | በልምምዱ ያገኘሁትን ግንዛቤና እውቀት ለወደፊቱ ተግባራዊ አድርጋለሁ | 15 | 31.91 | 10 | 21.27 | 18 | 38.29 | 4 | 8.51 |
| 21 | በታችላይ ሞዴል ልምምድ ማድረጌ ለወደፊቱ ጥሩ ልምድ አስጨብጦኛል፡፡ | 16 | 34.04 | 13 | 27.65 | 10 | 21.27 | 8 | 17.02 |

ተማሪዎች በቀረበላቸው ልምምድ አቀራረብ መሠረት ልምምድ ማድረጋቸው የማንበብን ተግባር በግላቸው እንዲተገብሩ እንዳደረጋቸውና ካነበቡ በኋላ የሚመጡ ጥያቄዎችን ከግል ገጠመኛቸው ጋር እያገናኙ እንዲመልሱ ያስቻላቸው መሆኑን በ19ኛ በቀረበላቸው ጥያቄ 10 ተማሪዎች (21.17%) እስማማለሁ ብለው ሲመልሱ 9(19.14%)ቱ በጣም መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ የቀሩ 16(34.04%)ቱ አለመስማማታቸውን ሲገልጹ 12(25.53%) በፈጹም አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ከዚህም የሚገረዳው በታችላይ ሞዴል ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት ስለምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት መገመትና ትንበያ መስጠትን የማይጠይቅ መሆኑን፣ የምንባቡን መልዕክት የምንባቡን ጥቃቅን አሀዶች በማንበብ መረዳት እንደሚቻልና ከጥቃቅን አሀዶች ተነስተው የምንባቡን ሃሳብ መረዳት አለመረዳታቸውን ለማረጋገጥ መልመጃዎች ሊቀርቡ እንደሚገባ USAID (2003)፣ ግሩም (2003) Grabe and Stoller (2005) እና Anderson (1999)ን በመጥቀስ ገልጸዋል፡፡

ስለዚህ ለተማሪዎች በታችላይ እንዲለማመዱ የቀረበውም በዚህ መልኩ የቀረበ ስለሆነ ከማንበባቸው በፊት ስለምነባቡ አጠቃላይ ሃሳብ እንዲገምቱ ተደርጎ ካለመቅረቡ የተነሳ ልምምዱ ምንባቦችን በግላቸው እንዲያነቡ መጋበዛቸው ጥሩ ሆኖ እንዲገምቱና የገመቱትን

ግምት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሲሉ ምንባቡን በጉጉት እንዲያነቡ ስለማይጋብዛቸው ለ19ኛው ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከመለሱት አሉታዊ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሌላው ደግሞ ለ20ኛው ጥያቄ 15(13.19%)ቱ ተማሪዎች በሃሳቡ መስማማታቸውን ሲገልጹ 10(21.27%)ቱ በሃሳቡ በጣም መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ የቀረትም 18(38.29%)ቱ አለመስማማታቸውን ሲያመለክቱ 4 ተማሪዎተ (8.51%)ቱ በሃሳቡ በፍጹም አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህም መልሳቸው የሚያስረዳው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በሰጡት አዎንታዊ መልስ በመነሳት ተማሪዎች በልምምድ ያገኙትን ግንዛቤና እውቀት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩም በታችላይ ሞዴል ማንበብን መለማመዳቸውን በተመለተ ለቀረበላቸው 21ኛ ጥያቄ 16(34.04%)ቱ መስማማታቸውን ሲገልጹ 13(27.65%)ቱ በጣም መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ 10(21.27%)ቱ አለመስማማታቸውን ሲያመለክቱ 8 ተማሪዎች በፍጹም አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ከምላሻቸውም መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች  በሃሳቡ ተስማምተው አዎንታዊ ምላሽ ስለሰጡ በታችላይ ሞዴል መለማመዳቸው ለወደፊቱ ጥሩ ልምድ እንዳስጨበጣቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሌላው በታችላይ ሞዴል አቀራረብ ላይ ተጨማሪ አስተያየት እንዲሰጡ ለተጠየቁት ጥያቄ አቀራረቡ ቀደም ሲል እየተማሩ ከነበሩት አቀራረብ የልምምዱ አቀራረብ ምንባቦችን በግላችን አንብበን የምንባቡን ሃሳብ ከራሳችን ገጠመኝ ጋር እያገናዘብን እንድንረዳ ተደርጎ የቀረበ ስለሆነ አቀራረቡ ጥሩ መሆኑን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከሰጡት አስተያየት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 4.3 ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች  ትንተና

ምልከታ ለዚህ ጥናት በፈተናና በጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን ለማጠናከር እና በዓላማ ሥር በጥያቄ መልክ ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት አጋዥ ሆኖ እንደሚያገለግል በምዕራፍ ሦስት ሥር ተገልጿል፡፡ በዚህም መሠረት ተማሪዎች ከልምምድ በፊት የማንበብ ትምህርት እንዴት እየተማሩ እንዳሉ ለማረጋገጥ ልምምድ ከመጀመራቸው በፊት የምልከታውን ዓላማ የክፍል ደረጃውን አማርኛ ቋንቋን ለምታስተምረው መምህርት በመግለጽ በሁለቱም ለልምምድ ዕጣ በደረሳቸው በእያንዳንዱ ክፍል ሦስት ሦስት ቀን በመግባት ምልከታው ተካሄዷል፡፡ በመቀጠለም በልምምዱ ወቅት ለልምምድ የቀረበላቸው አቀራረብ ምን ያህል አሳታፊ ሆኖ እንደቀረበላቸው በየትኛው አቀራረብ የቀረበላቸው የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል ተማሪዎች በፍላጎት እንዲለማመዱ እንዳደረጋቸው ለመለየት እና ከልምምዱ በፊት የማንበብ ትምህርቱን ሲማሩ ከነበራቸው ተሳትፎ ጋር በማነፃፀር የድምዳሜ ሃሳብ ለመስጠት

እንዲያስችል በልምምድ ወቅትም ምልከታ ተደርጐ የተገኙ መረጃዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 4.3.1 ከልምምድ በፊት ከተደረገ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

ምልከታው 29/01/2010 ዓ.ም እስከ 3/2/2010 ዓ.ም ድረስ በሁለቱም ክፍል በመግባት የታዩ ክንውኖች በአጭሩ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

- መምህርቷ "መስህቦቻችን" በሚለው ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ለማስተማር ወደ ምንባቡ ከመግባቷ በፊት ስለቃላት ጥናት በመጽሐፉ ላይ ያለውን ካነበበችላቸው በኂላ ከምንባቡ የወጡ ቃላትን በመነጣጠል እና በማጣመር አስነበበች፡፡ የቅድመ ማንበብ ጥያቄዎችን ጠይቀው ተማሪዎች እንዲወያዩ ጊዜ ሳይሰጧቸው ጊዜ የለም በማለት የምንባቡን አንቀጽ ፍቃደኛ ለሆኑ ተማሪዎች እና አንዳንድ ለመረጧቸው ተማሪዎች እንዲያነቡ ከፋፍለው ትእዛዝ ሰጡ፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲያነቡ የሚፈጥሩትን የቃላትና ሐረጋት አጠራር ስህተት ሌሎች ተማሪዎች እያረሟቸው አዳመጧቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩም መምህርቷ ድምጿን ከፍ አድርጋ ስታነብ ተማሪዎቹ በማድመጥ የማንበብ ትምህርቱን ሲማሩ ቆይተው አንብቦ የመረዳት ጥያቄውን ሳይሰሩና ከምንባቡ ምን እንደተረዱ ሳታረጋግጥ ጊዜው አልቆ ከክፍል ወጣች፡፡
- በቀጣዩም ቀን ምንባቡ በመምህርቷ ከፍ ያለ ድምፅ ከተነበበ በኂላ አንብቦ የመረዳት መልመጃ ጥያቄዎችን በቃል ከሰሩ በኂላ እንዲጽፉ ታዘዙ፡፡ በመቀጠልም የቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ምንባቡ በድጋሚ በአንድ ተማሪ ከፍ ያለ ድምፅ ተነበበ፡፡ ተማሪዎቹም ለቃላቱ አውዳዊ ፍቺ ሰጥተው ታርመላቸው፡፡ ለከበዳቸው ጥያቄዎችም መልሶቻቸውን መምህርቷ በመስራት ቀጣዩን የመልመጃ ጥያቄ ቤት እንዲሰሩ ተሰጣቸውና ተለያዩ፡፡
- በሦስተኛውም ቀን ያለፈውን ትምህርት እንዲያስታውሱ ካደረጉ በኂላ የቤት ስራቸውን አረሙ፡፡ መልሶቻቸውንም በጥቁር ሰሌዳ ጽፈው ማስተካከያ እንዲወስዱ ተደረገ፡፡ ከዚያም ቀጣዩን ጥያቄ ምንባቡን መሠረት አድርገው እንዲሰሩ ምንባቡ ተነቦላቸው ጥያቄውን ሰሩ፡፡

በዚህ ምልከታ ወቅት በአላማ ስር ለቀረበው ሦስተኛውንም ጥያቄ ለመመለስ እንዲያስችል ከልምምድ በኂላ የሚመጣ የውጤት ለውጥ ካለ ለውጡ በምን ምክንያት እንደመጣ ለመረዳትና

የተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቁ ከልምምድ በፊት የማንበብ ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ተጠይቀው ከመለሱት መልስ ጋር ተመሳሳይ የሆነ መረጃን ለማግኘት ተችሏል፡፡

❖ በቅድመ ምልከታ የተገኙ ነጥቦች፡-

- ተማሪዎች ከቅድመ ልምምድ በፊት የማንበብ ትምህርት በግል በማንበብ ሳይሆን ሌሎች ሲያነቡላቸው በማድመጥ በመማራቸው ይህም የአንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ውጤት ከፍ እንዳይል እንዳደረገው መረዳት ተችሏል፡፡
- ተማሪዎች በጉጉት እንዲያነቡ ቅድመ ማንበብ ጥያቄዎች ቢቀርቡም ተማሪዎች እንዲወያዩ ጊዜ አለመስጠታቸው ይህም ተማሪዎችን የገመቱትንና የተነበዩትን መልስ ለማረጋገጥ ሲሉ በጉጉት ምንባቦቹን እንዲያነቡ አለማድረጉን በምልከታው ተረጋግጧል፡፡
- የማንበብ ተግባር የተማሪውን የማንበብ ፍላጐት መምህሩ በመቀስቀስ በግል ፈልጉ እንዲያነብ ማነሳሳት ሲገባ አንዳንድ በፍላጐት ያነበቡ ተማሪዎች ብዙም የቃላትና የሐረጋት አጠራር ስህተት ያልፈጠሩ ሲሆኑ ያለፍላጐታቸው በመምህርቷ ትእዛዝ ያነበቡ ተማሪዎች ግን ብዙ ስህተቶችን ሲፈጥሩ ተማሪዎቹ እያረሟቸው በመሳቀቅ ማንበባቸውን መመልከት ተችሏል፡፡

ከላይ የቀረቡትን ተግባራት ማለትም አንዳንድ ተማሪዎች እንዲያነቡና ሌሎች እንዲያዳምጡ ማድረጋቸው ለሁሉም ተማሪ መጽሐፍ ባለመኖሩ መሆኑን፣ ቅድመ ማንበብ ጥያቄዎችን ለመስራት የጊዜ እጥረት መኖሩን መምህርቷ በየመሐሉ ገልፃለች፡፡ ስለዚህ ለምን በዚህ መልኩ እንደምታስተምር ምክንያቶቿን ከምትናገረው ንግግር መረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን እነዚህን ምክንያቶች መቅረፍ የሚችሉ መሆናቸውን በመፍትሄ ሃሳብ ላይ ተገልጿል፡፡

### 4.3.2 በልምምድ ወቅት ከተካሄደ የክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

ወደ ልምምዱ ከመገባቱ በፊት በሁለቱም ምድብ መምህራን Davis (1995) "ማንበብ ግላዊና የአእምሮ ግንዛቤ ሂደት ነው" ብለው የገለፁትን መሠረት በማድረግ መምህራኑም የማንበቡን ትምህርት ተማሪዎች በግላቸው እያነበቡ ፀሐፊው ምን ማለት እንደፈለገ በአእምሮአቸው እያብሰለሰሉ እንዲረዱ ማድረግ እንዳለባቸው፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ Nuttal (1982) "ማንበብ ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት ክሂሉን ማዳበር ብቻ ሳይሆን የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር የሚረዱ ክሂል ነው፡፡" ያሉትንም አገላለጽ መሠረት በማድረግ ለመምህራኑ ተማሪዎችን በግላቸው እንዲያነቡ ማድረግ አንደኛ የማንበብ ክሂላቸው እንዲያዳብሩ እንደሚያደርግ፤ ሁለተኛ የፀሐፊዎችን የቋንቋ አጠቃቀም በማየት የቋንቋ አጠቃቀም

ችሎታቸውን ከፍ ለማድረግ እንደሚቻል ተገልፆላቸዋል። ይህ ሳይሆን ተማሪዎችን የማንበብ ትምህርትን አንዳንድ ተማሪዎች ሲያነቡና መምህራን ሲያነቡ እንዲያዳምጡ እና ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ እያደረግን የምናስተምር ከሆነ በማንበብ ክፍለ ጊዜ ማድመጥን እያስተማርን መሆኑ መዘንጋት የለበትም። በማንበብ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች እንዲያነቡ የቀረበላቸውንም ምንባቦች ሆነ በመምህራኑ እንዲያነቡ የታዘዙ ምንባቦችን በግላቸው እንዲያነቡ ተደርጎ ማስተማር እንዳለባቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሃሳብ ተሰጣቸው።

በሌላ በኩል በላይታች ሞዴል የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ምንባቡ ከመነበቡ በፊት ከቀደመ እውቀታቸው ተነስተው የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት ምን ሊሆን እንደሚችልና ምን ምን ዝርዝር ጉዳዮችን በስሩ ሊይዝ እንደሚችል፣ የአንዳንድ አዳዲስ ቃላትና ሐረጋት ፍቺ እንዲገምቱ፣ ሊመጣ የሚችለውን መልዕክት እንዲተነብዩ መደረግ እንዳለበት፤ ይህንንም ማድረጉ ተማሪዎች የገመቱትን ግምት እና የተነበዩትን ትንበያ ትክክለኝነት ለማረጋገጥ ሲሉ ምንባቡን በጉጉት እንዲያነቡ ስለሚያደርጋቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዲፋጠን እንደሚያደርግ USAID (2003)፣ ግሩም (2003)፣ Cerell (1988)፣ Gove (1983) በመጥቀስ፣ እንግዳ (1992)፣ Higgin (1984)፣ Goodman (1970) በመጥቀስ ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን ሃሳብ ገልፀዋል። ይህንንም መሠረት በማድረግ በላይታች የምታስተምረው መምህርት የማንበብ ትምህርቱን ስታቀርብ ከማንበባቸው በፊት ስለምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር እያገናዘቡ እንዲመልሱና ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ተወያይተው ግምታዊ መልስ እንዲሰጡ ካደረጉ በኋላ በየግላቸው ምንባቡን ዝግ ባለ ድምጽ እንዲያነቡ በማድረግ እና በየመሐሉ የቀረቡ ጥያቄዎችን የማንበቡን ተግባር በማስቆም ጥያቄዎችን እያቀረቡ የገመቱት ግምት ምን ያህል ትክክለኛ እንደሆነና እንዳልሆነ ማረጋገጣቸውን፤ ቀጣይ ሊመጣ የሚችለውን ሃሳብ እንዲተነብዩ እያደረጉ ምንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ምንባቡን በአሰሳና በፍጥነት እያነበቡ መልስ እንዲሰጡ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የማንበብ ትምህርቱም እንዲያስተምሩ ሰፋ ያለ ውይይትና ገለፃ ተደርጐላቸዋል።

በተመሳሳይ መልኩም በታች ላይ ሞዴል የማንበብ ትምህርት አቀራረብ ሊሆን የሚገባው ተማሪዎቹ አንብበው እንዲረዱ በአንባቢው የቀደመ እውቀትና በጽሑፍ መካከል ጣልቃ ገብነት መኖር እንደሌለበት፤ ተማሪዎቹ የምንባቡን ሃሳብ መረዳት ያለባቸው የጽሑፍ ማጠቃለያ መልዕክት ከማንበባቸው በፊት ገምተው ሳይሆን የጽሑፉን ጥቃቅን ቅንጣቶች በመጠቀም የጽሑፉን መልዕክት መረዳት እንዳለባቸው፤ የጽሑፉን መልዕክት ለመረዳት ከድምፆች

አጠቃቀም ጀምሮ፣ ቃላት፣ ሐረጋት፣ ዐረፍተ ነገሮችን እየተገነዘቡ ከሄዱ በኋላ አጠቃላይ መልዕክቱን መረዳት እንደሚችሉ USAID (2003)፣ ግሩም (2003)፣ Garbe and Stoller (2005) እና Anderson (1999)ን ጠቅሰው ገልፀዋል፡፡ እነዚህም የመነሻ ሃሳቦች መሠረት በማድረግ በታችላይ ሞዴል ተማሪዎችን ለምታለማምዳቸው መምህርት ምንባቡን ለምን አላማ እንደሚያነቡ ከጠየቁና መልሶቻቸውን ከተቀበሉ በኋላ ቀጥታ ምንባቡን በየግላቸው ዝግ ባለ ድምፅ አንብበው የምንባቡን መልእክት እንዲረዱ እንዲያደርጉ፤ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ምንባቡን የተለያዩ የአነባብ ስልቶችን እየተጠቀሙ ደጋግመው አንብበው እንዲሰሩ በማድረግና አንብበው መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲያነቡና እንዲረዳዱ በማበረታታት እንዲያስተምሩ ተገለፀላቸው፡፡

የሁለቱንም ምድቦች አለማማጅ መምህራን በቀጣዩ ቀን እነሱ የልምምዱን ስራ ሲያከናውኑ አጥኚዋ በተመልካችነት እንደምከታተል ተነጋግረን ተለያየን፡፡

ከ6/02/2010 ዓ.ም እስከ 1/03/2010 ዓ.ም ድረስ ልምምዱ ሲካሄድ ክፍል በመግባትና ክንውኖችን በመከታተል የተገኙ መረጃዎችን እንደሚከለተው አጠር ተደርገው ቀርበዋል፡፡

- መምህራን ከላይ በተገለፀላቸው የማንበብ ትምህርት አቀራረብ መንገድ ተዘጋጅተው ልምምዱን ማካሄዳቸውን ማስተዋል ተችሏል፡፡
- የማንበብ ተግባሩ ላይ ግን በላይታች ሞዴል እንዲለማመዱ እጣ የደረሳቸው ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ቀድመው ስለምንባቡ ስለተነበዩ ምንባቡን ጓጉተው ሲያነቡ፤ በታችላይ ሞዴል የሚለማመዱ ተማሪዎች ግን ምንባቡን ለማንበብ ጥቂቶቹ ሲሰለቹ ተስተውሏል፡፡ የቀሩት ደግሞ ከምንባቡ ስር የቀረቡ ጥያቄዎችን ስሩ እንደተባሉ ጥያቄዎችን እያነበቡ ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት በአሰሳ መልሱ የሚገኝበትን ሲያነቡ እንጅ ሙሉ ምንባቡን ሲያነቡ አልተስተዋሉም፡፡ ይህንን ለመቅረፍ መምህርቷ በየመሐሉ ዞራ ተግባራቸውን ለመቀነስ ብትችልም ተማሪዎችን ሙሉ በሙሉ አጠቃላይ ምንባቡን እንዲያነቡ ማድረግ አለማቻሉን መመልከት ተችሏል፡፡
- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ለመስራት ምንባቡን ደጋግመው እንዲያነቡ በሚጋበዙበት ጊዜ ግን በሁለቱም ምድቦች ያሉ ተማሪዎች ሁሉም መልሱን ለማግኘት ምንባቡን ደጋግመው ሲያነቡ መመልከት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በምልከታው ከተገኙ መረጃዎች መሠረት የተማሪዎቹ የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት የተሻሻለው ቀድመው ተማሪዎች ማንበብን ሲማሩ ከነበሩት አቀራረብ በልምምዱ ያገኙት የሞዴሎች አቀራረብ የተሻለ ከመሆኑ የተነሳ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በምልከታው ተማሪዎችን የበለጠ ለማንበብ ሲያሳትፍ የነበረው ሞዴል የላይታች አቀራረብ ሞዴል መሆኑንም ከተማሪዎች ተሳትፎ ምልከታ መረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝም የሁለቱን ምድቦች የድህረ ልምምድ ፈተና ውጤት ሲነፃፀርም በታችላይ ሞዴል ከተማሩት ተማሪዎች ውጤት ይልቅ በላይታች ሞዴል የተማሩት የተማሪዎች ውጤት የተሻለ ሆኖ መገኘቱም ከምልከታው ከተገኘው መረጃ ጋር ለጥናቱን ተመሳሳይ መረጃን ሰጥቷል፡፡ መረጃው አስተማማኝ መሆኑንም ከዚህ መረዳት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5. ማጠቃለያ እና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓላማ ከላይ ታች እና ከታች ላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ ለመረዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክትላቸው የቱ እንደሆነ አነፃፅሮ መለየት ነው፡፡

ይህንን የጥናቱ ዓላማ ለማሳካት በዋነኝነት በፈትና በተጨማሪነት ተጠኚ ሆነው በዕጣ ናሙና ለተመረጡ ተማሪዎች ከቀረቡ የጽሑፍ መጠይቅና በአጥኚዋ ተሳታፊ ተመልካችነት ከተገኙ የምልከታ መረጃዎች ተሰብስቧል፡፡

በእነዚህ ከላይ በቀረቡ መረጃ መስብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙ ግኝቶች አጥኚው ከልምምዱ በፊት በፊትም ያገኘችውን ውጤት ከድህረ ልምምድ በኋላ ካገኙት ጋር ሲነፃፀር ከልምምዱ በፊት ለተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው አነስተኛ መሆኑን አረጋግጫለሁ፡፡ ከድህረ ልምምዱ በኋላ ከቀረበላቸው የፈተና ውጤቶች አማካይነት ከሁለቱ የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴሎች በላይ ታች የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ችሎታን ሊያዳብር የሚችለው የላይ ታች የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ሌላው ለተማሪዎች ከቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ከዚህ በፊት የአነባብ ስልቶችን ቀደም ባሉ ክፍል ደረጃ ቢማሩም ይህንን በተግባር እንዲያውሉ መምህራንም ሆኑ ወላጆቻቸው ከተለያዩ መጽሔቶች፣ መጽሐፍቶች፣ ጋዜጣዎች፣ ወዘተ… ስልቶችን ተጠቅመው እንዲያነቡ እንደሚያበረታቱ ከሰጡት መልስ መረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ንዑሳን ርዕሶችን በየትኛው ሞዴል ቢቀርብ ተመራጭ እንደሚሆን ተጠይቀው ለአብዛኛዎቹ ጥያቄዎች ትምህርቱ በላይ ታች ቢቀርብ የተሻለ እንደሆነ ከመልሶቻቸው ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም በምልከታውም ከተገኘ መረጃ ተማሪውን በጉጉት እንዲያነቡ ያበረታታቸውና የተለያዩ የአነባብ ስልቶችን ተጠቅመው እንዲያነቡ ያደረጋቸው ሞዴል በላይታች ሞዴል የቀረበላቸው ምድቦች የበለጠ ሲሳተፉ በምልከታ ወቅት መመልከት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ ካገለገሉ ከፈተና ውጤቶች ከጽሑፍ መጠይቅና ከምልከታ ከተገኙ መረጃዎች በአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ከፍ ለማድረግ የሚረዳ ሞዴል የላይታች የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል መሆኑን ጥናቱ አረጋጧል፡፡

## 5.2 አስተያየት

የማንበብ ክሂል በዕለት ተዕለት የሚገጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ብዙ ጥቅም የሚሰጥ ክሂል ነው፡፡ በዚህም ተጠቅመው ተማሪዎች የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው ተረድተው ከጽሑፍ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ፤ ለሚገጥሟቸው ችግሮች በቀላሉ መፍትሔ በእንዲያገኙ ለማድረግ ትምህርቱ እንዴት በየትኛው ሞዴል መቅረብ እንዳለበት የሚከተሉ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ትምህርቱን ተማሪዎች በግላቸው እያነበቡ የሚማሩበትን ሁኔታ ቢያመቻቹ፣
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ለማዳበር በመጽሐፉ ካሉ ምንባቦች ውጭ የተለያዩ ምንባቦችን ከመጽሐፍት፣ ከመጽሔት፣ ከጋዜጣና ከተለያዩ ጽሑፎች አንብበው የተረዱትን ነጥብ በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ቢያበረታቱ፣
- በተጨማሪም የተለያዩ ምንባቦችን ከማንበባቸው በፊት የምንባቡን ርዕስ አይተው የቀደሙ እውቀታቸውን ለማቀስቀስ ቅድመ ማንበበ ጥያቄዎችን እንዲያዘጋጁና ዓላማ ወስነው እንዲያነቡ ዘወትር ቢያነቃቁ፣ መምህራኑም ቅድመ ማንበብ የውይይት ጥያቄ ላልተዘጋጁ ምንባቦች ከርዕሱ ጋር አያይዘው ቅድመ ውይይት ጥያቄዎችን አዘጋጅተው ተማሪዎች በውይይቱ ላይ ያነሱትን ሃሳብ ትክክል መሆን አለመሆኑን ለማጋገጥ ሲሉ በጉጉት ምንባቡን እንዲያነቡ ሁኔታዎችን ቢያመቻቹ፣
- ወላጆችና የሚመለከታቸው አካለት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ከፍ ለማድረግ የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው ባነበቡት ሃሳብ ላይ ከወላጆቻቸው ጋር በየእለቱ ውይይት የሚያደርጉበት ሁኔታ እንዲመቻችላቸው የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ ከወላጆቹ ጋር ውይይትና ክትትል ቢያደርጉ፣
- የትምህርት ቤቱ የስነጽሑፍ፣ የድራማ፣ የሚኒ ሚዲያ ክበብ ተጠሪዎች ተማሪዎችን በእነዚህ ክበባት እንዲመዘገቡ ቢያደርጉና የተዘመገቡ አባላትም ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮችን አንብበው መጥተው የተረዱትን ነገር በየጊዜው በሰንደቅ ዓላማ፣ በዕረፍት ጊዜያቸው እንዲያስተላልፉ ቢያደርጓቸው የክበቡ አባል ያልሆኑትን ሌሎችንም ለማንበብ መቀስቀስ ይቻላል፡፡

- ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ትምህርቱን በላይታች ሞዴል እንዲያስተምሩ ስለሞዴሉ አቀራረብ ተከታታይ ስልጠና ቢሰጣቸው፡፡
- የመጽሑፍ አዘጋጆች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ከፍ ለማድረግና ተማሪዎችን ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፎች ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች በላይ ታች ሞዴል ማስተማሪያነት የሚያገለግሉ አድርጎ ቢያቀርቡ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

መአዛ ደጀኔ። (1999)። በ9ኛ ክፍል የንባብ ትምህርት አሰጣጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ በአዲስ አበባ በሚገኙ ሦስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)።

በድሉ ዋቅጅራ። (1996)። በስነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

እንግዳ ዘውዴ። (1992)። "የቶፕ ዳውን" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተተግባራዊነትና ውጤታማነት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)።

ያለው እንዳወቀ። (2006)። የምርምር መሠረታዊ መርህዎች እና አተገባበር። ለመጀመሪያ ደረጃ መምህራን የተዘጋጀ መመሪያ። አዲስ አበባ።

ይታያል ወርቁ። (2003)። የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጠ ሦስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)።

ግሩም ጥበቡ። (2003)። "የታችላይ" የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ለማዳበር ያለው ውጤታማነትና ተተግባሪነት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ (ያልታተመ)።

Davies, F. (1995). Introduction Reading. England, Clyes Ltd.

Grellet, F. (1981). Developing Reading Skills. Cambridge, University Press.

Meiryun, Y. (1995). "Teaching Efficient EFL Reading" Inkral, Tomas Leds. Teacher Development Making the Right Moves. Washington, DC. PP.

Nunan, D. (1993). Introducing Discourse Analysis. Princeton. English.

Nuttall, G. (1982). Teaching and Reading Skill Foreign Language. Heineman Educational Book Ltd.

USAID/Ethiopia. (2003). Improving Quality of Primary Education Program (USAID/IQPEP) in Ethiopia. Addis Ababa.

Wallace, C. (1992). Language Teaching Reading Skills. New York: Oxford University Press.

Williams, E. (1984). Reading in the Language Classroom. London: Macmillan Publishers.

**አባሪ**

## አባሪ አንድ

## ቅድመ ንባብ ፈተና

## ጉዞ ወደ ጊቤ ሸለቆ ብሔራዊ ፓርክ

ወደ ጊቤ ሸለቆ ብሔራዊ ፓርክ ይዣችሁ እጓዛለሁ፡፡ በጉዞዬ የገጠሙኝን አይነ ገብ ክስተቶች በምናባችሁ እንድታዩአቸው አደርጋለሁ፡፡

እኔና የሥራ በልደረቦቼ መነሻችን የነበረችው የደብብ ክልል ርዕሰ ከተማ የሆነችው ሐዋሳ ናት፡፡ በጠዋት ተነስተን ወደ አዲስ አበባ በሚወስደው የአስፖልት መንገድ ይዘን ጉዞ ጀመርን፡፡ መድረሻችን ደግሞ የጊቤ ሸለቆ ብሔራዊ ፓርክ ነው፡፡ መኪናችን አየሩን እየሰነጠቀ በፍጥነት ሲከንፍ እኛ ደግሞ በየመንገዱ ዳር የሚገኙትን የተለያዩ ትእይንቶችን እየተመለከትን ነበር፡፡ የሻሸመኔን ከተማ መሀል ለመሀል ሠንጥቀን በማለፍ ከኩየራ ቀጥሎ የሚገኘው የተንጣለለ ሜዳ ላይ የሚገኙትንና የተዘረጋ ዣንጥላ የሚመስሉትን የግራር ዛፎች አስተዋልናቸው፡፡ ትንሽ እንደተጓዝን ሰፊ የእርሻ መሬት ላይ የሚዘናፈል የጤፍ አዝመራ ተመለከትን፡፡ ትእይንቱ አይንን ይማርካል፡፡ በተወሰነ ርቀት ላይ የሚገኙትን ትንንሽ ከተሞች እያለፍን በመጓዝ ዝዋይ ከተማ ደረስን፡፡ ከዚያም አዲስ የተሠራውን የዝዋይ ቡታጅራ መንገድ ይዘን ጉዟችንን ቀጠልን፡፡

ቡታጅራ ከተማ ስንደርስ ለቁርስ እረፍት አደረግን፡፡ ቁርሳችንን ከበላን በኋላ ሰንሰላታማውን የዘቢዳር ጠመዝማዛ ተራራ እየተመለከትን ጉዛችንን ወደ ጊቤ ሸለቆ ብሔራዊ ፓረክ አደረግን፡፡ የዘቢዳር ተራራ ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ ድንቅ ነው፡፡ በአካባቢው የሚነፍሰው ነፋስ መንፈስን በማደሰ ዘና ያደርጋል፡፡ ተራራውን በመናድ የተሰራው የአስፓልት መንገድ ጠመዝማዘነት አይን ይማርካል፡፡

በአካባቢው ከፍታ የተነሳ ረፋድ ላይ እንኳን ይበርዳል፡፡ ይሁን እንጂ መኪና ውስጥ የነበረው ተጓዥ የበረደው አይመስልም፡፡ በቀዝቃዛው አየር ታጅበትን በመንገዱ ቅርጽ እና አሠራር እየተገረምን ጉዟችንን ቀጠልን፡፡

ጥቂት እንደተጓዝን ከመኪናቸው ወርደው የመንገዱን አሠራር የሚያደንቁ መንገደኞችን ተመልከትን፡፡ እኛም ተቀላቅልን መመልከት ጀመርን፡፡ በእድሜያቸው ገፋ ያሉ እንደ መንገደኛ "ይህ የምታዩት ሰንሰለታማ ተራራ ለዘመናት በቅርብ ርቀት የሚገኙትን የአካባቢውን ህዝብ እንዳይገናኙ አድርጓቸው ነበር፡፡ 'ለሁሉም ጊዜ አለው' እንደሚባለው ይኸው አሁን

እንደምታዩት በመንግስት ልዩ ትኩረት ተራራው ተሸንፏል። ተለያይተው የነበሩም ቤተ ጉራጌዎች ተገናኝተዋል። የመንገዱም አሠራር በጣም የሚገርም ነው" እያሉ የሚያውቁትን እይተናገሩ ነበር።

ይህን በአዲስ መልክ የተሠሪውና ድንቅ የምህንድስና ጥበብ የታየበትን መንገድ በመጠቀም የዋቢን ወንዝ ተሻግረን ወልቂጤ፣ ከዚያም ወደ ጊቤ ሸለቆ በሔራዊ ፓርክ ደረስን።

ፓርኩ 36 ሺህ ሄክታር ስፋት ያለውና እንጨታማ ደንና ቁጥቋጦ የበዛበት ሲሆን የግራር ዝርያዎች፣ ቀውጥ፣ ቦቶሮ፣ ቤሎ፣ የቦረና እጣን ዛፍና የዕፅዋት ዝርያዎች ይገኙበታል። የአየር ፀባዩም ሞቃታማ ነው። <u>ቀልብን</u> የሚስቡ የተለያዩ ባለቀለም አእዋፍ፣ የጦጣ ዝርያዎች ጉማሬና አዞ የመሳሰሉ የዱር እንስሳት እንደ ልባቸው <u>ሲቦርቁ</u> መመልከት ቻልን።

በፓርኩ ውስጥ ያስተዋልነው ሌላው ነገር የዋቤና የጊቤ ወንዞች በጊቤ ሰንሰለታማ የተፈጥሮ ተራራ ታጅበው ወደ ግልገል ጊቤ ሁለት የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ሲጓዙ ማየት ነው። ይህን አስገራሚ አካባቢ ማየት መታደል ነው። አበቃሁ።

(የደቡብ ትምህርት ቢሮ። 2007። የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣ 7ኛ ክፍል። ከገጽ 10-11)

**የሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት በተሰጣችሁ የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ፃፉ።**

1. ኀቢኚዎቹ ቁርሳቸውን የበሉት ዝዋይ ከተማ ነው።
2. የዘቢዳር ተራራ አካባቢ ከከፍታው የተነሳ ረፋድ ላይ ይሞቃል።
3. ሰንሰለታማው የዘቢዳር ተራራ ለዘመናት በቅርብ ርቀት የሚገኙትን የአካባቢውን ህዝብ እንዳይገናኙ አድርጓቸው ነበር።
4. የዘቢዳር ተራራ ተፈጥአዊ አቀማመጡ አስደናቂ ነው።
5. ፓርኩ እንጨታማ ደንና ቁጥቋጦ የበዛበት ነው።
6. ኀቢኚዎቹ በፓርኩ ውስጥ ቀልብን የሚስቡ የተለያዩ ባለቀለም ድንጋዮች መመልከታቸውን ገለጹ።
7. የዋቤና የጊቤ ወንዞች በጊቤ ሰንሰለታማ ተራራ ታጅበው ወደ ግልገል ጊቤ ወንዝ ይቀላቀላሉ።

**ቀጥሎ በ"ሀ" ረድፍ ለቀረበው ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ከ"ለ" ረድፍ ከተዘረዘሩት በምመረጥ አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 8. ማስተዋል | ሀ. ዘግናኝ |
| 9. ይማርካል | ለ. መንገደኛ |
| 10.ታጀበ | ሐ. ከተመገብን |
| 11. በመናድ | መ. አቋርጠን |
| 12. አስገራሚ | ሠ. ያማልላል |
| 13. የምታዩት | ረ. ከጠጣን |
| 14. ተጓዥ | ሰ.ጨረስኩ |
| 15. ከበላን | ሸ. አስደናቂ |
| 16. ሰንጥቀን | ቀ. በማፈራረስ |
| 17. አበቃሁ | በ. ማስታወስ፣ ማስብ |

ተ.ተከበን

ቸ. የምትመለከቱት

**የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በምንባቡ መሠረት አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

18. ፀሐፊው አይነግቡ የሆኑ ክስተቶችን በ ___________ እንድናይ አደረገን፡፡

19. የፓርኩ ስፋት _____________ ሄክታር ነው፡፡

20. የኀቢኚዎቹ የጉዞ መነሻ የሆነችው _________ ትባላለች፡፡

21. ኀቢኚዎቹ በፓርኩ ውስጥ የዱር እንስሳት እንደልባቸው _________ መመልከት ቻሉ፡፡

22. ይህንን አስገራዊ አካባቢን ማየት ___________ ነው፡፡

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል መርጣችሁ በመልስ መስጫ መረቀታችሁ ላይ ፃፉ፡፡**

23.‹‹ወፍ››ለሚለው ቃል ብዙ ቁጥር አመልካች ቃል የቱ ነው- ብሎ "ቃላት" ካለ "ወፍ" ብሎ ____ ይባላል፡፡

ሀ. ወፋት　　ለ. አዕዋፋት

ሐ. አእዋፍ　　መ. አእዋፋቶች

24.የዘቢዳር ተራራ ምን አይነት ተራራ ነው?

ሀ. ቀጥ ያለ ሐ. ዘመዝማዛ

ለ. ጉዞ የሚያመች መ. ለጥያለ ሜዳ

25.ተለያይተው የነበሩትን ቤተ ጉራጌዎች ያገናኘው

ሀ. በመንግስት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የተሠራው መንገድ ነው።

ለ. ድንቅ የምህንድስና ጥበበ የታየበት አዲስ መንገድ ነው።

ሐ. "ለሁሉም ጊዜ አለው" ተብሎ መነገሩ ነው።

መ. "ሀ" እና "ለ" መልስ ናቸው።

26."እንጨታማ" የሚለው ቃል የቃል ክፍሉ _____ ነው።

ሀ. ቅጽል ለ. ስም

ሐ. ግስ መ. ሁሉም

27.በአንቀጽ ሁለት ላይ "አይንን ይማርካል" የተባለው ምኑ ነው?

ሀ. ዣንጥላ የሚመስሉ የግራራ ዛፎች

ለ. በሰፊው መሬት ላይ የሚዘናፈለው የጤፍ አዝመራ

ሐ. የጊቤ ሸለቆ ብሔራዊ ፓርክ

መ. "ሀ" እና "ለ" መልስ ናቸው

28.የጎቢኚዎቹ መነሻ ሃዋሳ ከተማ ስትሆን መድርሻቸው የት ነው?

ሀ. ቡታጅራ ለ. ጊቤ ሸለቆ

ሐ. ዝዋይ ከተማ መ. የዘቢዳር ተራራ

29."ለሁሉም ጊዜ አለው" የሚለው አባባል ለምን በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ተቀመጠ?

ሀ. የፀሐፊው ሃሳብ ስለሆነ ለ. የፀሐፊው ሃሳብ ስላልሆነ

ሐ. የአንባቢው እና የፀሐፊው ሃሳብ ስለሆነ መ. የመንግስት ሃሳብ ስለሆነ

30. በአንቀጽ ሦስት "ይሁን እንጂ" የሚለው አያያዥ ቃል የገባው የሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ሃሳብ የመጀመሪያውን ዐረፍተ ነገር ሃሳብ ____ _____ መሆኑን ለማመልከት ነው።

ሀ. የሚደገፍ ለ. የሚቃረን

ሐ. የሚያጋንን መ. የሚያመጠቃልል

31. "በእድሜያቸው ገፋ ያሉ" ሲል ምን ለማለት ነው?

ሀ. ያረጁ ለ. አዛውንቶች

ሐ. ሽማግሌዎች መ. ሁሉም መልስ ናቸው

32.“ድንቅ ምህንድስና ጥበብ” የሚለው በሌላ አገላለጽ

ሀ. አስገራሚ የኢንጅነሪንግ እውቀት ሐ. በአጋጣሚ የተገኘ የምህንድስና እውቀት

ለ. አሳሳቢ የኢንጂነሪንግ እውቀት መ. የምያስተች የምህንድስና እውቀት

33. “ቁርሳችንን ከበላን በኋላ የዘቢዳርን ሰንሰለታማውን ተራራ እየተመለከትን ተጓዝን፡፡” በሚለው ዐረፍተ ነገረ የተሠመረበት ቃል ፍቺ ምንድነው

ሀ. ሜዳማውን ለ. የተያያዘውን

ሐ. አሸዋማውን መ. ሁሉም መልስ ናቸው

34.“ይኸው አሁን እንደሚታዩት በመንግስት ልዩ ትኩረት ተራራው ተሸንፏል፡፡” የተባለው ተራራ የቱ ነው

ሀ. የግልገል ጊቤ ተራራ ለ. የሐዋሳ ተራራ

ሐ. የዝዋይ ተራራ መ. ሰንሰለተማው የዘቢዳር ጠመዝማዛው ተራራ

35. በአንቀጽ አምስት ላይ “ከዚያም” የሚለው አያያዥ ቃል የገባው __________ ለማመልከት ነው፡፡

ሀ. የቦታ ቅድም ተከተልን ሐ. የዓይነት ቅደም ተከተልን

ለ. የጊዜ ቅድም ተከተልን መ. መልስ አልተሰጠም፡፡

36.ከላይ በጥያቄ ቁጥር 35 ላይ የተጠቀሰው አያያዥ ቃል በምንባቡ በአንቀጽ አምስት ላይ ምንን ከምን ጋር አያይዟል

ሀ. ሀረግን ከሀገር ጋር ሐ. አንቀጽን ከአንቀጽ ጋር

ለ. ዐረፍተ ነገረን ከዐረፍተ ነገር ጋር መ. ዐረፍተ ነገርን ከሀረግ ጋር

37. “በሰፊው መሬት ላይ የሚዘናፈለውን የጤፍ አዝመራ ተመለክትን፡፡” በሚል ዐረፍተ ነገር የተሠመረበት ቃል ፍቺው

ሀ. ቀጥ ብሎ የቆመውን ለ. የሚወዛወዘውን

ሐ. የተኛውን መ. የረገፈውን

38.ከሚከተሉት ውስጥ የብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያ የሌለበት ቃል የቱ ነው

ሀ. ሌሎች ለ. አእዋፍ ሐ. እፅዋት መ. መኪናችን

39. በአንቀጽ አራት ጎቢኚዎች የዘቢዳርን ተራራ ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ እያደነቁ ጥቂት እንደተጓዙ ከመኪናቸው የወረዱበት ምክንያት ምንድነው?

ሀ. ቁርስ ሊበሉ ነው፡፡ ለ. ምሳ ሊበሉ ነው፡፡

ሐ. አስገራሚ የሆነውን የመንገዱን አሠራር ለመመልከት ነው፡፡

መ. የዘቢዳርን ተራራ ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ ለማድነቅ ነው፡፡

40.“ፀሐፊው አይነገብ የሆኑ ክስተቶችን በምናባችሁ እንዲታየአቸው አድርጋችኂለሁ” ያለው እነማንን ነው?

ሀ. አንባቢያንን ለ. ራሱን ሐ.ጎቢኚዎችን

መ.ከእሱ ጋር ያሉ ጓደኞቹን

**ለሚለከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺያቸውን በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ ፃፉ፡፡**

41. ጥቂት
42. ሞቃታማ
43. መነሻ
44. ጠቃሚ
45. ቅርብ

**የሚከተሉትን ቃላት ዋናውን ቃል ከቅጥያዎቹ ነጣጥላችሁ በመልስ መስጫ ወረቀታችሁ ላይ ፃፉ፡፡**

46.መንገደኞች

47.ባልደረቦቹ

48.መድረሻችን

49.ጓደኞቹን

50.እንጨታማ

# አባሪ ሁለት

## ታችላይ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል

USAID/Ethiopia (2003)፣ ግሩም (2003) እነ Grabe and Stoller (2002) Amderson (1999) ዋቢ በማድረግ የታች ላይ ሞዴል የአንድን ጽሑፍ መልዕክት አንብቦ ለመረዳት መሠረት መደረግ ያለበት የሰዋስው እውቀት መሆን እንዳለበት፤ የአንባቢውን የቀደመ እውቀት በጽሑፉ መካከል ጣልቃ መግባት እንደሌለበት፤ አንባቢው በራሱ የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ ለመረዳት ከአነስተኛ ውህድ አሀድ በመነሳት መስመራዊ በሆነ መንገድ ከዝርዝር ሃሳብ ወደ አጠቃላይ ሃሳብ የሚሄድ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

ከዚህም ሃሳብ በመነሳት ለታች ላይ ማስተማሪያነት የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት እና የምንባቡን አጠቃላይ ሃሳብ የሚጠይቁ ጥያቄዎች በብዛት አልቀረቡም፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ የቀደመ እውቀት በማንበብ ጊዜ ጣልቃ መግባት የለበትም ስለተባለ በምንባብ ጊዜ ቀዳሚ እውቀታቸውን የሚያገናዝቡት ጥያቄ አልቀረበም፡፡ በድህረ ማንበብ ጊዜ የቀረቡ ጥያቄዎች የምንባቡን ዝርዝር ጉዳዮች እና ሰዋሰዋዊ ጥያቄዎችን በደንብ መረዳታቸውን ለማወቅ የሚያስችሉ ጥያጠቄዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## በታችላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል ለሚማሩ ተማሪዎች የቀረበ ምንባብ

### ምንባብ አንድ

**ተግባር አንድ፡- የማንበብ ሂደት**

### የአፈር እንክብካቤ

የተፈጥሮ ሀብቶች ከሚባሉት መካከል አፈር ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል፡፡ አፈር የሰብል ምርት ለማምረት፣ የካርቦን ልቀትን ለመምጠጥ፣ ንጥረ ነገሮችንና ውኃን ጠብቆ ለመያዝ ይጠቅማል፡፡ አፈር ለሰው ልጆችም ሆነ ለሌሎች ፍጥረታት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ኑሮን ለማሻሻል ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ስለሆነም አፈር እንደሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ውስን ሀብት በመሆኑ በእንክብካበ ሊያዝ ይገባል፡፡

በኢትዮጵያ በተለይም በደጋማ በሆኑ ከፍተኛ ቦታዎች፣ አፈሩ በሰዎች አያያዝ ጉድለት እየተራቆተ ነው፡፡ በመራቆቱም አፈሩ ውኃ የማከማቸት አቅሙ ውስን ሆኗል፡፡ የአፈር ክምችቱ

ስስ፣ መሬቱ አለታማና ለካልሲየም ካርቦኔት አጥረት የተጋለጠ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በደጋማው ከፍተኛ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ሰብል የሚያመርቱት ሰው ሰራሽ በሆነ የማዳበሪያ ውጤቶች በመጠቀም ነው፡፡ ማዳበሪያ የማጥቀሙት ግን የሚያመርቱት የምርት መጠን ዝቅተኛ ነው፡፡

የአፈር ለምነትን ለመጨመር ረጅም ጊዜ ይወስዳል፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት አንድ ሳንቲ ሜትር ለም አፈር ለመጨመር በርካታ አመታትን ሊፈጅ ይችላል፡፡ የአፈር ለምነትን መጨመር የሚቻለው ደግሞ አፈርን ለማዳበር የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡፡

አፈር በጎርፍና በነፋስ እንዳይወሰድና ለምነቱን እንዳያጣ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መንከባከብ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው አማራጭ ተራራማ ቦታዎችን በደን መሸፈን ነው፡፡ በዚህም ዛፎች አፈር በጎርፍ እንዳይሸረሸርና በነፋስ እንዳይጠረግ መካለከል ይችላሉ፡፡ ዛፎች በሥራቸው አማካይነት አፈሩን በመያዝ መሬቱ በጎርፍ እንዳይሸረሸር ያደርጋሉ፡፡ ከፍተኛ ዝናብ በሚጥልበት ወቅት ደግሞ ሃይሉን በመቆጣጠር አፈሩ እንዳይታጠብ ይከላከላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዛፎች የአፈርን ለምነትና ውፍረት በመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ የዛፎች ቅጠሎች አፈር በንጥረ ነገሮች እንዲዳብር ያደርጋል፡፡ ከዛፎች የሚረግፉት ቅጠላ ቅጠሎች ወደ ብስባሽ ስለሚለወጡ የአፈር ለምነትን ይጨምራሉ፡፡ ስለዚህ ተራራማ ቦታዎችን በደን በመሸፈን እና የአፈር መከላትን በመከላከል ለምነትን መጨመር ይቻላል፡፡

በተጨማሪም በዳገታማ ቦታዎች ላይ እርከንን ክትር በመሥራት አፈርን በመከላከል ማዳን ይቻላል፡፡ ዳገታማ መሬቶችን አግደም በማረስ፣ በድንጋይና በአፈር እርከንን በመሥራት፣ አፈሩን በጎርፍ ታጥቦ እንዳይሄድ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህም ከከፍተኛ እርከኑ ላይ ያረፈረው አፈርም ውኃ መቋጠር ስለሚችል ለምነት ይኖረዋል፡፡ እርከን በሆኑ ቦታዎች ላይ ደግሞ ክትር በመስራት የጎርፍ ፍጥነትን መግታትና አፈር ታጦቦ ወደሌላ ቦታ እንዳይሄድ መከላከል ይቻላል፡፡

የጥራጥሬ እህሎችን (አተር፣ ባቄላ፣ ጓያ፣ ሽንብራና የመሳሰሉትን) አፈራርቆ በመዝራትም የአፈር ለምነትን መጠበቅ ይቻላል፡፡ እነዚህን የጥራጥሬ እህሎች በሌሎች ሰብሎች መካከል በየአመቱ አፈራርቶ መዝራት አፈሩ በተለያዩ ንጥረ ነገሮች እንዲበለፅግ በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል፡፡

ከዚህም ሌላ የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ሥርዓትን መከተል ያስፈልጋል፡ መሬትን ለእርሻ፣ ለደን ልማት፣ ለግጦሽ በማለት ከፋፍሎ በሥርአት መጠቀም የመሬት ለምነትን ይጨምራል። ይህ ሲሆን አፈር ያለአግባብ አይባክንም።

በአጠቃላይ አፈር ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ የሆነ ውስን ሀብት ስለሆነ በእንክብካቤና በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል።

(የደቡብ ትምህርት ቢሮ። 2007። የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣ ከገጽ 16-17)

**አንብቦ መረዳት**

**ተግባር ሁለት**

**የሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. አፈር በጎርፍና በነፋስ እንዳይወሰድ ተራራማ አካባቢዎች በደን ሊሸፈኑ ይገባል።
2. ከዛፎች የሚረግፉ ቅጠላ ቅጠሎች ወደ ብስባሽነት ስለሚለወጡ የአፈርን ለምነት ይቀንሳሉ።
3. ጥራጥሬ እህሎችን በሌሎች ሰብሎች መካከል አፈራርቆ መዝራት የአፈር ለምነትን ያበለጽጋል።
4. ክትር በመስራት የጎርፍ ፍጥነትን መቀንስ ይቻላል።
5. መሬትን ለእርሻ፣ ለደን ልማት፣ ለግጦሽ በማለት ከፋፍሎ መጠቀም የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ስርአትን ያሳጣል።

**ተግባር ሦስት**

**ቀጥሎ በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡ ቃላት በምንባቡ መሠረት ተመሳሳይ ፍቺያቸውን በ"ለ" ረድፍ ከተዘረዘሩት በመምረጥ አዛምዱ።**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ቀዳሚ | ሀ. ማነስ |
| 2. ማከማቸት | ለ. መዳበር |
| 3. እጥረት | ሐ. የመጀመሪያ |
| 4. በርካታ | መ. ጥቂት |
| 5. መበልጸግ | ሠ. ማጠራቀም |
| | ረ. ብዙ |

## ተግባር አራት

የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በምንባቡ መሠረት አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. አፈር ኑሮን ለማሻሻል ከፍተኛ _______ አለው፡፡

ለ. የአፈር ___ ለመጨመር ረዥም ጊዜ ይወስዳል፡

ሐ. በደጋማ ቦታዎች ላይ እርከንና ክትር በመሥራት አፈርን _________ ማዳን ይቻላል፡፡

መ. ደጋማ አካባቢ የሚገኙ ሰዎች ሰብልን በ___________ ማዳበሪያ ተጠቅመው ያመርታል፡፡

## ተግባር አምስት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል መርጣችሁ አክብቡ፡፡**

1. በአንቀጽ አንድ መጨረሻ ላይ የሚገኘው "ይገባል" የሚለው ቃል _________ ሲነበብ የምንባቡን ሃሳብ ይገልፃል፡፡

ሀ. ላልቶ ለ. ጠብቆና ላልቶ ሐ. ጠብቆ መ. ላልቶና ጠብቆ

2. ከሚከተሉት ውስጥ ብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያ የሌለበት ቃል የቱ ነው?

ሀ. ፍጥረታት ሐ. ሰዎች

ለ. አመታት መ. መልስ አልተሰጠም

3. በ"ሆነ" በሚለው ቃል መድረሻ ላይ የተቀጠለው ቅጥያ የቱ ነው?

ሀ. -ኡ ለ. -ኑ ሐ. ቅጥያ የለበትም መ. -ኽ

4. በአንቀጽ ሰባት ላይ "ይህ ሲሆን" የተባለው ምንን ለማመልከት ነው

ሀ. የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ የመሬት አያያዝ ሥርአት መከተልን

ለ. መሬትን ለእርሻ፣ ለደን ልማት፣ ለግጦሽ ከፋፍሎ መጠቀምን

ሐ. ክትር መስራት

መ. ሀ ና ለ መልስ ናቸው

5. በአንቀጽ ሁለት ላይ "በዚህ ምክንያት" የሚለው አያያዥ ቃል የሚያመለክተው ምክንያት

ሀ. አፈሩ በሰዎች አያያዝ ጉድለት መራቆቱን

ለ. የአፈር ለምነቱን መሳሳቱ

ሐ. መሬቱ ለአለታማና ለካልሲየም ካርቦነት አጥረት መጋለጡን

መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

## ተግባር ስድስት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደየአጠያየቃቸው መልሱ፡፡**

ሀ. ከምንባቡ ሃሳብ በተጨማሪ የአፈር ለምነትን ሊጨምሩ የሚችሉ ነገሮችን ከተለያዩ ጽሑፎች አንብባችሁ በራሳችሁ አገላለጽ ከፃፋችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

ለ. የአፈር ለምነትን መጠበቅ ያስፈልገበት ምክንያት ምንድነው? በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

# አባሪ ሦስት

## የላይታች የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል

USAID/Ethiopia (2003), Nuttal (1982), Nunnan (1993), ግሩም (2003), Carellil (1988), Gave (1983), ዋቢ በማድረግና እንግዳ (1992) እነ Higgirs (1984), እና Goodman (1970), ዋቢ በማድረግ በላይ ታች ሞዴል አንድን ጽሁፍ መልዕክት አንብቦ ለመረዳት የአንባቢዎችን የቀደመ እውቀት የሚጠይቅ መሆኑንና ከማንበብ በፊት ስለ ምንባቡ መገመት፣ መተንበይ፣ በንባብ ጊዜ የቀደመ እውቀትን ከምንባቡ መልእክት ጋር ማዛመድና መተርጎም የገመቱትን ግምት ትክክለኝነት ማረጋገጥ፤ ለመማር ሰዋሰዋዊ እውቀት ብቻ በቂ አለመሆኑንና አንባቢው ቀድመው ስለምንባቡ አጠቃላይ መልእክት መገመቱና መተንበዩ ዝርዝር ጉዳዩን በቀላሉ እንዲረዳ የሚያደርግ ሞዴል መሆኑን ገልጸዋል።

ስለዚህ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት የላይ ታች ምንባብ አቀራረቡ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ለመቀስቀስ የሚያስችሉ ቅድመ ማንበብ መልመጃዎች ተዘጋጅተዋል። በመቀጠልም የቀደመ እውቀታቸውን ከምንባቡ ውስጥ ካገኙት እውቀት ጋር እንዲያነጻጽሩና እንዲያዛዱ የሚያስችሉ የምንባብ ጊዜ ጥያቄዎችም ቀርበዋል። በድህረ ማንበብ ጊዜ ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ከፍ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅተዋል።

**በላይ ታች የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል ለሚማሩ ተማሪዎች የቀረበ ምንባብ**

**ምንባብ አንድ**

**የአፈር እንክብካቤ**

**ቅድመ ማንበብ**

**ተግባር አንድ**

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በቃል ስጡ።**

ሀ. የአፈር እንክብካቤ ማለት ምን ማለት ነው

ለ. አፈርን በምን መልኩ መንከባከብ ይቻላል

ሐ. አፈርን መንከባከብ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል

ተግባር ሁለት፡ የማንበብ ሂደት

# ምንባብ

የተፈጥሮ ሀብቶች ከሚባሉት መካከል አፈር ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል፡፡ አፈር የሰብል ምርት ለማምረት፣ የካርቦን ልቀትን ለመምጠጥ፣ ንጥረ ነገሮችንና ውኃን ጠብቆ ለመያዝ ይጠቅማል፡፡ አፈር ለሰው ልጆችም ሆነ ለሌሎች ፍጥረታት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ኑሮን ለማሻሻል ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ስለሆነም አፈር እንደሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ውስን ሀብት በመሆኑ በእንክብካበ ሊያዝ ይገባል፡፡

በኢትዮጵያ በተለይም  በደጋማ በሆኑ ከፍተኛ ቦታዎች፣ አፈሩ በሰዎች አያያዝ ጉድለት እየተራቆተ ነው፡፡ በመራቆቱም አፈሩ ውኃ የማከማቸት አቅሙ ውስን ሆኗል፡፡ የአፈር ክምችቱ ስስ፣ መሬቱ አለታማና ለካልሲየም ካርቦኔት አጥረት የተጋለጠ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በደጋማው ከፍተኛ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ሰብል የሚያመርቱት ሰው ሰራሽ በሆነ የማዳበሪያ ውጤቶች በመጠቀም ነው፡፡ ማዳበሪያ የማጥቀሙት ግን የሚያመርቱት የምርት መጠን ዝቅተኛ ነው፡፡

የአፈር ለምነትን ለመጨመር ረጅም ጊዜ ይወስዳል፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት አንድ ሳንቲ ሜትር ለም አፈር ለመጨመር በርካታ አመታትን ሊፈጅ ይችላል፡፡ የአፈር ለምነትን መጨመር የሚቻለው ደግሞ አፈርን ለማዳበር የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡፡

አፈር በጎርፍና በነፋስ እንዳይወሰድና ለምነቱን እንዳያጣ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መንከባከብ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው አማራጭ ተራራማ ቦታዎችን በደን መሸፈን ነው፡፡ በዚህም ዛፎች አፈር በጎርፍ እንዳይሸረሸርና በነፋስ እንዳይጠረግ መካለከል ይችላሉ፡፡ ዛፎች በሥራቸው አማካይነት አፈሩን በመያዝ መሬቱ በጎርፍ እንዳይሸረሸር ያደርጋሉ፡፡ ከፍተኛ ዝናብ በሚጥልበት ወቅት ደግሞ ሃይሉን በመቆጣጠር አፈሩ እንዳይታጠብ ይከላከላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዛፎች የአፈርን ለምነትና ውፍረት በመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ የዛፎች ቅጠሎች አፈር በንጥረ ነገሮች እንዲዳብር ያደርጋል፡፡ ከዛፎች የሚረግፉት ቅጠላ ቅጠሎች ወደ ብስባሽ ስለሚለወጡ የአፈር ለምነትን ይጨምራሉ፡፡ ስለዚህ ተራራማ ቦታዎችን በደን በመሸፈን እና የአፈር መከላትን በመከላከል ለምትን መጨመር ይቻላል፡፡

የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

ተግባር ሦስት

1. በቅድመ ማንበብ ጊዜ ለቀረበላችሁ ጥያቄዎች በግምት የመለሳችሁት መልስ ትክክል ነው ወይስ አይደለም ትክክል ካልሆነ ምክንያቱን አብራርታችሁ ግለጹ
2. እስካሁን ካነበባችሁት ስለ አፈር እንክብካቤ ምን ምን ዋና ነጥቦች አገኛችሁ ተናገሩ፡፡

በተጨማሪም በዳገታማ ቦታዎች ላይ እርከንን ክትር በመሥራት አፈርን በመከላከል ማዳን ይቻላል፡፡ ዳገታማ መሬቶችን አግደም በማረስ፣ በድንጋይና በአፈር እርከንን በመሥራት፣ አፈሩን በጎርፍ ታጥቦ እንዳይሄድ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህም ከከፍተኛ እርከኑ ላይ ያረፈረው አፈርም ውኃ መቋጠር ስለሚችል ለምነት ይኖረዋል፡፡ እርከን በሆኑ ቦታዎች ላይ ደግሞ ክትር በመስራት የጎርፍ ፍጥነትን መግታትና አፈር ታጦቦ ወደሌላ ቦታ እንዳይሄድ መከላከል ይቻላል፡፡

የጥራጥሬ እህሎችን (አተር፣ ባቄላ፣ ጓያ፣ ሽንብራና የመሳሰሉትን) አፈራርቆ በመዝራትም የአፈር ለምነትን መጠበቅ ይቻላል፡፡ እነዚህን የጥራጥሬ እህሎች በሌሎች ሰብሎች መካከል በየአመቱ አፈራርቶ መዝራት አፈሩ በተለያዩ ንጥረ ነገሮች እንዲበለፅግ በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል፡፡

ከዚህም ሌላ የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ሥርዓትን መከተል ያስፈልጋል፡ መሬትን ለእርሻ፣ ለደን  ልማት፣ ለግጦሽ በማለት ከፋፍሎ በሥርአት መጠቀም የመሬት ለምነትን ይጨምራል፡፡ ይህ ሲሆን አፈር ያለአግባብ አይባክንም፡፡

በአጠቃላይ አፈር ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ የሆነ ውስን ሀብት ስለሆነ በእንክብካቤና በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

(የደቡብ ትምህርት ቢሮ፡፡ 2007፡፡ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣ ከገጽ 16-17)

## አንብቦ መረዳት

## ተግባር አራት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት ከነምክንያታችሁ መልሱ።**

ሀ. አፈር ለሰው ልጆችም ሆነ ለሌሎች ፍጥረታት ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ለ. ዛፎች አፈረ በጎርፍ እንዳይሸረሸርና በነፋስ እንዳይጠረግ መከላከል ይችላሉ

ሐ. ተራራማ ቦታዎችን በደን መሸፈን አያስፈልግም።

## ተግባር አምስት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ብቻ በመምረጥ አክብቡ።**

1. "አፈር በጎርፍና በነፋስ <u>እንዳይወሰድ</u> እና ለምነቱን እንዳያጣ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል" በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ሐረግ ፍቺ

ሀ. እንዳይከላ ለ. እንደይሸረሸር

ሐ. እንዳይሰረቅ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

2. "በገደላማ ቦታዎች ላይ ክትር በመስራት የጎርፍ ፍጥነትን <u>መግታት</u> ይቻላል።" በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ የተሠመረበት ቃል ፍቺው

ሀ. መከላከል ለ. ሸለቆ መፍጠር

ሐ. አፈሩ ታጥቦ እንዲሄድ ማድረግ መ. ሁለም መልስ ናቸው

3. የኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢ መሬቶች በእንክብካቤ ጉድለት የአፈሩ መራቆት ምን ችግር ፈጠረባቸው?

ሀ. የአፈር ክምችቱ መሳሳት

ለ. አፈሩ ውኃ የማጠራቀም ወስነነት

ሐ. መሬቱ አለታማና ለካልሲየም ካርቦኔት እጥረት መጋለጥ

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4. “የአፈር መራቆት” ሲል ምንን ለመግለፅ ነው?

ሀ. አፈሩ ልብስ አለመልበሱን ለመግለጽ ነው፡፡

ለ. አፈሩን ከጎርፍና ከነፋስ ለሚከላከሉ ሣርና ዛፎች አለመኖራቸውን ለመግለጽ ነው፡፡

ሐ. አፈሩ ለም መሆኑኑ ለመግለጽ ነው፡፡

መ. ከ”ለ” በስተቀር ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

5. በአራተኛው አንቀጽ ሁለተኛ መስመር ላይ የሚገኘው “የመጀመሪያው” የሚለው አያያዥ ቃል ምንን ያመለክታል?

ሀ. የቦታ ቅድም ተከተልን

ሐ. የጊዜ ቅደም ተከተልን

ለ. የዓይነት ቅድም ተከተል

መ. ምክንያትን ያመለከታል

6. የአንቀጽ አምስት ዋና ሃሳብ ምንድነው?

ሀ. አፈርን እርከንና ክትር በመሥራት መንከባከብ

ለ. ጥራጥሬ እህሎችን አፈራርቆ መዝራት

ሐ. ተራራማ ቦታዎችን በደን መሸፈን

መ. የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ሥርአትን መከተል

## ተግባር ስድስት

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች እንደየ አጠያየቃቸው መልስ ስጡ፡፡

ሀ. በአካባቢያችሁ ያሉ ማህበረሰቦች አፈርን ለመከላከል ምን እንደሚያደርጉ ሰዎችን ጠይቃችሁ ሃሳቡን በአንድ አንቀጽ ፃፉና በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

ለ. ስለአፈር እንክብካቤ የተፃፉ ጽሑፎችን ከመጽሔት፣ ጋዜጣ፣ ከተለያዩ ጽሑፎች አንብቦና ባገኛችሁት ሃሳብ ላይ ከጓደኞቻችን ጋር ተወያይታችሁ በጋራ ተስማምታችሁ ያገኛችሁትን ነጥብ ፃፍና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

# አባሪ አራት
# በታች ላይ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል ለሚማሩ ተማሪዎች የቀረበ ምንባብ
## ምንባብ ሁለት
## የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት
## ተግባር አንድ
## የማንበብ ሂደት
## የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት

እንደምንናቸሁ ውድ እናቶችና አባቶች ደህና ሰነበታችሁ ኧ… ወይኒቱ እባላለሁ  በዚህ ቀበሌ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ነኝ፡፡ ኧ… በጥሪያችን መሠረት ሰዓቱን አክብራችሁ በመገኘታችሁ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በጋራ የተገናኘውነው ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደል መቼም ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በየጊዜው ውይይት እንዳደረጋችሁ እገምታለሁ፡ እሺ እናቶቼና አባቶቼ ዛሬ ደግሞ የጤና ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ሃሳቦችን አቀርብላችኋለሁ፡፡

የቤተሰብ ምጣኔ ማለት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሊኖር የሚገባቸውን የልጆች ቁጥር የመመጠን ልምድና በውልደት መካከል ያለውን የጊዜ ርዝመት የመወሰን ጉዳይ ማለት ነው፡፡ ለማብራራት ያህል በቤተሰብ ውስጥ የልጆች ቁጥር መመጠን ማለት ነው፡፡ አይለም እንዴ ኧ… ብልህ የሆኑ ባልና ሚስት እኮ ስለኑሯቸው ይወስናሉ፡፡ እንዲያውም ሰዎች በህይወታቸው ከሚወስኗቸው ጠቃሚ ውሳኔዎች መካከል ስንት ልጆች መውለድ እንዳለባቸው መወሰን አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ እናንስትስ ኧ… በየቤታችሁ የልጆቻችን ቁጥር ወስናችሁ ታወቃላችሁ እንዳልኳችሁ ይህ እኮ ትልቅ ነገር ነው፡፡ እስቲ በጥሞና ከተከታተሉኝ፡

ኃላፊነት የሚሰማችሁ ወላጆች እኮ… ለሚወልዷቸው ልጆች የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ፣ ፍቅርና ድጋፍ መስጠት ይፈልጋሉ፡፡ እናንተስ እንንተም ኃላፊነት እንደሚሰማችሁ እተማመናለሁ፡፡ ለማንኛውመ የልጆችን ቁጥር ለመወሰን ስለሚያስችሉ ዘዴዎች እንነጋገራለን፡፡

እንግዲህ ስለቤተሰብ ምጣኔ ስናነሳ የልጆችን ቁጥር ለመመጠንና አራርቆ ለመውለ የሚያስችሉ ሁለት ዘዴዎች እንዳሉ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ እነሱም ተፈጥሯዊና ዘመናዊ ዘዴዎች ይባላሉ፡፡ ሁለቱም እርግዝናን ይከላከላሉ፡፡ ተፈጥሯዊ ዘዴዎች የሚባሉት ከግንኙነት መታቀብ፣ ቀን መቁጠርና ጡት ማጥባት ናቸው፡፡ ዘመናዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች ደግሞ ኮንዶም (የወንድና የሴት)፣ ዳይፍራም (ብራንፊ)፣ እንክብል፣ ሉፕ፣ በመርፌ የሚሰጥ መከላከያ (ዳይፓፐርቢራ) እና በክንደ የማቀርብ (ኖርፕላንት ካንትራሴሀፕቲቭ ኢምፕላንት) እና

የመሰሰሉት ናቸው፡፡ አያችሁ እንግዲህ እናንተም ከነዚህ ዘዴዎች አንዱን መርጣችሁ እንደምትጠቀሙ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

እንግዲህ ሃሳቤን ላጠቃል፡፡ እናንተ መገንዘብ የሚገባችሁ ዋናው ጉዳይ ኧ… የቤተሰብ ምጣኔ ማለት ኧ… ወላጆች መቼ ልጅ ይ…ተን እና ኧ… ስንት ልጅ ይኑረን ብለው ምላሽ የሚሰጡበት እቅድ መሆኑ ነው፡፡ ይህንንም ተረድታችሁ ከዛሬ ጀምሮ ከባለቤታችሁ ጋር ተወያዩና ወደጤና ጣቢያ በመምጣት ኧ… አገግሎቱን በህክምና ባለሙያ ድጋፍ መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ በተረፈ ዛሬ በውይይቱ ላልተካፈሉ ለምታውቋቸው እናቶች ሁሉ ፍሬ ነገሩን ባገኛችሁት አጋጣሚ እንድታስረዱ ኧ… እስከምንገናኝ ደህና ሁኑ፡፡

(የደቡብ ትምህርት ቢሮ፡፡ 2007፡፡ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣ ከገጽ 22-24)

## አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች
## ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡**

ሀ. ልጆችን መጥኖና አራርቆ መውለድ የሚወሰነው በመንግስት ነው፡፡

ለ. የቤተሰብ ምጣኔ ማለት ወንድና ሴት ልጅን ቀላቅሎ መውለድ ማለት ነው፡፡

ሐ. ኃላፊነት የሚሰማቸው ወላጆች ለልጆቻቸው አስፈላጊውን ነገር ለማሟላት ይፈልጋሉ፡፡

መ. ኮንዶምና በመርፌ የሚሰጥ መከላከያ ዘመናዊ የወሊድ መቆጣጠሪያዎች ናቸው፡፡

## ተግባር ሁለት

### በ"ሀ" ረድፍ ለተዘረዘሩ ቃላትና ሐረጋት በ"ለ" ስር ከተዘረዘሩት ተመሳሳይ ፍቺዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| 1. ድጋፍ | ሀ. ማብራራት |
| 2. ፍቅር | ለ. ብራልጥ |
| 3. ጠቃሚ | ሐ. እገዛ |
| 4. መግለጽ | መ. ሃሳብን መረዳት |
| 5. መገንዘብ | ሠ. መውደድ |
| 6. ብልህ | ረ. አጠናቀቅክ |
| 7. አበቃሁ | ሰ. አስፈላጊ |
| | ሸ. ጎጂ |
| | ቀ. ጥላቻ |

## ተግባር ሦስት

## የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በምንባቡ መሠረት አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. ከጠቃሚ ውሳኔዎች አንዱና ዋነኛው ______________ እንዳለባቸው መወሰን ነው፡፡

ለ. አንድ ጥሪን አክብሮ የመጣን ሰው ________________ ተገቢ ነው፡፡

ሐ. ________ የጤና ኤክስቴሽን ባለሙያ ነች፡፡

መ. በአንቀጽ አራት "ከነዚህ ዘዴዎች1" ተብሎ የተገለጸው ___________ እና _______ የወሊድ መቆጣጠሪያዎች ናቸው፡፡

ሠ. የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት የተገጸው በአንቀጽ ________ ላይ ነው፡፡

## ተግባር አራት

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ አክብቡ፡፡

1. አንደኛው አንቀጽ በስንት ዐረፍተ ነገሮች የተገነባ ነው?

ሀ. በሰባት ለ. በስምንት ሐ. በዘጠኝ መ. በአራት

2. "እንዳደረጋችሁ" በሚለው ሀረግ ባለቤት አመልካቹ ቅጥያ የቱ ነው?

ሀ. እንደ- ለ. - ችሁ ሐ. -ኣችሁ መ. እንደ -ኣችሁ

3. በአምስተኛው አንቀጽ መጀመሪያ መስመር ላይ "ሃሳቤን" በሚለው ቃል "በ" ላይ የተቀጠለችው "ኤ" ሃሳቡ የማን እንደሆነ ይገልፃል ሀ. የወይኒቱ ለ. የተሰብሳቡ አባቶች ሐ. የተሰብሳቢ እናቶች መ. የሁሉም ሃሳብ መሆኑን ይገልፃል፡፡

4. በአንቀጽ ሦስት ላይ የሚገኘው "እንደሚስማችሁ" ከሚለው ሀረግ ዋና ቃሉ?

ሀ. እንደ- ለ. -ም ሐ. -ኣችሁ መ. ሰማ

5. ከሚከተሉት ውስጥ ውስብስብ ዐረፍተ ነገር ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. እናንተም ከነዚህ ዘዴዎች አንዱን መርጣችሁ እንደምትጠቀሙ ተስፋ አድርጋለሁ

ለ. እናቶች ፍሬ ነገሩን ባገኛችሁት አጋጣሚ አስረዱ

ሐ. ስለደመጣችሁ አመሰግናለሁ

መ. መልስ አልተሰጠም

## ተግባር አምስት

**የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ከዋናው ቃሉ ቅጥያዎችን ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡**

ሀ. በህይወታቸው ሐ. ስላዳመጣችሁ ሠ. ስለቤተሰብ

ለ. ታውቃላችሁ መ. አባቶቼ ረ. የሚገባቸውን

## ተግባር ስድስት

**የሚከተለውን ጥያቄ በጽሑፍ መልሱ፡፡**

ሀ. ቤተሰብን መጥኖ አለመውለድ ምን ምን ችግሮችን እንደሚያስከትል በራሳችሁ አገላለጽ በአንድ አንቀጽ ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

# አባሪ አምስት

## በላይ ታች የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል ለሚማሩ ተማሪዎች የቀረበ ምንባብ

## ምንባብ ሁለት

## የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት

**ቅድመ ማንበብ ጥያቄ**

**ተግባር አንድ፡ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩና ያገኛችሁትን መልስ በቃል ተናገሩ፡፡**

ሀ. የቤተሰብ ምጣኔ ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ቤተሰብን አለማመጣጠን የሚያስከትለው ጉዳት ምንድነው?

**ተግባር ሁለት**

**የማንበብ ሂደት**

### የቤተሰብ ምጣኔ

እንደምንናችሁ ውድ እናቶችና አባቶች ደህና ሰነበታችሁ ኧ… ወይኒቱ እባላለሁ በዚህ ቀበሌ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ነኝ፡፡ ኧ… በጥሪያችን መሠረት ሰዓቱን አክብራችሁ በመገኘታችሁ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በጋራ የተገናኘውነው ዛሬ ለመጀመሪያ ጉ አይደል መቼም ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በየጊዜው ውይይት እንዳደረጋችሁ እገምታለሁ፡ እሺ እናቶቼና አባቶቼ ዛሬ ደግሞ የጤና ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ሃሳቦችን አቀርብላችኋለሁ፡፡

የቤተሰብ ምጣኔ ማለት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሊኖር የሚገባቸውን የልጆች ቁጥር የመመጠን ልምድና በውልደት መካከል ያለውን የጊዜ ርዝመት የመወሰን ጉዳይ ማለት ነው፡፡ ለማብራራት ያህል በቤተሰብ ውስጥ የልጆች ቁጥር መመጠን ማለት ነው፡፡ አይለም እንዴ ኧ… ብልህ የሆኑ ባልና ሚስት እኮ ስለኑሯቸው ይወስናሉ፡፡ እንዲያውም ሰዎች በህይወታቸው ከሚወስኗቸው ጠቃሚ ውሳኔዎች መካከል ስንት ልጆች መውለድ እንዳለባቸው መወሰን አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ እናንሰትስ ኧ… በየቤታችሁ የልጆቻችን ቁጥር ወስናችሁ ታወቃላችሁ እንዳልኳችሁ ይህ እኮ ትልቅ ነገር ነው፡፡ እስቲ በጥሞና ከተከታተሉኝ፡

ኃላፊነት የሚሰማችሁ ወላጆች እኮ… ለሚወልዷቸው ልጆች የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ፣ ፍቅርና ድጋፍ መስጠት ይፈልጋሉ፡ እናንተስ እንንተም ኃላፊነት እንደሚሰማችሁ እተማመናለሁ፡፡ ለማንኛውመ የልጆችን ቁጥር ለመወሰን ስለሚያስችሉ ዘዴዎች እንነጋገራለን፡፡

የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

ተግባር ሦስት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ

ሀ. ከላይ ስለቤተሰብ ምጣኔ ምንነት በግምት የመለሳችሁት መልስ ትክክል ነው? ወይስ አይደለም? ትክክል ካልሆነ ትክክል ያልሆነበትን ምክንያት ምንድነው?

ለ. ከዚህ በኋላ ስለቤተሰብ ምጣኔ ምን ተጽፎ እናገኛለን ብላችሁ ትገምታላችሁ?

እንግዲህ ስለቤተሰብ ምጣኔ ስናነሳ የልጆችን ቁጥር ለመመጠንና አራርቆ ለመውለ የሚያስችሉ ሁለት ዘዴዎች እንዳሉ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ እነሱም ተፈጥሯዊና ዘመናዊ ዘዴዎች ይባላሉ፡፡ ሁለቱም እርግዝናን ይከላከላሉ፡፡ ተፈጥሯዊ ዘዴዎት የሚባሉት ከግንኙነት መታቀብ፣ ቀን መቁጠርና ጡት ማጥባት ናቸው፡፡ ዘመናዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች ደግሞ ኮንዶም (የወንድና የሴት)፣ ዳይፍራም (ብራንፊ)፣ እንክብል፣ ሉፕ፣ በመርፌ የሚሰጥ መከላከያ (ዳይፓፕሮቢራ) እና በክንደ የማቀርብ (ኖርፕላንት ካንትራሴሀፕቲቭ ኢምፕላንት) እና የመሰሰሉት ናቸው፡፡ አያችሁ እንግዲህ እናንተም ከነዚህ ዘዴዎች አንዱን መርጣችሁ እንደምትጠቀሙ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

እንግዲህ ሃሳቤን ላጠቃል፡፡ እናንተ መገንዘብ የሚገባችሁ ዋናው ጉዳይ ኧ... የቤተሰብ ምጣኔ ማለት ኧ... ወላጆች መቼ ልጅ ይ...ተን እና ኧ... ስንት ልጅ ይኑረን ብለው ምላሽ የሚሰጡበት እቅድ መሆኑ ነው፡፡ ይህንንም ተረድታችሁ ከዛሬ ጀምሮ ከባለቤታችሁ ጋር ተወያዩና ወደጤና ጣቢያ በመምጣት ኧ... አገግሎቱን በህክምና ባለሙያ ድጋፍ መጠቀም ትችላላችሁ፡፡ በተረፈ ዛሬ በውይይቱ ላልተካፈሉ ለምታውቋቸው እናቶች ሁሉ ፍሬ ነገሩን ባገኛችሁት አጋጣሚ እንድታስረዱ ኧ... እስከምንገናኝ ደህና ሁኑ፡፡

(የደቡብ ትምህርት ቢሮ፡፡ 2007፡፡ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣ ከገጽ 22-24)

## አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች

## ተግባር አራት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱና መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማንበብ በመልሶቻችሁ ላይ ተወያዩበት**

ሀ. ከምንባቡ ስለቤተሰብ ምጣኔ ምን ተረዳችሁ?

ለ. ወሊድን በምን መንገድ ልንቆጣጠረው እንችላለን?

ሐ. ልጅን አራርቆ መውለድ ለምን አስፈለገ?

መ. ወይኒቱ በቤተሰብ ምጣኔ ላይ ካነሳችው ሃሳብ ውስጥ የማትስማሙበት ሃሳብ አለ? ካለ ለምን እንዳልተስማማችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን የውሳኔ ሃሳብ ፃፉ፡፡

## ተግባር አምስት

**የሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት ከነምክንያታችሁ በቃል ተናገሩ፡፡**

ሀ. ወይኒቱ የተሰበሰቡ ሰዎች ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር መወያየታቸውን በእርግጥኝነት ትናገራለች፡፡

ለ. በምንባቡ ውስጥ አልፎ አልፎ "እ.." የሚለው የቀረ ሃሳብ መኖሩን ለማመልከት ነው፡፡

ሐ. ልጅን መጥኖ ለመውለድ የሚወስኑት ባልና ሚስት መሆናቸውን ወይኒቱ ተናግራለች፡፡

መ. እንክብልና ሉፕ ተፈጥሮአዊ የእርግዝና መከላከያዎች ናቸው፡፡

## ተግባር ስድስት

**ለሚከተሉት ቃላት መዝገበ ቃል በማንበብ ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ፃፉ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ወሰነ | ሐ. ብልህ | ሠ. መገንዘብ |
| ለ. አብራራ | መ. ጠቃሚ | |

## ተግባር ሰባት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ አክብቡ፡፡**

1. በአንቀጽ አንድ ላይ በስብሰባው መጀመሪያ ላይ ምን እንደተከናወነው በቅደም ተከተል ሲገልጽ

ሀ. የሰላምታ ለውውጥ፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ ስልተገኙ ማመስገን፣ ርዕስ ማስተዋወቅ ለ. ራስን ማስተዋወቅ፣ ርዕስ ማስተዋወቅ፣ ስለተገኙ ማመሰግነ፣ የሰላምታ ልውውጥ ሐ. የሠላምታ ልውውጥ፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ ርዕስ ማስተዋወቅ፣ ስለተገኙ ማመስገን መ. ራስን ማስተዋወቅ፣ የሠላምታ ልውውጥ፣ ርዕስ ማስተዋወቅ፣ ስለተገኙ ማመስገን

2. የ"ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ነኝ፡፡" በሚለው ዐረፍተ ነገር ከሥሩ የተሠመረበት አውዳዊ ፍቺው

ሀ. የጤና ጥበቃ ባለሥልጣን መሆኗን ይገልጻል፡፡

ለ. የሠፈሩ አንድ ለአምስት መሪ መሆኗን ይገልፃል፡፡

ሐ. በጤና ነክ ጉዳዮች ላይ የሠለጠነች ሠራተኛ መሆኗን ይገልፃል፡፡

መ. መልስ አልተሰጠም፡፡

3. በአንቀጽ አራት ላይ "ከእነዚህ ዘዴዎች" የተባሉት _________ ና ________ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ናቸው፡፡

ሀ. ሰው ሰራሽ ለ. ተፈጥሮአዊ

ሐ. ዘመናዊ መ. "ለ" እና "ሐ" መልስ ናቸው

4. ስለቤተሰብ ምጣኔ ብያኔ የተሰጠው በስንተኛው አንቀጽ ላይ ነው?

ሀ. በአንደኛው ለ. በሁለተኛው

ሐ. በአራተኛው መ. በአምስተኛው

5. ከሚከተሉት ውስጥ ከሰዎች ጋር ገና ስንገናኝ የምናደርገው የሰላምታ ልውውጥ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. እንደምን ሰነበታችሁ? ለ. ደህና ሁኑ፡፡

ሐ. እንደምን አደራችሁ? መ. እንደምን ቆያችሁ?

6. ከሚከተሉት ውስጥ ውስብስብ ዐረፍተ ነገር የቱ ነው?

ሀ. ከሌሎች የጤና ባለሙያዎች ጋር ውይይት እንዳደረጋችሁ እገምታለሁ፡፡

ለ. ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

ሐ. ኃላፊነት እንደሚስማችሁ እተማመናለሁ፡፡

መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

7. “በመገኘታችሁ” በሚለው ቃል ውስጥ ባለቤት አመልካቹ

ሀ. በ-ኣችሁ ለ. -መገኘት- ሐ. -ኣችሁ መ. በ-

**ተግባር ስምንት**

**የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ዋናውን ቃል ከቅጥያዎቹ ነጣጥላችሁ ከፃፉችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ልጆቻችሁን | ሐ. እናቶቼ | ሠ. ሆኑ |
| ለ. እንዳደረጋችሁ | መ. የሚገባችሁ | ረ. ባለሙያዎች |

**ተግባር ዘጠኝ**

**የሚከተለውን ጥያቄ በጽሑፍ መልሱ፡፡**

ሀ. ስለቤተብ ምጣኔ አስፈላጊነት ከተለያዩ ጽሑፎች አንብባችሁ ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

# አባሪ ስድስት

# በታች ላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል ለሚማሩ ተማሪዎች የቀረበ ምንባብ

# ምንባብ ሦስት

## ተግባር አንድ

## የማንበብ ሂደት

### ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች

ውድ የስብሰበው ተሰታፊዎች! እንደምናችሁ? እ… ዘሀራ መሐመድ እባላላሁ፡፡ የእናቶችና የሕፃናት ሀኪም ነኝ፡፡ ዛሬ በዚህ ቦታ ለተገኛችሁ ጎልማሶች ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ <u>አመለካከቶች</u> ትምህርት እንድሰጥ በጎልማሶች ትምህርት አስተባባሪ በመጋበዜ አመሰግናለሁ፡፡ እናንተም ትምህርቱን ለመከታተል እዚህ በመገኘታችሁ ኧ… ከልብ አመሰግናችኋለሁ፡፡

እያችሁ! የቤተሰብ ምጣኔ በቤት ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸውን የልጆች ቁጥር ለመመጠንና አራርቆ ለመውለድ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ልጆችን በእንክብካቤ ለማሳደግና የእናቶችን ጤንነት ለመጠበቅ ይረዳል፡፡ እ… ኑሮንም በአግባቡ ለመምራት ጠቀሜታ አለው፡፡ ይሁን እንጂ ስለቤተሰብ ምጣኔ ሰዎች የተለያዩ አመለካከቶች አሏቸው፡፡

እ… አንዳንድ ሰዎች ስለቤተሰብ ምጣኔ በጎ አመለካከት የላቸውም፡፡ በተለይም እንደእኛ ባሉ ታዳጊ ሀገሮች አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህንን በስፋት ከሚነገሩት አስተያየቶች መረዳት ትችላላችሁ፡፡ ከእነዚህ አስተያየቶች መካከል እ… "የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መጠቀም መሃን ያደርጋል" የሚለው አንዱ ነው፡፡ በዚህ አባባል ትስማማላችሁ? እንዴት መሰላችሁ እ… የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መጠቀም ልጅ መውለድ በማይፈልግበት ጊዜ ብቻ ላለመውለድ የሚያገለግል ዘዴ ነው፡፡ መውለድ ሲፈለግ ደግሞ አግልግሎቱን በማቋረጥ ልጅ መውለድ ይቻላል፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ ከመሀንነት ጋር የሚያያዝ አይደለም፡፡ መሀንነትንም አያስከትልም፡፡ <u>ግልፅ</u> ነው? በጣም ጥሩ፡፡

ሌላው አመለካከት ደግሞ የቤተሰብ ምጣኔ መጠቀም "ልጆችን እንደመግደል ስለሚቆጠር ኃጢያት ነው" የሚል ነው፡፡ ይህንን አባባል ስንቶቻችሁ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እ… የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ልጅ ከመፀነሱ በፊት የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡ ስለዚህ ፅንስን እንደመግደል ተቆጥሮ እንደጨካኝና እንደኃጢያተኛ የሚያስቆጥር አይደለም፡፡

ሦስተኛው አመለካከት ምን መሰላችሁ? እ… "ልጅ በዕድሉ ያድጋል" የሚለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ልጆች ከተወለዱ በኋላ የቤተሰብ ድጋፍና እንክብካቤ ካልደተደረገላቸው ከሚፈለገው ደረጃ ላይ ሊደርሱ አይችሉም፡፡ እ… ስለዚህ ልጆችን መጠኖ መውለድ በእንክብካበ ለማሳደግ ጠቃሚ ነው፡፡ ኧረ ስንቱ… አንድ ልጨምር፡፡

በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩ ወላጆች እንደ … ገቢ ምንጭ በመቁጠር የቤተሰብ ምጣኔን ሲያሳጥሉት ይታያል፡፡ እ… ልጆችን እንደገቢ ምንጭ መቁጠር ማለት ወሊድን ከመቆጣጠር ይልቅ በብዛት በመውለድ ጉልበታቸውን ለመጠቀም መፈለግ ነው፡፡ ይህ እኮ በጣም የሚገርም ነው! ይህ አመለካከት ልጆች ያለዕድሜያቸው <u>በሥራ እንዲጠመዱና</u> ከወላጆቻቸው ማግኘት የሚገባቸውን

ድጋፍና እንክብካቤ እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡ ለእንግልትም ይዳርጋቸዋል፡፡ መቼም ዘርዝሬ አልጨርሰውም፡፡ አንድ ልጨመርና ላብቃ፡፡

እም… አንዳንድ ቤተሰቦች ደግሞ ልጆቻቸውን እንደ ጧሪ ቀባሪ በመቁጠር፣ “ዘር ማብዛት ይገባል” ይላሉ፤ በተጨማም ሁለቱን ፆታዎች ለማግኘት፣ ማለትም ሴት ያላቸወ ወንድ ለማግኘት፣ ወንድ ያላቸው ደግሞ ሴት ለማግኘት ሲሉ የቤተሰብ ምጣኔን አይደግፉም፡፡

በአጠቃላይ ቀደም ብዬ እንደነገርኳችሁ የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች በተለየዩ አመለካከቶች ምክንያት የቤተሰብ ምጣኔን አይደግፉም፡፡ እንደዚህ አይነት አመለካከት ካላቸው ሰዎች የሚወለዱ ልጆች በእድሜያቸው ማግኘት የሚገባቸውን ነገር ስለማያገኙ ለበርካታ ችግሮች ይዳረጋሉ፡፡ ራሳቸውም ተጠቃሚና ደስተኛ አይሆኑም፡፡ ግልፅ ነው? እ… ደህና ዛሬ በቤተሰብ ምጣኔ አጠቃቀም ረገድ ስላሉ የተለያዩ አመለካከቶች ተወያይተናል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ በተመሳሳይ ትምህርት እንድሰጥ ከተጋበዝኩ ልንገናኛ እንችላለን፡፡ ለዛሬው ተሳትፏችሁ በጣም አመሰግናለሁ! ደህና ሁኑ!

(የደቡብ ትምህርት ቢሮ፣ 2007፡፡ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣ 7ኛ ክፍል፡፡ ከገጽ 28-30)

## አንብቦ መረዳት

## ተግባር ሁለት

**በምንባቡ መሠረት የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ “እውነት” ትክክል ካልሆኑ “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡**

ሀ. ልጆችን ተንከባክቦ ለማሳደግና የእናቶችን ጤንነት ለመጠበቅ የቤተሰብ ምጣኔን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

ለ. ስለቤተሰብ ምጣኔ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ባላደጉ ሀገሮች ውስጥ የሚኖሩ ማህበረሰቦች ብቻ ናቸው፡፡

ሐ. በቤተሰብ ምጣኔ መጠቀም ማሀን ያደርጋል፡፡

መ. አብዛኛዎቹ ሰዎች ስለቤተሰብ ምጣኔ በጎ አመለካከት የላቸውም፡፡

## ተግባር ሦስት

**በ”ሀ” ረድፍ ለተዘረዘሩ ቃላትና ሀረጋት በ”ለ” ረድፍ ከተዘረዘሩ አውዳዊ ፍቺያቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

| “ሀ” | “ለ” |
| --- | --- |
| 1. ተሳትፏችሁ | ሀ. የሥራ ጫና መፍጠር |
| 2. አመለካከት | ለ. ልጅ መወለድ አለመቻል |
| 3. ግልፅ | ሐ.ጥሩ |
| 4. በሥራ መጠመድ | መ. ድብቅ |
| 5. መሃን | ሠ. እንቅስቃሴያችሁ |
| 6. በጎ | ረ. ገሀድ |
| | ሰ. አስተያየት |
| | ሸ. ልጅ መውለድ ማቆም |

## ተግባር አራት

**በምንባቡ መሠረት በ"ለ" ረድፍ የተዘረዘሩትን ፍሬ ሃሳቦች በ "ሀ" ረድፍ ከተዘረዘሩ የሃሳቡ መገኛ አንቀጽ ጋር አዛምዱ።**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አንቀጽ ስድስት | ሀ. የቤተሰብ ምጣኔን መጠቀም መሀንነትን አያሳጣም |
| 2. አንቀጽ ሰባት | ለ. የቤተሰብ ምጣኔ መጠቀም ጠቀሜታ |
| 3. አንቀጽ አራት | ሐ. የሰላምታ ልውውጥ ርዕስን ማስተዋወቀ |
| 4. አንቀጽ አንድ | መ. ልጆችን እንደ ጧሪ ቀባሪ መቁጠር |
| 5. አንቀጽ ሦስት | ሠ. የቤተሰብ ምጣኔ ልጅ ከመፀነሱ በፊት ይሰጣል |
| 6. አንቀጽ ሁለት | ረ. ልጅን እንደ ገቢ ምንጭ መቁጠር |

## ተግባር አምስት

**የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም ድርብ ዓረፍተ ነገሮች መሥርቱ።**

ስለዚህ፣ ይሁን እንጅ፣ ነገር ግን፣ ከዚህ የተነሳ

ለምሳሌ፡- በቤተሰብ ምጣኔ መጠቀም የእናቶች ጤንነት ይጠብቃል። <u>ይሁን እንጂ</u> አንዳንድ እናቶችም ስለቤተሰብ ምጣኔ አሉታዊ አመለካከት ያራምዳሉ።

## ተግባር ስድስት

**የሚከተሉትን መስተዋድዶች በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች መሥርቱ።**

ስለ-፣ እንደ-፣ ከ-፣ ለ-

ለምሳሌ፡- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት <u>ሲ</u>ተች አይገባም።

## ተግባር ሰባት

**ለሚከተለው ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ፃፉ።**

ሀ. በምንባቡ በወ/ሮ ዘሀራ ስለቤተሰብ ምጣኔ አሉታዊ አመለካከቶች ተብለው በተዘረዘሩ ሀሳቦች ላይ ትስማማላችሁ? ወይስ? ለምን? ተወያዩና በጋራ የተስማማችሁትን ሃሳብ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

## አባሪ ሰባት

## በላይ ታች የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል ለሚማሩ ተማሪዎች የቀረበ

## ምንባብ ሦስት

## ስለ ቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች

**ቅድመ ማንበብ ጥያቄ**

**ተግባር አንድ**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. በእናንተ አካባቢ የሚገኙ ማህበረሰቦች ስለ ቤተሰብ ምጣኔ ምን ዓይነት አመለካከትን ያራምዳሉ፡፡

ለ. እናንተስ ብዙ ወንድሞችና እህቶች ቢኖራችሁ ወይስ ባይኖራችሁ ደስ ይላችኋል? ለምን

**ተግባር ሁለት**

**የማንበብ ሂደት**

### ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች

ውድ የስብሰበው ተሰታፊዎች! እንደምናችሁ? እ… ዘሀራ መሐመድ እባላላሁ፡፡ የእናቶችና የሕፃናት ሀኪም ነኝ፡፡ ዛሬ በዚህ ቦታ ለተገኛችሁ ጎልማሶች ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች ትምህርት እንድሰጥ በጎልማሶች ትምህርት አስተባባሪ በመጋበዜ አመሰግናለሁ፡፡ እናንተም ትምህርቱን ለመከታተል እዚህ በመገኘታችሁ ኸ… ከልብ አመሰግናችኋለሁ፡፡

አያችሁ! የቤተሰብ ምጣኔ በቤት ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸውን የልጆች ቁጥር ለመመጠንና አራርቆ ለመውለድ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ልጆችን በእንክብካቤ ለማሳደግና የእናቶችን ጤንነት ለመጠበቅ ይረዳል፡፡ እ… ኑሮንም በአግባቡ ለመምራት ጠቀሜታ አለው፡፡ ይሁን እንጂ ስለቤተሰብ ምጣኔ ሰዎች የተለያዩ አመለካከቶች አሏቸው፡፡

እ… አንዳንድ ሰዎች ስለቤተሰብ ምጣኔ በጎ አመለካከት የላቸውም፡፡ በተለይም እንደእኛ ባሉ ታዳጊ ሀገሮች አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህንን በስፋት ከሚነገሩት አስተያየቶች መረዳት ትችላላችሁ፡፡ ከእነዚህ አስተያየቶች መካከል እ… "የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መጠቀም መሃን ያደርጋል" የሚለው አንዱ ነው፡፡ በዚህ አባባል ትስማማላችሁ? እንዴት መሰላችሁ እ… የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መጠቀም ልጅ መውለድ በማይፈልግበት ጊዜ ብቻ ላለመውለድ የሚያገለግል ዘዴ ነው፡፡ መውለድ ሲፈለግ ደግሞ አግልግሎቱን በማቋረጥ ልጅ መውለድ ይቻላል፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ ከመሀንነት ጋር የሚያያዝ አይደለም፡፡ መሀንነትንም አያስከትልም፡፡ ግልፅ ነው? በጣም ጥሩ፡፡

ሌላው አመለካከት ደግሞ የቤተሰብ ምጣኔ መጠቀም "ልጆችን እንደመግደል ስለሚቆጠር ኃጢያት ነው" የሚል ነው፡፡ ይህንን አባባል ስንቶቻችሁ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እ… የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ልጅ ከመፀነሱ በፊት የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡ ስለዚህ ፅንስን እንደመግደል ተቆጥሮ እንደጨካኝና እንደኃጢያተኛ የሚያስቆጥር አይደለም፡፡

ሦስተኛው አመለካከት ምን መሰላችሁ? እ… "ልጅ በዕድሉ ያድጋል" የሚለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ልጆች ከተወለዱ በኋላ የቤተሰብ ድጋፍና እንክብካቤ ካልደተደረገላቸው ከሚፈለገው ደረጃ ላይ ሊደርሱ አይችሉም፡፡ እ… ስለዚህ ልጆችን መጠኖ መውለድ በእንክብካበ ለማሳደግ ጠቃሚ ነው፡፡ ኧረ ስንቱ… አንድ ልጨምር፡፡

| |
|---|
| **የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች**<br>**ተግባር ሦስት**<br>የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልስ ሰጡ፡፡<br>ሀ. ከማንበባችሁ በፊት ለቀረቡ ጥያቄዎች አካበቢያችሁን መሠረት አድርጋችሁ የሰጣችሁት መልስ ከምንባቡ ሃሳብ ጋር ግንኙነት አለ? ወይስ የለም? ከሌለ ምንድነው ልዩነቱ ግለጹ፡፡<br>ለ. ከላይ ባሉ አንቀጾች አልተገለጹም፡፡ ከዚህ በታች ባሉ አንቀጾች ሊቀርቡ ይችላሉ ብላችሁ የምትገምቷቸውን ስለቤተሰብ ምጣኔ የሚሰነዘሩ አሉታዊ አመለካከቶች ዘርዝሩ፡፡ |

በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩ ወላጆች እንደ … ገቢ ምንጭ በመቁጠር የቤተሰብ ምጣኔን ሲያሳጥሉት ይታያል፡፡ እ… ልጆችን እንደገቢ ምንጭ መቁጠር ማለት ወሊድን ከመቆጣጠር ይልቅ በብዛት በመውለድ ጉልበታቸውን ለመጠቀም መፈለግ ነው፡፡ ይህ እኮ በጣም የሚገርም ነው! ይህ አመለካከት ልጆች ያለዕድሜያቸው በሥራ እንዲጠመዱና ከወላጆቻቸው ማግኘት የሚገባቸውን ድጋፍና እንክብካቤ እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡ ለእንግልትም ይዳርጋቸዋል፡፡ መቼም ዘርዝሬ አልጨርሰውም፡፡ አንድ ልጨመርና ላብቃ፡፡

እም… አንዳንድ ቤተሰቦች ደግሞ ልጆቻቸውን እንደ ጧሪ ቀባሪ በመቁጠር፣ "ዘር ማብዛት ይገባል" ይላሉ፤ በተጨማም ሁለቱን ፆታዎች ለማግኘት፣ ማለትም ሴት ያላቸወ ወንድ ለማግኘት፣ ወንድ ያላቸው ደግሞ ሴት ለማግኘት ሲሉ የቤተሰብ ምጣኔን አይደግፋም፡፡

በአጠቃላይ ቀደም ብዬ እንደነገርኂችሁ የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች በተለየዩ አመለካከቶች ምክንያት የቤተሰብ ምጣኔን አይደግፋም፡፡ እንደዚህ አይነት አመለካከት ካላቸው ሰዎች የሚወለዱ ልጆች በእድሜያቸው ማግኘት የሚገባቸውን ነገር ስለማያገኙ ለበርካታ ችግሮች ይዳረጋሉ፡፡ ራሳቸውም ተጠቃሚና ደስተኛ አይሆኑም፡፡ ግልፅ ነው? እ… ደህና ዛሬ በቤተሰብ ምጣኔ አጠቃቀም ረገድ ስላሉ የተለያዩ አመለካከቶች ተወያይተናል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ በተመሳሳይ ትምህርት እንድሰጥ ከተጋበዝኩ ልንገናኛ እንችላለን፡፡ ለዛሬው ተሳትፏችሁ በጣም አመሰግናለሁ! ደህና ሁኑ!

(የደቡብ ትምህርት ቢሮ፣ 2007፡፡ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣ 7ኛ ክፍል፡፡ ከገጽ 28-30)

## አንብቦ መረዳት

## ተግባር አራት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ፡፡**

1. የቤተሰብ ምጣኔ ለምን ይጠቅማል?
2. የቤተሰብ ምጣኔ መጠቀም "ልጆችን እንደ መግደል ይቆጠራል፡፡" የሚለውን አመለካከት ትደግፋላችሁ? ወይሰ? ለምን? ግለጹ፡፡

3. ስለቤተሰብ አሉታዊ አመለካከት ካላቸው ሰዎች የሚወለዱ ልጆች ምን ችግር ያጋጥማቸዋል?
4. በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የቤተሰብ ምጣኔን የሚቃወሙት ለምንድነው?

## ተግባር አምስት

**በምሳሌው መሠረት በቦዶ ቦታ የሚስማማውን ከምንባቡ በመፈለግ ሠንጠረዡን አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

| ተ.ቁ | የፍሬ ሃሳቦች መገኛ አንቀጽ | የቀረቡ ፍሬ ሃሳቦች |
|---|---|---|
| 1 | አንቀጽ አንድ | የሠላምታ ልውውጥ እና ርዕስ ማስተዋወቅ |
| 2 | አንቀጽ ሁለት | |
| 3 | አንቀጽ ሦስት | |
| 4 | አንቀጽ አራት | |
| 5 | አንቀጽ አምስት | |
| 6 | አንቀጽ ስድስት | ልጅን የገቢ ምንጭ አድርጎ መጠቀም |

## ተግባር ስድስት

**ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡**

*ሀ. አመለካከት*　　*ሐ. መሀን*　　*ሠ. በጎ*

*ለ. ግልፅ*　　*መ. በሥራ መጥመድ*

ምሳሌ፡- ተሳትፏችሁ እንቅስቃሴያችሁ

ተግባር ሰባት

የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም ድርብ ዓረፍተ ነገሮች መሥርቱ፡፡

ስለዚህ፣ ይሁን እንጅ፣ ነገር ግን፣ ከዚህ የተነሳ

ለምሳሌ ልጆች የቤተሰብ ድጋፍና እንክብካቤ ካልተደረገላቸው ተፈላጊውን ደረጃ አይደርሱም፡፡

ስለዚህ ልጆችን መጥኖ መውለድና መንከባከብ አስፈላጊ ነው፡፡

## ተግባር ስምንት

**የሚከተሉትን መስተዋድዶች በመጠቀም ውስብስብ ዓረፈተ ነገር መሥርቱ፡፡**

ስለ-፣ እንደ-፣ ከ-፣ ለ-

**ለምሳሌ፡-** በስብሰባው ላይ ስለተገኛችሁ አመስግናለሁ፡፡

## ተግባር ዘጠኝ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደየ አጠያየቃቸው መልሱ፡፡**

ሀ. የምንባቡን ሃሳብ አሳጥራችሁ በአንድ አንቀጽ ፃፉ፡፡

ለ. ወይዘሮ ዘሀራ የቤተሰብ ምጣኔን ለውጥ እንዳይኖር ያደረጉ አሉታዊ መመለካከቶች ብለው በዘረዘሩት ሃሳብ ላይ ትስማማላችሁ? ወይስ? ለምን? አካባቢያችሁን መሠረት አድርጋችሁ ተወያዩና የተስማማችሁበትን ሃሳብ በሁለት አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

**አባሪ ስምንት**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩሚኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚየኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር**

በጋሞ ጎፋ ዞን በኡባ ድብረ ፀሐይ ወረዳ በበቶ አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤት በሚገኙ በሰባተኛ ክፍል በታች ላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በተማሩ ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ፡፡

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው ከላይ ታች እና ከታች ላይ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል ተማሪዎች በየትኛው ቢማሩ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን እንደሚዳብርና ውጤታማ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ለመፈተሽ የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ የምትሰጡት መልስ የጥናቱን ውጤት የተሳካ ወይም ያልተሳካ ሊያደርገው ስለሚችል በጥንቃቄ አንብባችሁ እውነተኛና ትክክለኛ ነው የሚትሉትን መለስ በመስጠት ተባበሩ፡፡

ስለትብብራችሁ አመሰግናለሁ! አጥኚዋ

**ማሳሰቢያ**

ሀ. መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

ለ. ለመጠይቆቹ የሚትሰጡትን መልስ በሚስጥር ያዙት፡፡

ሐ. በመጠይቁ ለቀረቡ ጥያቄዎች በሙሉ መልስ እንድትሰጡ ትጠየቃላችሁ፡፡

መ. በክፍል አንድ ለቀረቡ ጥያቄዎች መልሳችሁን በባዶ ቦታ ፃፉ፡፡

ሠ. በክፍል ሁለት ለቀረቡ ጥያቄዎች አራት አማራጮች ቀርበዋል፡፡

**በመረጣችሁት ምርጫ ሥር ይህን (✓) ምልክት አስቀምጡ፡፡**

**ክፍል አንድ**

**በባዶ ቦታ ተፈላጊውን መረጃ በመሙላት አመልክት/ቺ፡፡**

1. ፆታ ____________
2. እድሜ ___________
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ____________

## ክፍል ሁለት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አራት አማራጭ ደረጃዎች ቀርበዋል በመረጣችሁት ምርጫ ስር ይህን (✓) ምልክት ያድርጉ፡፡**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ | አልስማማም | በፍፁም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በማንበብ ትምህርት ጊዜ የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት ከራሳችሁ ገጠመኞች ጋር እያገናኘን እንድንገመግም የመወያያ ጥያቄዎች ቀርበውልን ነበር፡፡ | | | | |
| 2 | ከልምምዱ በፊት መምህራችን በምንባቡ ርዕስ ዙሪያ በቂ የቀደመ እውቀት ከሌለ በማንበብ ጊዜ እንቅፋት እንዳይሆንብን ከምንባቡ መልዕክት ውስጥ አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም ፍንጭ ይሰጡን ነበር፡፡ | | | | |
| 3 | ከልምምዱ በፊት ለምን እንደምናነብ እንዴት እንደምናነበው ወስነን እንድናነብ መምህራችን ያበረታቱናል፡፡ | | | | |
| 4 | ከልምምዱ በፊት የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ዝግ ባለ ድምፅ ምንባቦችን በግላችን እንድናነብ ሁኔታዎችን ያመቻቹልን ነበር፡፡ | | | | |
| 5 | ከማንበቤ በፊት ለምንና እንዴት ማንበብ እንዳለብኝ መወሰኔ የማንበብ ፍላጎትን ቀስቅሶልኛል፡፡ | | | | |
| 6 | በማንበብ ጊዜ ከማንበባችን በፊት የገመትነውን ግምት እንድናረጋግጥና ቀጣይ ሊመጣ የሚችለውን እንድንተነበይ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥሮልን ነበር፡፡ | | | | |
| 7 | ከዚህ ቀደም መምህራችን ከመጽሐፋችን ውጪ ከጋዜጣዎች፣ ከመጽሔቶች፣ ከመጽሐፎች፣ ወዘተ አንብበን ያገኘናቸውን ቁም ነገሮች በመጽሐፍ ለክፍል ጓደኞቻችን እንድናነብ እና እንድንወያይ ይጋብዙናል፡፡ | | | | |
| 8 | ወላጆቻችሁ ከተለያዩ ጽሑፎች ስለተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች አንብበን በጉዳዩ ዙሪያ እንድንወያይ ያደርጉናል፡፡ | | | | |
| 9 | ከማስታወቂያና ከሌሎች ጽሑፎች የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ ለማግኘትና ለመረዳት የምናደርገው የአነባብ ስልት ተመሳሳይ አለመሆኑን ከልምምዱ ተረድቻለሁ፡፡ | | | | |
| 10 | የምናነበው አንብቦ የመረዳት ክሂላችንን ለማዳበር ሳይሆን በትምህርታችን ጥሩ ውጤት ለማምጣት እና ለማህበራዊ ኑሯችን ለመጠቀም ጭምር መሆኑን በልምምዱ ወቅት ተረድቻለሁ፡፡ | | | | |
| 11 | የአንድን ምንባብ ፍሬ ሃሳብ በቀላሉ ለመረዳት አጠቃላይ መልዕክቱን አስቀድመን ባንገምትም ፍሬ ሃሳቡን ከምንባቡን ረቂቅ አሃዶች አወቃቀር ተነስተን እንድንረዳው ሆኖ ቀርቦልናል፡፡ | | | | |
| 12 | ከዚህ ቀደም ስለ ምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት አስቀድሞ ባይገመትም ስለርዕሱ የቀድመ እውቀት ባይቀሰቀስም የማንበብ ፍላጎትን አልቀንሰም ነበር፡፡ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 13 | ለልምምድ የቀረቡ የመልመጃ ጥያቄዎች ለውይይትና ለመረዳዳት አመቺ ሆነው የቀረቡ ስለሆነ የመልመጃ ጥያቄዎችን እየተወያዩ እና እየተረዳዱ ለመስራት ተችሏል፡፡ | | | | |
| 14 | ለልምምዱ የቀረቡ መልመጃዎች ለአዳዲስ ቃላት ሐረጋት አውዳዊና ቀጥተኛ ፍቺ እንዲሰጥ የሚጋብዙ ስለሆኑ ምንባቡን በተለያዩ የአነባብ ስልት በመጠቀም ደጋግሜ ማንበቤ ለቃላትና ለሐረጋት አውዳዊ ፍቺና ቀጥተኛ ፍቺ እንድሰጥ አስችሎኛል፡፡ | | | | |
| 15 | ለልምምዱ የቀረቡ መልመጃዎች በምንባቡ ዋና ሃሳብ ላይ እንድንወያይና የራሳችንን ሃሳብ እንድንሰጥ የሚጋብዙ ሆነው የቀረቡ ስለሆነ የምንባቡን ዋና ሃሳብ ከግል ገጠመኝ ጋር በማዛመድ የግል አስተያየት ለመስጠት ጥረት አድርጊያለሁ፡፡ | | | | |
| 16 | ለልምምድ የቀረቡ መልመጃዎች የምንባቡን ዋና ሃሳብ ከራሳችን አካባቢ ጋር እያገናዘብን በራሳችን አገላለጽ ሃሳቡን አሳጥረን እንድንገልጽ ምቹ ሆነው ቀረበዋል፡፡ | | | | |
| 17 | ለልምምድ የቀረቡ መልመጃዎች ማንበባችንን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ስለዚህም ምንባቡን ካነበብኩ በኋላ ጥያቄዎችን በመስራት ምን ያህል እንደተረዳሁ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ | | | | |
| 18 | ለልምምዱ የቀረቡ መልመጃዎች ሰዋስዋዊ ይዘቶችን እንድንሰራ አመቺ ሆነው ቀርበዋል፡፡ | | | | |
| 19 | ልምምድ ማድረጌ በግል የተለያዩ ጽሑፎችን ከማንበቤ በፊት ስለምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት እንድገምት፣ የማንበብ ስልቶችን እንድወስን፣ በማንበብ ጊዜ ግምቴ ትክክል መሆን አለመሆኑን እንዳረጋግጥ ካነበብኩ በኋላ የተረዳሁትን ነገር ከራሴ ገጠመኝ ጋር በማገናኘት እንድረዳ አስችሎኛል፡፡ | | | | |
| 20 | በልምምዱ ያገኘሁትን ግንዛቤና እውቀት ለወደፊቱ ተግባራዊ አድርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 21 | በታችላይ ሞዴል ልምምድ ማድረጌ ለወደፊቱ ጥሩ ልምድ አስጨብጦኛል፡፡ | | | | |

**ለሚከተለው ጥያቄ የግል አስተያየታችሁን ስጡ**

22. ታች ላይ ሞዴል አቀራረብ ላይ ተጨማሪ አስተያየት ከላህ/ሽ አብራርታችሁ ፃፉ፡፡ ______

________________________________________________________________

__________________________________________________________

**አባሪ ዘጠኝ**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩሚኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚየኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር**

በጋሞ ጎፋ ዞን በኡባ ድብረ ፀሐይ ወረዳ በቦቶ አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤት በሚገኙ በሰባተኛ ክፍል በታች ላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በተማሩ ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ፡፡

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው ከላይ ታች እና ከታች ላይ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል ተማሪዎች በየትኛው ቢማሩ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን እንደሚዳብርና ውጤታማ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ለመፈተሽ የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ የምትሰጡት መልስ የጥናቱን ውጤት የተሳካ ወይም ያልተሳካ ሊያደርገው ስለሚችል በጥንቃቄ አንብባችሁ እውነተኛና ትክክለኛ ነው የሚትሉትን መለስ በመስጠት ተባበሩ፡፡

ስለትብብራችሁ አመሰግናለሁ! አጥኚዋ

**ማሳሰቢያ**

ሀ. መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

ለ. ለመጠይቆቹ የሚትሰጡትን መልስ በሚስጥር ያዙት፡፡

ሐ. በመጠይቁ ለቀረቡ ጥያቄዎች በሙሉ መልስ እንድትሰጡ ትጠየቃላችሁ፡፡

መ. በክፍል አንድ ለቀረቡ ጥያቄዎች መልሳችሁን በባዶ ቦታ ፃፉ፡፡

ሠ. በክፍል ሁለት ለቀረቡ ጥያቄዎች አራት አማራጮች ቀርበዋል፡፡

**በመረጣችሁት ምርጫ ሥር ይህን (✓) ምልክት አስቀምጡ፡፡**

**ክፍል አንድ**

**በባዶ ቦታ ተፈላጊውን መረጃ በመሙላት አመልክት/ቺ፡፡**

1. ፆታ ____________
2. እድሜ ___________
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ____________

## ክፍል ሁለት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አራት አማራጭ ደረጃዎች ቀርበዋል በመረጣችሁት ምርጫ ስር ይህን (✓) ምልክት ያድርጉ፡፡**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ | አልስማማም | በፍፁም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በማንበብ ትምህርት ጊዜ የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት ከራሳችሁ ገጠመኞች ጋር እያገናኘን እንድንገመግም የመወያያ ጥያቄዎች ቀርበውልን ነበር፡፡ | | | | |
| 2 | ከልምምዱ በፊት መምህራችን በምንባቡ ርዕስ ዙሪያ በቂ የቀደመ እውቀት ከሌለ በማንበብ ጊዜ እንቅፋት እንዳይሆንብን ከምንባቡ መልዕክት ውስጥ አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም ፍንጭ ይሰጡን ነበር፡፡ | | | | |
| 3 | ከልምምዱ በፊት ለምን እንደምናነብ እንዴት እንደምናነበው ወስነን እንድናነብ መምህራችን ያበረታቱናል፡፡ | | | | |
| 4 | ከልምምዱ በፊት የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ዝግ ባለ ድምፅ ምንባቦችን በግላችን እንድናነብ ሁኔታዎችን ያመቻቹልን ነበር፡፡ | | | | |
| 5 | ከማንበቤ በፊት ለምንና እንዴት ማንበብ እንዳለብኝ መወሰኔ የማንበብ ፍላጎትን ቀስቅሶልኛል፡፡ | | | | |
| 6 | በማንበብ ጊዜ ከማንበባችን በፊት የገመትነውን ግምት እንድናረጋግጥና ቀጣይ ሊመጣ የሚችለውን እንድንተነበይ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥሮልን ነበር፡፡ | | | | |
| 7 | ከዚህ ቀደም መምህራችን ከመጽሐፋችን ውጪ ከጋዜጣዎች፣ ከመጽሔቶች፣ ከመጽሐፎች፣ ወዘተ አንብበን ያገኘናቸውን ቁም ነገሮች በመጽሐፍ ለክፍል ጓደኞቻችን እንድናነብ እና እንድንወያይ ይጋብዙናል፡፡ | | | | |
| 8 | ወላጆቻችሁ ከተለያዩ ጽሑፎች ስለተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች አንብበን በጉዳዩ ዙሪያ እንድንወያይ ያደርጉናል፡፡ | | | | |
| 9 | ከማስታወቂያና ከሌሎች ጽሑፎች የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ ለማግኘትና ለመረዳት የምናደርገው የአነባብ ስልት ተመሳሳይ አለመሆኑን ከልምምዱ ተረድቻለሁ፡፡ | | | | |
| 10 | የምናነበው አንብቦ የመረዳት ክሂላችንን ለማዳበር ሳይሆን በትምህርታችን ጥሩ ውጤት ለማምጣት እና ለማህበራዊ ኑሯችን ለመጠቀም ጭምር መሆኑን በልምምዱ ወቅት ተረድቻለሁ፡፡ | | | | |
| 11 | የአንድን ምንባብ ፍሬ ሃሳብ በቀላሉ ለመረዳት አጠቃላይ መልዕክቱን አስቀድመን ባንገምትም ፍሬ ሃሳቡን ከምንባቡን ረቂቅ አሃዶች አወቃቀር ተነስተን እንድንረዳው ሆኖ ቀርቦልናል፡፡ | | | | |
| 12 | ከዚህ ቀደም ስለ ምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት አስቀድሞ ባይገመትም ስለርዕሱ የቀድመ እውቀት ባይቀሰቀስም የማንበብ ፍላጎትን አልቀንሰም ነበር፡፡ | | | | |
| 13 | ለልምምድ የቀረቡ የመልመጃ ጥያቄዎች ለውይይትና ለመረዳዳት አመቺ ሆነው የቀረቡ ስለሆነ የመልመጃ ጥያቄዎችን እየተወያዩ እና እየተረዳዱ ለመስራት ተችሏል፡፡ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ለልምምዱ የቀረቡ መልመጃዎች ለአዳዲስ ቃላት ሐረጋት አውዳዊና ቀጥተኛ ፍቺ እንዲሰጥ የሚጋብዙ ስለሆኑ ምንባቡን በተለያዩ የአነባብ ስልት በመጠቀም ደጋግሜ ማንበቤ ለቃላትና ለሐረጋት አውዳዊ ፍቺና ቀጥተኛ ፍቺ እንድሰጥ አስችሎኛል፡፡ | | | | |
| 15 | ለልምምዱ የቀረቡ መልመጃዎች በምንባቡ ዋና ሃሳብ ላይ እንድንወያይና የራሳችንን ሃሳብ እንድንሰጥ የሚጋብዙ ሆነው የቀረቡ ስለሆነ የምንባቡን ዋና ሃሳብ ከግል ገጠመኝ ጋር በማዛመድ የግል አስተያየት ለመስጠት ጥረት አድርጊያለሁ፡፡ | | | | |
| 16 | ለልምምድ የቀረቡ መልመጃዎች የምንባቡን ዋና ሃሳብ ከራሳችን አካባቢ ጋር እያገናዘብን በራሳችን አገላለጽ ሃሳቡን አሳጥረን እንድንገልጽ ምቹ ሆነው ቀረበዋል፡፡ | | | | |
| 17 | ለልምምድ የቀረቡ መልመጃዎች ማንበባችንን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ስለዚህም ምንባቡን ካነበብኩ በኋላ ጥያቄዎችን በመስራት ምን ያህል እንደተረዳሁ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ | | | | |
| 18 | ለልምምዱ የቀረቡ መልመጃዎች ሰዋስዋዊ ይዘቶችን እንድንሰራ አመቺ ሆነው ቀርበዋል፡፡ | | | | |
| 19 | ልምምድ ማድረጌ በግል የተለያዩ ጽሑፎችን ከማንበቤ በፊት ስለምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት እንድገምት፣ የማንበብ ስልቶችን እንድወስን፣ በማንበብ ጊዜ ግምቴ ትክክል መሆን አለመሆኑን እንዳረጋገጥ ካነበብኩ በኋላ የተረዳሁትን ነገር ከራሴ ገጠመኝ ጋር በማገናኘት እንድረዳ አስችሎኛል፡፡ | | | | |
| 20 | በልምምዱ ያገኙሁትን ግንዛቤና እውቀት ለወደፊቱ ተግባራዊ አድርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 21 | በላይታች ሞዴል ልምምድ ማድረጌ ለወደፊቱ ጥሩ ልምድ አስጨብጦኛል፡፡ | | | | |

**ለሚከተለው ጥያቄ የግል አስተያየታችሁን ስጡ**

22. ላይ ታች ሞዴል አቀራረብ ላይ ተጨማሪ አስተያየት ከላህ/ሽ አብራርታችሁ ፃፉ፡፡ ______

______________________________________________

______________________________________________

# አባሪ አስር

ማንበብን በላይታች ሞዴል በተማሩና በታችላይ ሞዴል በተማሩ ተማሪዎች መካከል ጉልህ የውጤት ልዩነት መኖሩን አለመኖሩን ለማረጋገጥ በጥቅም ላይ የዋለ እስታስቲካዊ ቀመር

1. $S^2 = \frac{\left(x_{1-\bar{x}}\right)^2}{n-1}$

2. t= $\frac{\overline{x_1} - \overline{x_2}}{\sqrt{\frac{(n_{1-1})s^2{}_{1+(n_{2-1})s_2^2}}{\left(n_{1+}\, n_2\right)-2}\ \left(\frac{1}{n_1}+\frac{1}{n_2}\right)}}$

3. s= $\sqrt{\frac{(x-\bar{x})}{n-1}}^2$

ምልክቶች የሚወክሉት

$x_1$= በላይታች የተለማመዱ የእያንዳንዱ ታሳታፊ ውጤት ድምር

$x_2$= በታችላይ የተለማመዱ የእያንዳንዱ ተሳታፊ ውጤት ድምር

$\bar{x}$ = ከናሙና የተገኘ አማካይ ውጤት

$s^2$= የናሙና ልይይት መጠን

s= መደበኛ ልይይት

n= የናሙና አባላት ብዛት

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለፀው የድህረ ምረቃ ተማሪ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራሴ መሆኑንና የተጠቀምኳቸው የመረጃ ምንጮች በትክክል የተጠቀሱ መሆናቸውን በፊርማ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ________________________________

ፊርማ ____________________

ቀን ______________________